# የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ

# የ2016 በጀት ዓመት ረቂቅ አመላካች ዕቅድ

## የልማት ዕቅድና ኢኮኖሚ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ግንቦት 2015 ዓ.ም

ሐዋሳ

## ማውጫ


I. መግቢያ ..... 4
II. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አጭር መግለጫ ..... 5
III. በ2015 በጀት አመት የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች በአጭሩ ሲታይ፤ ..... 10
ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሻሻል ..... 10
የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል ..... 14
የጤና ቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻል ..... 15
የመድሃኒት ደህንነት ቁጥጥርን ማጠናከር ..... 15
የጤና ተቋማት ቁጥጥር ስርዓት ማሻሻል ..... 15
የምግብ ደህንነት ቁጥጥርን ማሻሻል ..... 15
የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ማሳደግና አግባባዊ አጠቃቀምን ማሻሻል ..... 16
የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሻሻል ..... 17
በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና ፈጠራ ማሻሻል ..... 17
የጤና መሰረተ ልማት ማሻሻል ..... 17
የጤና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማጠናከር ..... 19
የጤና ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል ..... 19
III. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ..... 21
የጤና ዘርፍ ራዕይ ..... 21
የጤና ዘርፍ ተልዕኮ ..... 21
ዕሴት ..... 21
IV. ዓላማ ..... 21
V. የጤናው ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 21
VI. የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች ..... 22
VII. በዝግጅት እና በትግበራ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች ..... 22
VIII. በ2015 በጀተ አመት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ..... 23
IX. በ2016 በጀት አመት የታቀዱ ዒላማዎች፤ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት ..... 25
1 . ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሻሻል፤ ..... 25
1.1 የስነ ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህጻናት፣ የህጻናት እና የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና 25
1.1.1 የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ..... 25
1.1.2 የእናቶች ጤና አገልግሎት ..... 28
1.1.3. የጨቅላ ሕፃናት እና የሕፃናት ጤና አገልግሎት ማሻሻል፤ ..... 29

1.1.4. የክትባት አገልግሎት ..... 30
1.2 የሥርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ ..... 32
የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ ..... 35
1.3 የበሽታ መከላከልእና ቁጥጥር ማሻሻል ..... 38
1.3.1 ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቲጥኝና ሄፓታይተስ ከመከላከልና መቆጣጠር ..... 38
1.3.2 ሌሎች በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ..... 45
1.4 የህክምና አገልግሎት መሻሻል ..... 58
1.4.1 የህክምና አገልግሎት ..... 58
1.4.2 የድንገተኛ ሕመም፣ የአካል ጉዳት አዳጋ እና ጽኑ ህክምና አገልግሎቶች ..... 60
1.4.3 የጤና ስርአት ኢኖቬሽን፤ ጥራት፤ ፍትሃዊነትን እና አመራርን ማሻሻል፡ ..... 62
1.4.4 የላቦራቶሪ ህክምና እና ሌሎች ዳያግኖስቲክ አገልግሎቶችን ጥራት ማሻሻል ..... 67
1.4.5 የደም ባንክ አገልግሎት ..... 67
1.5 ሀይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎት ..... 68
1.6 የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እና የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አገልግሎትን ማጠናከር ..... 71
2. የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል ..... 75
3. የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሻሻል ..... 76
4. የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማሻሻል ..... 78
5. የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ማሳደግና አግባባዊ አጠቃቀምን ማረጋገጥ ..... 82
6. በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና ፈጠራ ማሻሻል ..... 84
7. የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደርን ማሻሻል ..... 86
8. የጤና መሰረተ ልማት ማሻሻል ..... 89
9. የጤና ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል ..... 90
10. አመራር እና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል ..... 93
11. የጤና ዲጂታል ቴክኖሎጂን ማሻሻል ..... 94
12. የባህላዊ ህክምናን ማሻሻል፤ ..... 97
13. ጤና በሁሉም ዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መካተቱን ማረጋገጥ ..... 98
14. የግሉ ዘርፍ በጤና ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ ..... 98
ተጨማሪ ከተለያዩ ዘርፎች ጋር የሚሰሩ ስራዎችን በሚመለከት ..... 99
ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮትችና ሊወሰዱ የታሰቡ የመፍትሄ እርምጃዎች ..... 101

# I. መግቢያ

በጤናው ዘርፍ መሪ የአስር አመት ዕቅድ እና ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የሁለተኛውን የአምስት ዓመት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሁም ከአምስት ዓመት ዕቅድ መነሻ የሶስተኛዉን አመት ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በመቀናጀት ትግበራዉን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተነደፉት አስራ አራት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመተግበር የሚያስችሉ ስትራቴጂክ እርምጃዎችን በማስቀመጥ በየደረጃው ያለው አመራር እና ባለሙያዎች በዕቅድ አፈጻጸም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች በየወቅቱ በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ዘርፉ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዘርፉ ትኩረት ከተሰጡት መስኮች አንዱ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እና ፍትሃዊ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል በተዋረድ የሚገኝ አመራርና ባለሙያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በዘርፉ የሚዘጋጀው አንኳር ዕቅድ ወጥ፤ የተቀናጀ እና የተናበበ እንዲሆን በማድረግ በየደረጃው ለሚገኙ ፈጻሚ አካላት በተገቢው መንገድ ዕቅዱን በማውረድና አፈፃፀሙን በየወቅቱ በመከታተል የተፈለገውን ግብ ለማሳካትና ውጤት ለማምጣት እንዲቻል ከዚህ በፊት ተመሳሳይ የዕቅድ አዘገጃጀት፤ የአፈጻጸም ክትትል አሰራር ስርዓትን በዘርፉ በመዘርጋት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ ሁሉ አሁንም ካለፈው ተሞክሮ በመውሰድ የሚታዩትን ድክመቶችና ተግዳሮቶችን በመፍታት የተሻለ ስራ በመስራት የሕብረተሰቡ እርካታ የሚሻሻልበት መንገድ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በሶስተኛ አመት የተቀመጡትን ዒላማዎች ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም በአሁን ወቅት በተጨባጭ የተደረሰበትን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ፤ ወረዳዎች እና ,ጤና ተቋማት የተናበበ ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ይህ የ2016 በጀት ዓመት ረቂቅ አመላካች ዕቅድ ሰነድ በማዘጋጀት በክልል ጤና ቢሮ ስር የሚገኙት ሥራ ዘርፎችና እና ተጠሪ ተቋማት አስፈላጊ ግብአት እንዲያካትቱበት እና በመጨረሻ በቢሮ አመራሮች ታይቶ ከፀደቀ በኃላ በተዋረድ የሚገኙ ዞኖች፤ ወረዳዎችና ጤና ተቋማት እንደ መነሻ እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

ይህ ረቂቅ አመላካች ዓመታዊ ዕቅድ አጠቃላይ ይዘት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎችን ስኬት የሚለኩ የመለኪያዎች መነሻ ዒላማዎች እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ትኩረት የሚሰጣቸው እርምጃዎች እና ዋና ዋና ተግባራትን ያካተተ ሲሆን በክልሉ የሚገኙ ተቋማት የአከባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ሰነዱን በማዳበር ዞኖች፤ ወረዳዎችና ጤና ተቋማት ዕቅዳቸው ሲያዘጋጁ በግብአትነት በመጠቀም የተናበበ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ይጠበቃል፡፡

## II. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አጭር መግለጫ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ2012 ዓ.ም ሐምሌ ወር አስረኛዉ ክልል ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እንደ ክልል ሥራ ከጀመረ ሶስት ዓመት ያህል አስቆጥሯል፡፡ ክልሉን በስተደቡብ ኦሮሚያ ክልል(ጉጂ ዞን) እና ጌዴኦ ዞን፣ በስተሰሜን ኦሮሚያ ክልል(ምዕራብ አርሲ ዞን)፣ በስተምዕራብ የደቡብ ክልል(ወላይታ ዞን) እና በስተምስራቅ የኦሮሚያ ክልል(ምዕራብ አርሲ ዞን) ያዋስኑታል፡፡ የክልሉ የቆዳ ስፋት **7,139.1** ስኩየር ኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡ የክልሉ መቀመጫ ሐዋሳ ከተማ ሲሆን ከአዲስ አበባ በ275 ኪ.ሜ ርቀት በስተ ደቡብ አቅጣጫ ይገኛል፡፡ ክልሉ ለአስተዳደር በሚያመች መልኩ ሐዋሳ ከተማን ጨምሮ በዉስጡ 31 የገጠር ወረዳዎች፣ በ7 የከተማ አስተዳደሮች እና በ636 ቀበሌያት (89 የከተማና 547 የገጠር ቀበሌያት) የተዋቀረ ነው፡፡

በክልሉ ሶስት አይነት የአየር ንብረት ያለ ሲሆን ከነዚህም ዉስጥ 29.3% ቆላማ፣ 55% ወይና ደጋማ እና 15.7% ደጋማ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛው ቦታ ከመሬት ወለል በላይ በ3300 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘው የጋራምባ ተራራ ጫፍ ሲሆን ዝቅተኛው ሥፍራ ደግሞ በሎካ አባያ ወረዳ በአባያ ዙሪያ ቀበሌ በአባያ ሃይቅ አካባቢ ከባሕር ወለል በላይ በ1200 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡

የክልሉ ህዝብ ብዛት በ2007 ማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ መነሻ መሰረት በ2016 ዓ.ም **4,748,639** ይገመታል፡፡ ይህም የሃገሪቷን 5% ያህል የህዝብ ብዛት የያዘ ሲሆን በክልሎች ደረጃም በ6ኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኛው የክልሉ ህዝብ ሰፍሮ የሚገኘው በሁሉም የክልሉ ክፍል ሆኖ በምዕራብ በኩል ከሌላዉ አንፃር አሰፋፈሩ ሲታይ የተራራቀ የህዝብ አሰፋፈር ያለ ሲሆን በክልሉ በአንድ ስኩየር ኪሎ ሜትር በአማካይ **665** ሰዎች ይኖሩበታል፡፡ የክልሉ የህዝብ አሰፋፈር በገጠር በከተማ ሲታይ 79% የሚሆነው በገጠር ሲሆን ቀሪው 21% በከተማ የሚኖር ነው፡፡





ስዕል-1 የክልሉ ካርታ

በ2016 በጀት ዓመት ከክልሉ ህዝብ መካከል ሴቶች 2,394,739(50.43%)፤ ወንዶች ደግሞ 2,353,900(49.57%) መሆኑ የሚገመት ሲሆን በመውለድ እድሜ ክልል (ከ15-49 የእድሜ ክልል) ውስጥ የሚገኙ ሴቶች 1,106,433(23.3%) እና ነፍሰጡር የሆኑ እናቶች መጠን 164,303(3.46%)፣ በህይወት የሚወለዱ ህፃናት 164,303(3.46%)፣ እድሜያቸው ከአንድ አመት በታች የሆኑ ህጻናት 151,482(3.19%)፣ ከሁለት ዓመት በታች ህፃናት 246,929(5.2%)፣ ከአምስት ዓመት በታች 740,788(15.6%) እና ከ15-59 ዕድሜ ክልል የሚገኙ 2,293,593(48.3%) መሆኑን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ስሌት ያሳያል፡፡

## የጤና ተቋማት መረጃ

ባሳለፍናቸው አመታት በጤና አገልግሎት አቅርቦት ህብረተሰቡን ለመድረስ የጤና ተቋማት ግንባታ በከፍተኛ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ውስጥ 21 የመንግስት ሆስፒታሎች(1 ኮምፕርሄንስፍ እስፔሻላይዝድ፣ 5 አጠቃላይ እና 15 የመጀመሪያ ደረጃ)፣ 136 ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎች(132 የመንግስት፣ 2 የፖሊስ እና 2 የመያድ) እና 551 ጤና ኬላዎች ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት 1 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል እና በተለያዩ ወረዳዎች 9 ጤና አጠ/ጣቢያዎች በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙት ግንባታቸው ሲጠናቀቅ የሆስፒታሎች ብዛት ወደ 22 የጤ/አ/ጣቢያ ብዛት 145 ይደርሳል፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ጤና ተቋማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ የሚገኙ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 5 ሆስፒታሎች፣ 4 ጤና ጣቢያዎች እና ከ180 በላይ የተለያዩ ክሊኒኮች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከክልሉ ህዝብ ብዛት አንጻር የጤና ተቋማት ስርጭት በንጽጽር ሲታይ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንጻር ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ የመያድና የግል ክሊኒኮች ምንም እንኳን በጤና ተቋማትና ህዝብ ጥምርታ ንፅፅር ውስጥ ባይካተቱም ለህብረተሰቡ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡




ስዕል-2፡ የጤና ተቋማት ስርጭት በካርታ ሲታይ

## የጤና ተቋማት ብዛት ከህዝብ ጥምርታ አንፃር(2016 በጀት ዓመት)

| የተቋሙ አይነት | አሁን ያለ ተቋም ቁጥር | አሁን ያለው የጤና ተቋም ህዝብ ጥምርታ | የአለም ጤና ድርጅት የጤና ተቋም ህዝብ ጥምርታ መስፈርት | አጠቃላይ የሚያስፈልግ | ጉድለት |
|---|---|---|---|---|---|
| ኮምፐርሄንስቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | 1 | 1: 4,748,639 | 1: 5,000,000 | 1 | 0 |
| አጠቃላይ ሆስፒታል | 5 | 1: 949,728 | 1: 1,000,000 | 5 | 0 |
| የመጀ/ደረጃ ሆስፒታል | 15 | 1: 316,575 | 1፡ 100,000 | 47 | 32 |
| ጤና አጠ/ጣቢያ | 136 | 1: 34,916 | 1: 25,000 | 189 | 53 |
| ጤና ኬላ | 551 | 1: 8,618 | 1፡ 5,000 | 950 | 399 |

## የጤና አገልግሎት ሽፋን

የጤና አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለማዳረስ ባለፉት አስርት ዓመታት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን እስከአሁን ባለዉ የጤና አገልግሎት ሽፋን በጤና ጣቢያ 72.0% በጤና ኬላ 58.0%፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 31.9%፣ በአጠቃላይ ሆስፒታል 100% እና በኮምፕርሄንስቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል 100% መድረሱን ያሳያል፡፡ በቀጣይ ዓመት በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ጤና ጣቢያዎች ተጠናቀው ስራ ሲጀምሩ የጤና አጠባበቅ ጣቢያ ሽፋኑ ወደ 76.7% ይደርሳል፡፡

## የተቋማት እና የህዝብ ብዛት መረጃ በየወረዳዉ ሲታይ (2016 በጀት ዓመት)

| ተ.ቁ | የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ስም | የሆስፒታል ብዛት | የጤ/አ/ጣቢያ ብዛት | የጤና ኬላ ብዛት | የህዝብ ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አለታ ጩኮ ከተማ | 1 | 1 | 4 | 55,526 | |
| 2 | አለታ ጩኮ ወረዳ | 0 | 7 | 20 | 175,668 | |
| 3 | አለታ ወንዶ ከተማ | 1 | 0 | 0 | 59,868 | |
| 4 | አለታ ወንዶ ወረዳ | 0 | 7 | 27 | 208,100 | |
| 5 | አርቤጎና ወረዳ | 1 | 4 | 30 | 159,428 | |
| 6 | አሮሬሳ ወረዳ | 1 | 5 | 15 | 113,038 | |
| 7 | በንሣ ወረዳ | 0 | 7 | 22 | 210,221 | |
| 8 | ብላቴ ዙሪያ ወረዳ | 0 | 5 | 17 | 152,856 | |
| 9 | በና ዙሪያ ወረዳ | 1 | 5 | 24 | 165,403 | |
| 10 | በሪቻ ወረዳ | 1 | 3 | 13 | 135,273 | |
| 11 | ቡራ ወረዳ | 0 | 2 | 8 | 56,378 | |
| 12 | ቡርሣ ወረዳ | 1 | 3 | 18 | 101,285 | |
| 13 | ጫቤ ጋምቤልቱ ወረዳ | 0 | 2 | 9 | 88,051 | |
| 14 | ጭሬ ወረዳ | 1 | 3 | 12 | 131,792 | |
| 15 | ጭሮኔ ወረዳ | 0 | 1 | 9 | 51,683 | |
| 16 | ዳኤላ ወረዳ | 0 | 1 | 5 | 49,928 | |
| 17 | ዳሌ ወረዳ | 0 | 10 | 32 | 264,644 | |
| 18 | ዳራ ወረዳ | 1 | 3 | 20 | 129,953 | |
| 19 | ዳራራ ወረዳ | 0 | 3 | 14 | 121,766 | |
| 20 | ዳራ ኦትልቾ ወረዳ | 0 | 3 | 15 | 116,614 | |
| 21 | ዳዬ ከተማ | 1 | 1 | 3 | 44,395 | |
| 22 | ጎርቼ ወረዳ | 0 | 5 | 19 | 137,080 | |
| 23 | ሐዌላ ወረዳ | 0 | 4 | 11 | 113,900 | |
| 24 | ሐዋሳ ዙሪያ ወረዳ | 1 | 5 | 23 | 182,791 | |
| 25 | ሆኮ ወረዳ | 0 | 2 | 14 | 105,428 | |
| 26 | ሁላ ወረዳ | 1 | 3 | 16 | 105,604 | |
| 27 | ለኩ ከተማ | 1 | 0 | 1 | 41,997 | |
| 28 | ሎካ አባያ ወረዳ | 1 | 5 | 22 | 116,789 | |
| 29 | ማልጋ ወረዳ | 1 | 4 | 23 | 162,218 | |
| 30 | ሻፋሞ ወረዳ | 0 | 2 | 14 | 73,757 | |
| 31 | ሸበዲኖ ወረዳ | 0 | 6 | 23 | 209,063 | |
| 32 | ጤጢቻ ወረዳ | 0 | 2 | 15 | 82,681 | |
| 33 | ወንሸ ወረዳ | 0 | 5 | 17 | 132,172 | |
| 34 | ወንዶ ገነት ከተማ | 1 | 1 | 0 | 22,144 | |
| 35 | ወንዶ ገነት ወረዳ | 0 | 3 | 14 | 164,021 | |
| 36 | ይርጋለም ከተማ | 1 | 1 | 4 | 88,411 | |
| 37 | ሐዋሳ ከተማ አስተዳደር | 4 | 12 | 18 | 418,712 | |
| | **አጠቃላይ ድምር** | **21** | **136** | **551** | **4,748,639** | |

## III. በ2015 በጀት አመት የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች በአጭሩ ሲታይ፤

በ2015 በጀት ዓመት በተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ስር የሚገኙ ዋና ዋና የአፈፃፃም መለኪያዎች ከወረዳ ወረዳ እና ከተቋማት ተቋማት አፈፃፃሙ ሲታይ የተለያየ መሆኑ የተመላከተ ሲሆን በክልል ደረጃ በያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ ዝርዝር መነሻ የተሰሩ ስራዎችን ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ከዚህ በታች በቀረበዉ ፅሁፍ ማየት ይቻላል፡፡

### ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሻሻል

### የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት

ጥራቱን የጠበቀ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ለማሻሻል የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተቋማትን አቅም በማሳደግ አዳዲስ የቤተስብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለመጨመር የሚያስችሉ ስራዎች ሲሰሩ ቆይቷል፡፡ ከዚህ በፊት አገልግሎት በማይሰጡ ተቋማት አገልግሎት የማይሰጡባቸው ምክንያቶች ከተለየ በኂላ የጤና ተቋማት ስልጠና በመስጠትና ግብአት በማሟላት ስራ ማስጀመርና እና የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የበኩላቸው ድርሻ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

በበጀት አመቱ ከታቀዱ ዋና ዋና ተግባሮች አንዱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት 835,478 (92%) ለሚሆኑ እድሜቸው በወሊድ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች አገልግሎቱን ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 32,635 (24%) የሚሆኑ እናቶች ከወሊድ በኂላ የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

### የእናቶች ጤና አገልግሎት

በ2015 በጀት ዓመት በጤና ተቋማት 181,749 (ከ100% በላይ) የሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶች ቢያንስ ለአንድ ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ሲሆን 149,361(93%) የሚሆኑ እናቶች ደግሞ ለ4 ጊዜ ክትትል አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም 131,829(82%) ለሚሆኑ እናቶች በሰለጠነ ባለሙያ የታገዘ የወሊድ አገልግሎት ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ በሰባት ቀን ውስጥ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ሽፋን 178,245 (ከ100% በላይ) ለማድረስ ተችሏል፡፡ 6,765(5.1%) እናቶች በቀዶ ጥገና የወሊድ አገልግሎት ማግኘት ችለዋል፡፡ ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ህፃናት መጠንም 4 ከ 1000 ከሚወለዱ ህፃናት ላይ መሆኑን መረጃችን ያሳያል፡፡

### የህፃናት ጤና እና የክትባት አገልግሎት

በ2015 በጀት ዓመት እድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ 148,261(100%) ህጻናት የፀረ አምስት ክትባት ለሶስተኛ ጊዜ ማግኘት የቻሉ ሲሆን 158,909(ከ100% በላይ) የሚሆኑ ህፃናት ደግሞ የክትባት

አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ ዙር ኩፍኝ መከላከያ ክትባት 148,537(ከ100% በላይ) ለሚሆኑ ህፃናት አገልግሎቱን ማድረስ ተችሏል፡፡

### የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት

እድሜያቸው 14 አመት ለሆናቸው ልጃገረዶች የሁለተኛውን የማህጸን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት በሚያዝያ ወር 2015 በጀት ዓመት በዘመቻ ለመስጠት ታቅዶ ከኮቪድ 19 ክትባት ጋር በማቀናጀት 75,793 (91%) ለሚሆኑ ልጃገረዶች አገልግሎቱን ማድረስ ተችሏል፡፡

### ሥርአተ ምግብ በተመለከተ

በየወሩ የእድገት ክትትልና ማበልጸግ የሚደረግላቸው እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን በበጀት ዓመቱ 205,522(88%) ላይ ተደርሷል፡፡ ቫይታሚን ኤ የወሰዱ ህጻናት ሽፋን 471,456(75%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የደም ማነስ መከላከያ የአይረን ፎሌት ኪኒን የወሰዱ ነፍሰጡር እናቶች ሽፋን 134,478(84%) ማድረስ ተችሏል፡፡

### የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ

በክልሉ እስከአሁን የሰቆጣ ቃልኪዳን ትግበራ በ10 ወረዳዎች እየተከናወነ ያለ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት በሙከራ ደረጃ አዲስ 4(አራት) ወረዳዎች ይጀመራል ተብሎ ታቅዶ ያልተጀመረ ቢሆንም በማስፋት እቅዱ ላይ በየዓመቱ 4 ሌሎች ወረዳዎችን በመጨመር 2015 በጀት አመት ያልተጀመሩ 4 ወረዳዎችን ጨምሮ፣ በ2016 በጀት አመት ወደ 18 ወረዳዎች ከፍ ለማድረግ እና ከቢግዊን በተገኘዉ የገንዘብ ድጋፍ የማስፋፋት ምዕራፍ ወረዳዎች ላይ ትግበራውን የሚያግዙ መነሻ ጥናቶችን ለማከናወን ToR ተጠናቋል፡፡

ለጤናማ እና ቀጣይነት ያለው የአመጋገብ ፖሊሲ ጥቅም ላይ የማዋል ስርዓት በኢትዮጵያ ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የመረጃ መሰብሰብ ስራ በክልላችን ተሰርቶ ዉጤትም ይፋ ሆኗል፡፡

## የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ

### የኤች አይ ቪ በሽታን የመከላከል እና ቁጥጥር በተመለከተ

ኤች አይ ቪ፣ ቂጥኝ እና ጉበት (Hepatitis B) በሽታ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል በበጀት ዓመቱ የነፍሰ ጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የኤች አይ ቪ ምርመራ ሽፋን 100% የደረሰ ሲሆን የቂጥኝ ምርመራ 81% እና የጉበት (Hepatitis B) ምርመራ 59% ደርሷል፡፡ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝባቸው ነፍሰጡር፣ ወላድ እና የሚያጠቡ እናቶች የጸረ ኤች.አይ.ቪ ህክምና አገልግሎት ሽፋን 24% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ለኤች አይቪ የተጋለጡ ህፃናት የኤች አይቪ ምርመራ ሽፋን 33% ደርሷል፡፡

በክልል ደረጃ 24,306 ሰዎች ኤችአይቪ በደማቸው ይኖራል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 51% (የመጀመሪያው ዘጠና አምስት ግብ) የሚሆኑት ተመርምረው ውጤታቸውን ያወቁ ሲሆን ውጤታቸውን ካወቁት ውስጥ 10,529 የፀረ HIV መድኃኒት እየወሰዱ ያሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 279

እድሜያቸው 0-14 ዓመት የሆኑ ህጻናት ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የፀረ HIV መድኃኒት ከሚወስዱት አዋቂዎችና ህጻናት ውስጥ በደማቸው ያለው የ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ50 ኮፒ በታች የሆኑት ሽፋን ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በክልል ደረጃ 95% ማድረስ ተችሏል።

በ2015 በስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ተደረሰው የተመረመሩ ሴተኛ አደሪዎች 84% ሲሆን በአጠቃላይ የኮንዶም ስርጭቱ 42% ለማድረስ ተችሏል።

በክልል፤ ሀዋሳ ከተማ፤ በወረዳዎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችና የልማት ተቋማት የኤድስ ፈንድ 0.5% የሚያዋጡ ሴክተሮችና ተቋማት ከተገኘ የኤድስ ፈንድ ተጠቃሚ ሠራተኞች አሁን በቁጥር 142 ሲሆኑ 2% የሚያዋጡ የክልል፤ ሀዋሳ ከተማና ወረዳዎችን 22% ማድረስ ተችሏል።

በቀጣይም በ2025 እኤአ ለማሳካት የተቀመጠውን የሶስቱን 95 ግቦች ለማሳካት በመረጃ ላይ ተመርኩዞ በተለዩት ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችና ከፍተኛ የኤች አይቪ ስርጭት ያለባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

### የቲቢና ስጋደዌ በሽታን የመከላከል እና ቁጥጥር በተመለከተ

የሁሉም አይነት የቲቢ በሽታ ልየታ ሽፋን 6769 (147%) ለመድረስ ተችሏል፡ ከዚህ በተጨማሪ የቲቢ ህክምና ሙሉ ለሙሉ ያጠናቀቁ የቲቢ ህሙማን ሽፋን 97% ላይ ደርሷል።

### በወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ውስጥ 513,644 ለሚሆኑ የወባ ህሙማን ተጠርጣሪዎች የላቦራቶሪና የፈጣን ምርመራ ተደርጎ በወባ በሽታ መያዛቸው ለተረጋገጠ 128,411 ሰዎች የህክምና አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከባለፈው አመት በ316% መጨመሩን ያሳያል።

### ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር ተግባራት

በአዋቂዎች የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን ከባለፉት አመታት አንፃር ሲታይ ልየታው በሪፖርቱ የተሻለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በአዋቂዎች የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋንንም የተሻለ ለማድረግ ተችሏል። ይህ አፈፃፀም ከሚጠበቀው አንፃር ግን ያነሰ መሆኑ ሪፖረቱ ያሳያል።

### የህክምና አገልግሎቶችን ማሻሻል

በክልል አቀፍ ደረጃ 4,513,378, ተገልጋዮች የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ይህም በህዝብ ጥምርታ አኳያ የአገልግሎቱ ምጣኔ (OPD attendant per capita) 1.05 ደርሷል። በተያያዘም በሆስፒታል ተኝቶ የመቆያ ጊዜ (Average length of Stay) 3.6 ሲሆን የአልጋ መያዝ መጠን ደግሞ (Bed occupancy rate) 65% ላይ ይገኛል።የኢትዮጵያ ጥራት ለጥምረት (EHAQ 4th cycle) ትግበራ አፈጻጸም 58.3% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የሆስፒታሎች ሪፎርም ትግበራ 71.6% ማድረስ ተችሏል።

በተጨማሪም ሆሰፒታል ቁልፍ መለኪያዎች ዉስጥ ተኝቶ ህክምና መረጃ አሞላል 74.9%፤ ጽዱና ምቹ ሆሰፒታል ማድረግ ስራ 82.8%፤ የህሙማን እርካታ 82.6% ታካሚው ሀኪሙን እስኪያገኝ ድረስ የሚፈጀዉ ቆይታ ጊዜ 24.3 ደቂቃ ማድረስ ተችሏል፡፡ የሆስፒታሎች ቦርድና የማህበረሰብ ፎርም ከሚጠበቀው በታች ቢሆንም በዓመቱ ያለዉ አፈጻጸም የቦርድ 41% እና ማህበረሰብ ፎርም 37% የተመዘገበ በመሆኑ ቀጣይ ዓመት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ሆኖ ታይቶዋል፡፡

የስፔሻሊቲና ሰብ-ስፔሻሊቲ ህክምና አገልግሎት ፍኖተ ካርታ መሰረት በክልል ደረጃ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በፍኖተ ካርታውም መሰረት 2 የሰብ-ስፔሻሊቲ ህክምና ማዕከሎች (Nuclear medicine and Rehabilation center) ተመርጠው አንድ በወንዶ ገነት ሆስፒታል ዉስጥ የህክምና መገልገያ መሳሪያ በማስገባት ላይ ይገኛል፡፡ በይርጋዓለም አጠቃላይ ሆስፒታል የኩላልት እጥበት ስራ ለማስጀመር ግብኣቶችን በማስገባት ቀጣይ ጊዜ ስራ በማስጀመር በዚህ ጉዳይ ከክልል ሪፈር የሚደረጉ ህሙማን እንግልት ለማስቀረት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## ድንገተኛና ጽኑ ህክምና አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ በድንገተኛና ጽኑ ህክምና አገልግሎት ሰፊ ስራ የተሰራ ሲሆን ለአብነት የአንቡላስ አገልግሎት ምላሽ ያገኙ 80%፤ ጽኑ ህክምና አገልግሎት የጀመሩ ሆስፒታሎች አምስት የደረሱ እና ድንገተኛ ክፍል ሞት ወደ 0.23% በማዉረድ በተጨማሪም ሶስተኛ ወገን ህክምና አገልግሎት የጀመሩ ሆስፒታሎች 42.8% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ደም ባንክ አገልግሎትን ማሻሻል

በበጀት ዓመት ዉስጥ በ2 ማዕከላት 7113 (80%) ዩኒት ደም ተሰብስቧል፡፡ ደም ከለገሱት በጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች 40% ያህሉ ከአዲስ ጀማሪ ደም ለጋሾች ሲሆን የተሰበሰበው ደም ሙሉ በሙሉ ከበጎ ፈቃድ ደም ለጋሾች ነው፡፡

## የጤና አገልግሎት ጥራት ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ በጤና አገልግሎት ጥራት ስራ በሰፊዉ የተሰራ ሲሆን በዋናነት የሆስፒታሎች አገልግሎት ጥራት ሪፎርም(HSTQ) ትግበራ አፈጻጸም 71%፤ ተኝቶ ታካሚ የሞት ምጣኔ 1.3% በማዉረድና በአጠቃላይ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ህሙማን በቁጥር 10,340 ሲሆን የቀዶ ህክምና በአግባቡ ማግኘታቸዉን የሚያረጋግጥ ፎርም የተሞላላቸዉ (SSCU) 89.3% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ማሻሻል

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አገልግሎትን ለማሻሻል በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማሻሻያ ፍኖተ-ካርታን እውን ለማድረግ እንዲያስችል በክልሉ የሚገኙትን ሁሉንም ጤና ኬላዎች ለመለየት በተሰራው

ስራ የ551(100%) ጤና ኬላዎችን መረጃ በመተንተን የልየታ ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን በመረጃውም መሰረት 387(70%) ቤዚክ፤ 69(13%) ኮምፕሬሄንሲቭ እና 95(17%) Merged መሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

የወረዳ ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸምን በተመለከተ በወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ክትትል የተደረገ ሲሆን የ2015 የ2ኛ ሩብ አመት ሪፖርት በመሰብሰብና በመተንተን ግብረመልሱንም ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ተሰጥቷል። በዚህም በአጠቃላይ 35 ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች፤ 134 የመጀመሪያ ደረጃ አሃዶች እና 606 ቀበሌዎች ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በራስ ምዘናው 3(8.5%) ወረዳዎች፤ 52(38%) የመጀመሪያ ደረጃ አሃዶች እና 134(22%) ቀበሌዎች ሞዴል መሆናቸውን በራስ ግምገማ መስፈርት አረጋግጠዉ ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን የአፈጻጸም ደረጃቸው በክልል ደረጃ የማረጋገጥ ስራ የሚሰራ ይሆናል።

በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በጤና ጣቢያዎች የኦአር ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ 2 ጤና ጣቢያዎች ለማስጀመር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

## የሃይጅን ስራዎችን በተመለከተ

በዋን ዋሽ፣ በኮዋሽ ፣በዩኒሴፍ እና በቲ-ዋሽ ወረዳዎች የሳኒቴሽን ግብይት ማእከላትን በማቋቋም እንድሁም የሳኒቴሺን ግብዓትን በመግዛትና በመጠቀም ህብረተሰቡ የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት እንድገነባ በማድረግ ሰፊ ርብርብ የተደረገ ሲሆን በዚህም የተሻሻለ መፀዳጃ ሽፋን 38% ማድረስ ተችሏል። ቀበሌያትን ሜዳ ላይ ከመፀዳዳት ነፃ ለማድረግ ከተለያዩ ደረጃ ከሚገኙ አመራሮች ጋር የንቅናቄ መድረክ የተደረገ ሲሆን ድጋፍና ክትትልም በተለያዩ ጊዜ ተደርጓል። በዚህም ሜዳ ላይ ከመፃዳዳት ነፃ የሆኑ ቀበሌያት ሽፋን 40% ማድረስ ተችሏል።

## የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል

በክልል ደረጃ የተቋቋመው የድንገተኛ ኦፕሬሽን ማዕከል ኮሚቴ በቋሚነት በሳምንት አንድ ጊዜ እየተገናኙ ስራዎችን መገምገም ችለዋል። በሕብረተሰብ ጤና እንስትቲዩት በኩል በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የተመረጡ ጤና ተቋማት በአጠቃላይ 656,813.50 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የመድሀኒት፤ ህክምና መሳሪያዎች እና ግብዓትቶች ተሰራጭቷል። በፌዴራል መንግስት ለግብአት የሚሆን ለሕብረተሰብ ጤና እንስትቲዩት 734,591.2 ብር ድጋፍ ተደርጓል።

በክልሉ በበጀት አመቱ የኮሌራ ወረርሽን በሀዋሳ ከተማ ዉስጥ የተከሰተ ሲሆን 81 ኬዞች ሪፖርት ተደርገዋል። የወባ ወረርሽኝም በአንዳንድ ወረዳዎች የተከሰተ ሲሆን 393,708 **ታማሚዎች** ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 101,664 በወባ በሽታ መያዛቸው ተረጋግጦ ህክምና ተደርጎላቸዋል፡

ኮቪድ 19 ወረርሽኝ አስመልክቶ እስከአሁን ድረስ በጠቅላላው **105,118** ሰዎች ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ **12,998** ፖዜቲቭ የሆኑ ሲሆን በአጠቃላይ የሞቱ **246** ሰዎች መሆናቸዉ ታዉቋል፡፡

## የጤና ቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻል

### የመድሃኒት ደህንነት ቁጥጥርን ማጠናከር

ጥራቱ እና ደህንነቱ በተጠበቀ መድኃኒት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ በመድኃኒት ተቋማት ላይ የኦዲቲንግ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ነው፡፡ በዚህም 550,000(አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ብር በላይ የሚገመቱ ህገ ወጥ መዲኃኒት ምርቶችን ከ21 የግል ተቋማት ተሰብስቦ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡

በ4 ዙር በህገ-ወጥ የመድኃኒት አዘዋዋሪዎች፤ ደረጃዉን ያልጠበቁና ተመሳስለዉ የተሰሩ የመድሃኒት ምርቶች ላይ የገበያ ዳሳሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በ3 ዙር (75%) ማካሄድ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በ4 ዙር ህገ-ወጥ የመድሃኒትና ንግድ ዝውውር፤ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና ተመሳስለው የተሰሩ መድኃኒቶች ላይ የሰርቬላንስ ስራ ለመስራት ታቅዶ 2 ጊዜ(50%) ማካሄድ  የተቻለ ሲሆን በሰርቪላንስ ውጤት መሠረት በሁሉም ተቋማት ማለትም 14 በሚሆኑ መድኃኒት ቤቶችና መደብሮች የኦፕሬሽን ስራ መስራት ተችሏል፡፡ የናርኮቲክ እና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ከመቆጣጠር አንጻር ሰፊ የቁጥጥር ስራ ተከናውኗል፡፡

### የጤና ተቋማት ቁጥጥር ስርዓት ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ በክልል ደረጃ የአገሪቷን ስታንዳርድ ለሚያሟሉ የጤና ተቋማት ቁጥጥር የተደረገባቸው በክልሉ መንግስት ስር ባሉ የጤና ተቋማት መካከለኛ ክሊኒኮች 70 ታቅዶ 59(84%)፣ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ 65 ታቅዶ 58(89%)፣ ጠቅላላ ሆስፒታሎች በቁጥር 5 ታቅዶ 4(80%)፣ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 23 ታቅዶ 22(96%)፣ ልዩ ክሊኒክ 20 ታቅዶ 16(80%)፣ ልዩ ማዕከል 6 ታቅዶ 5(83%)፣ መድኃኒት መደብር 145 ታቅዶ 140(96%) እና መድኃኒት ቤት 57 ታቅዶ 53(93%) ተከናዉኗል፡፡

### የምግብ ደህንነት ቁጥጥርን ማሻሻል

የምግብ ደህንነት ቁጥጥርን ለማጠናከር አንዱ የሚከናወነው ተግባር አስፈላጊውን መስፈርቶች በሟሟላት ምግብን መዝግቦ የገበያ ፍቃድ መስጠት ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ለ5 ምግብ አምራች ድርጅቶች እና 2 የምግብ አከፋፋይ ድርጅቶች እንዲሁም ለ11 መድኃኒት ቤት እና 23 መድኃኒት መደብር የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡ በ10 የምግብ አምራች እና 50 የምግብ አከፋፋይ ተቋማት ላይ ድህረ ፍቃድ ኦዲትንግ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 6(60%) የምግብ አምራች እና 40(80%) የምግብ አከፋፋይ ተቋማት ላይ የድህረ ፍቃድ ኦዲቲንግ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ተችሏል፡፡

ከባዕድ ነገር ጋር የተቀላቀሉ እና ህገወጥ የምግብ ምርቶችን የመለየት፣ የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት ስራዎችን በተመለከተ በምግብ ገበያ ማዕከላት እና የምግብ ችርቻሮ ድርጅቶች ላይ በተለዩ የምግብ ዓይነቶች ላይ 8 ጊዜ ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡በ4 ዙር በተለዩ የምግብ ዓይነቶች ላይ ምርት ተኮር የሆነ የገበያ ቅኝት/market survey/በገበያ ማዕከላት ለማድረግ ታቅዶ 3 ዙር (75%) ማካሄድ ተችሏል፡፡

654,560(ስድስት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ስድሳ) ብር በላይ የሚገመቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸዉ እና የገላጭ ጽሑፍ የሌላቸዉ ምርቶች ተሰብስበው እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ 426 በሚሆኑ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ላይ ስጋራን ከማጨስ ነፃ ለማድረግ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡

### የትንባሆ ምርት ቁጥጥር ሥራን ማጠናከር

ህዝብ በሚሰበሰብባቸዉና የተከለከሉ ቦታዎችን ከትምባሆ ጭስ ነጻ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሰፊ ሥራ ለመስራት ተችሏል፡፡ ይህንንም ለማጠናከር 800 የሚሆኑ ሲጋራ ማጨስ ክልክል መሆኑን የሚገልፁ ጽሑፎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡ 1,329,500 ብር የሚያወጡ በህገ-ወጥ መንገድ የገቡ የትምባሆ ምርቶች ላይ የቁጥጥር ስራ ተሰርቶ ምርቱ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡

### ለጤና ባለሙያዎች ብቃት ማረጋገጫ መስጠትና የቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር

አዲስ የሙያ ምዝገባ ፍቃድ ምስክር ወረቀት 1010 ታቅዶ 889(88%) ለሚሆኑ ባለሙያዎች ለመስጠት የተቻለ ሲሆን የሙያ ምዝገባ ፍቃድ ምስክር ወረቀት ዕድሳት ደግሞ 672 ታቅዶ 526(78%) ተከናውኗል፡ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ (CPD) ሰርትፊኬት አቅርበው እንዲታደስላቸዉ ለ125 ታቅዶ 111(89%) ተከናውኗል፡፡

## የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ማሳደግና አግባባዊ አጠቃቀምን ማሻሻል

### የፋርማሲ አገልግሎት እና መረጃ ማሻሻል በተመለከተ፤

በበጀት አመቱ ሰባት የማህበረሰብ ፋርማሲዎች ተከፍተዉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሁለት ሆስፒታሎች ለኦዲት ምቹ የሆነ ፋርማሲ አገልግሎት ተጀምሯል፡፡ በ19 ጤና ተቋማት የዳጉ2 የመድኃኒት መረጃ አያያዝ ስርዓት ወደ ስራ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡በክልሉ ያሉ ሁሉም ጤና ተቋማት (94%) በየጊዜዉ RRF በመላክ አስፈላጊ የሆኑ የፕሮግራም መድኃኒቶችን በመዉሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በክልሉ ያሉ ሁሉም ሆስፒታሎችና የተመረጡ ጤና ጣቢያዎች የመድኃኒት ምጠና እንድሰሩ ተደርጓል፡፡

### የህክምና መሳሪያዎችን ተከላና ጥገና በተመለከተ

በበጀት አመቱ 73 ፍሪጆችና 73 ሶላሮች ተተክሏል፡፡ በ22 ጤና ተቋማት ኦክስጂን ኮንሰንትሬተሮች፣ ፍሎወ ስፕሊተር፣ ፔሽንት ሞኒተር እና ፓልስ-ኦክሲሜትር ተከላ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በ44 ጤና ተቋማት የተከላና የአጠቃቀም ኦሬንቴሽን በዘመቻ ተሠጥቷል፡፡ በሁሉም ወረዳዎች በዘመቻ በመዞር የወላዶች አልጋ ጥገና ተደርጓል፡፡

## የመድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት

በአሁኑ ወቅት አማካይ የህይወት አድንና መሠረታዊ የመደበኛ መድሃኒቶች አቅርቦት አፈፃፀም 76% እና የፕሮግራም 95% መሆኑን ያሳያል፡፡ አጠቃላይ የመሠረታዊ መድሃኒቶች አማካይ አቅርቦት አፈፃፀም 85.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ የመድኃኒት ብክነት 1.8% ላይ ይገኛል፡፡

በበጀት አመቱ ውስጥ ጤና ተቋማቱ በራሳቸዉ ከሚገዙት መድኃኒት ዉጭ የክልሉ ጤና ቢሮ በድጎማ የመደበኛ በጀት በብር 30,000,000(ሰላሳ ሚሊዮን) ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች፣ ሪኤጀንቶች፣ የህክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች ለጤና ተቋማት ተመድቧል፡፡

የህክምና መሣሪያዎችን በተመለከተ በጤና ኘሮግራም በኩል 16,650,150 ብር ዋጋ ያላቸው የህክምና መሳሪያዎች ከክልሉ መጋዘኖች ተሰራጭተዋል፡፡

## የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ የሴቶች የብቃት ማጎልበቻ ስልጠና ለ12,945 ሴቶች ስልጠናውን የጀመሩ ሲሆን 12,565 ሴቶች ስልጠናውን አጠናቀዋል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ስልጠና ያጠናቀቁትን ምዘና ለማካሄድ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ የሰለጠኑ ሴቶችን ወደ ስራ በማስገባት የሞዴል ቤተሰብ ሽፋን 278,572(30%) ላይ ይገኛል፡፡

## በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና ፈጠራ ማሻሻል

### ወረዳን መሰረት ያደረገ የተናበበ እቅድ ዝግጅት

ወረዳን መሰረት ያደረገ የተናበበ የዘርፉ ዕቅድ ለሚዘጋጀው ከሁሉም ዞንና ወረዳዎች ለተውጣጡ የዕቅድ ዝግጅት ባለሙያዎች ስልጠና በተዋረድ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ወረዳዎች እና ጤና ተቋማት ዕቅዳቸው አቅደዋል፡፡

### የክትትል እና ግምገማ ስርዓት መገንባት

ከዳይሬክቶሬቶች እና ከተጠሪ ተቋማት የሚላኩ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የመገምገም እና ግብረ መልስ የመስጠት ስራ በከፊል የተከናወነ ሲሆን በተጨማሪ ቢሮዉ ከዞንና ወረዳዎች ጋር በመሆን የየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም የተገመገመ ሲሆን የ6 ወራት አፈፃፀም ግምገማም በዳይሬክቶሬቶች ደረጃ ተካሂዷል፡፡ የሪፖርት ሙሉዕነት ወቅታዊነት አፈፃፀሙ 44% እና 92% የደረሰ መሆኑ ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

## የጤና መሰረተ ልማት ማሻሻል

በክልላችን በአጠቃላይ እየተገነቡ ያሉና የተገነቡ ተቋማትን በሚመለከት 6 ሆስታፒሎች፤ 13 ጤና ጣብያዎች፤ 5 ፋርማሲዎች፤ 1 ኦር ብሎክ፤ 1 ሪጅናል ላብራቶሪ፤ 5 የጤና ባልሙያዎች ማደሪያ፤2ኛ ትውልድ ጤና ኬላዎች፤ 1 ኮምፕርሄንሲቭ ጤና ኬላ እና ሌሎች 17 የተለያዩ በጤና ተቋማት ውስጥ

የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም እስከ 2015 በጀት ዓመት ያሉበትን የአፈጻጸም ከታች በዝርዝር ቀርቧል፡፡

ከዚህ በፊት እየተገነቡ የቆዩ ስድስት ሆስፒታሎችን በሚመለከት የቡርሳ እና የወንዶ ገነት ሆስፒታሎች 100% ተጠናቀው የጊዜያዊ ርክክብ ተደርጎ ስራ የጀመሩ ሲሆን የቦና ሆስፒታል ማስፋፊያ 58%፣ የዳዬ ሆስፒታል 90%፣ የአላሙራ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 85%፣ የአላሙራ G+3 ማስፋፊያ ብሎክ 30%፣ ለኩ G+3 ማስፋፍያ ብሎክ 30% የደረሱ ሲሆን በ2016 ለመስራት ለታቀደው የጎርቼ ኮምፓክት የመጀመሪያ ሆስፒታል የዲዛይን እና ሰነድ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡
እየተገነቡ ያሉ 13 ጤና ጣብያዎችን በሚመለከት የዳራ ቀባዶ፣ የአለታ ጩኮ፣የሎኮ አባያ ሀንጣጤ እና የኦዶላ ጤና ጣብያዎች 100% የተጠናቀቁ ሲሆን ስራ ለማስጀመር ያልተሟሉ የመጸዳጃ ቤት፤ የዘበኛ ቤት እና የፕላሴንታ ፒት ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ሌሎች አለታ ወንዶ 70%፤ ጭሬ 85%፤ አርቤጎና 85%፤ ሃዋሳ ዙሪያ 45%፤ ሁላ 85%፤ ኤቻማ 40%፤ ሆኮ 30%፤ ለኩ 70%፤ ይርባ 55% የደረሱ ሲሆን በ2016 አዲስና ተጨማሪ ለሚገነቡት የአዋዬ ቀራሮ እና ሩፎ ጫንጮ ጤና ጣብያዎች የጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ፋርማሲዎች በሚመለከትእ ተገነቡ ካሉት 5 ፋርማሲዎች መካከል ሻመና ጎዶና ጋሉኮ ህሪዬ፣ ሚሪዲቻ እና ሞቶ ፋርማሲዎች የተጠናቀቁ ሲሆን ጤጥቻና 2ኛ ሞጊሳ 70%፣ ማልጋኖ እና አባያ ታካ 75%፣ ስንቡራ ገደቤ እና ጉጉማ 40% ተጠናቋል፡፡

ጨፌ ኮትጅዌሳ ጤና ጣቢያ ኦር ብሎክ ውል የተቋረጠ ሲሆን ከዛም በሁላ ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ውድቅ ሆኗል፡፡ ይርጋለም ሪጅናል ላበራቶሪ ግንባታው 85% ደርሷል፡፡ እየተገነቡ ካሉት 5 የባለሙያ ማደሪያችን በሚመለከት የዳማ ባንቆ፤ የአባያ ዙሪያ፤ የወሌ ማጋዶ እና ሃጤሳ የተጠናቀቁ ሲሆን የጣራቱ ውል ተቋርጧል፡፡ ሁለተኛው ትውልድ ጤና ኬላ ያሉን ሁለት ሲሆኑ ሁለቱም ሆማቾ ጫዋ እና ሁሮ ጤዋሮ 100% ተጠናቀዋል፡፡ ዳሌ ዳጋራ ኮምፕርሄንሲቭ ጤና ኬላ ግንባታን በሚመለከት ግንባታው እተከናወነ ሲሆን 25 ፐርሰንት ደርሷል፡፡

የተለያዩ 17 ፕሮጀክቶች በሚመለከት ሃንጣጤ ሆስፒታል አጥር ስራ 100%፤ ደራራ ኤርጎኖሚክስ 100%፤ አለታ ጩኮ ሴፕቲክ ታንክ 10%፤ ይርጋለም ድያሌስስ 100%፤ ሃንጣጤ ሴፕቲክ ታንክ 100%፤ ሎኮ ኣባያና አባያ ዙሪያ (መጸዳጃ ቤት፣ ዘበኛ ቤት፣ ፕላሲንታ ፒት፣ኢንሲነሪተር) 30%፤ ሁላ እና አርቤጎና(መጸዳጃ ቤት፣ዘበኛ ቤት፣ፕላሲንታ ፒት፣ኢንሲነሪተር)55%፤ ዳራ እና አለታ ጩኮ (መጸዳጃ ቤት፣ ዘበኛ ቤት፣ፕላሲንታ ፒት፣ኢንሲነሪተር) 40%፤ አለታ ወንዶ እና ጭሬ(መጸዳጃ ቤት፣ዘበኛ ቤት፣ፕላሲንታ ፒት፣ኢንሲነሪተር) 30%፤ የስብሰባ አዳራሽ 25%፤ የወጣቶች ስነ ተዋልዶ 40%፤ ፋልቃ እና ፈቃ ጤና ጣብያዎች ጥገና 50%፤ ሁሮ ጠዌሮ 2ኛ ትውልድ ወደ ኮምፐርሄንሲቭ ጤና ኬላ ማሳደግ 60%፤ ይርጋለም ሆስፒታል ሜዲካል ወርክ ሾፕ ሪኖቬሽን 90% ደርሰዋል፡፡

## የጤና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማጠናከር

የተቀናጀ የሰው ሀብት መረጃ ስርዓት /iHRIS/ በክልሉ ደረጃ ሲሰተሙን መጠቀም እንዲችሉ በጤና ሚኒስቴር መረጃ ማእከል በኩል ተጭኖ ለክልሉ የዳታ ማስገቢያ አካውንት ተፈጥሯል፡፡ በክልል ደረጃ ዳታ ማስገባት ተጀምሯል፡፡ የMFR መረጃ ሥርዓትን በተመለከተም በጤና ቢሮ ስር የሚገኙ የግል፤ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የጤና ተቋማት መረጃ በMaster Facility Registry (MFR) ተመዝግቦ ወቅታዊ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የeHMIS (DHIS2) የመረጃ ሥርዓት በተመለከት የሶፍትዌር ከስተማይዜሽን እና የማልማት ስራ በፌደራል በመጠናቀቁ ከክልላችን በተውጣጡ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ፍተሻ ተደርጎለት አስፈላጊዉ ማስተካከያ በሙሉ ከተደረገ በኃላ በተዋረድ ለባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የelectronic Medical Record System (EMR) ትግብራን በለኩ አጠቃላይ ሆስፒታል ሙሉ ለሙሉ በጤና ሚኒስቴር ድጋፍ የተጀመረ ሲሆን በቱላ መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልም በአዲስ መልክ እና በአዳሬ አጠቃላይ ሆስፒታል ደግሞ የቀድሞዉን በአዲሱ በመቀየር እየተጀመረ ይገኛል፡፡ የኤሌክተሮኒክ የማህበረሰብ የጤና መረጃ ስርዓት (eCHIS) ለማጠናከር ሲባል ስርዓቱን ተጠቅመው የቤተሰብ ምዝገባ የጀመሩ ጤና ኬላዎችን 248(45%) ጤና ኬላዎች ለማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ የአባወራ ምዝገባ 298,418(77%) ሲሆን የቤተሰብ አባል ምዝገባ 1,355,872(72%) ማድረስ ተችሏል፡፡ ሁሉንም አፕልኬሽን በመጠቀም አገልግሎት እንዲሰጡ ሁለት ወረዳዎች ማለትም በና ዙሪያና ዳራ ኦትልቾ ተመርጠዉ ሙሉ በሙሉ ስልጠና ወስደዉ ወደ ስራ መግባት ችለዋል፡፡ በዳሌ ወረዳ ደግሞ የeCHISን አገልግሎት ከጣት አሻራ (Biometrics) ጋር በማስተሳሰር እየተሰራ ይገኛል፡፡ በክልሉ በአጠቃላይ አፕልኬሽኑን በመጠቀም አገልግሎት መስጠት የጀመሩትን ጤና ኬላዎች ብዛት 134(54%) ማድረስ ተችሏል፡፡

በተመረጡ ጤና ተቋማት የeAPTS ትግበራ/የDAGU 2.0 መረጃ ሥርዓት፤ በሰቆጣ ዲክላሬሽን ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የተተገበረ የመረጃ ስርዓት እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ የኤሌክትሮኒክ ስራዎች ማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

## የጤና ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል

የመደኛዉን የጤና ሴክተር ተግባራት ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ከልማት አጋር ድርጅቶች በዓመቱ መሰብሰብ ከነበረበት 310 ሚሊዮን ETB ዉስጥ በዘጠኝ ወራት **293,521,286.43** ETB እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ ይህም አፈጻጸሙ ከዕቅዱ 94.6% የደረሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

በባለፈው በጀት ዓመት የፀደቀውን የማዐጤመ አዋጅ ለማስተግበር የሚከናወኑ ተግባራትን፣ ስርዓቱ የሚተገበርባቸውን ወረዳዎች ቁጥር ለማሳደግ፣ የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት በማስተባበር

ውጤታማ የማህበረሰብ ንቅናቄ እና የቅስቀሳ ተግባራት በማከናወን የተጠቃሚ ዜጎች ሽፋን ከፍ ለማድረግ፣ ከክልሉ የሚገኙ ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር የጤና ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ እንዲሁም የማህበራዊ የጤና መድህን ሥርዓት ለማስጀመር የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማጠናቀቅን የተመለከቱ ስትራተጂያዊ ጉዳዮችን ያካተተ መሪ ዕቅድ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ቢሆንም በክልል ደረጃ ሁሉን አቀፍ የጤና መድህን 142,453,130 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ በ41 ወረዳዎች እና ክ/ከተማዎች በዘጠኝ ወሩ 127,280,554 ብር (89.3%) መሰብሰብ ተችሎአል፡፡

## III. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

### የጤና ዘርፍ ራዕይ

☞ ጤናማ፣ ምርታማና የበለጸገ ኅብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው፡፡

### የጤና ዘርፍ ተልዕኮ

☞ ጥራቱን የጠበቀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ፓኬጅ በመስጠት እና በመቆጣጠር የህዝቡን ጤና ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡

### ዕሴት

☞ ወጥነት/አንድነት፣ ታማኝነት፣ ሐቀኝነት
☞ ግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት እና ሚስጥር ጠባቂነት
☞ አለማዳላት
☞ ህግ አክባሪነት
☞ ሩህሩህነት
☞ አርአያነት
☞ ተባባሪነት
☞ ሙያ አክባሪነት
☞ ለውጥ/ፈጠራ

## IV. ዓላማ

☞ በጤናው ዘርፍ በአምስት አመት ዕቅድ የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት እንዲቻል በተዋረድ የተናበበና የተቀናጀ ዕቅድ በማዘጋጀት የተሻለ ውጤት ለማምጣት ነው፡፡

## V. የጤናው ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች

1) ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሻሻል
2) የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ አስተዳደር ሥርዓትን ማሻሻል
3) የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሻሻል
4) የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማሻሻል
5) የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ማሳደግና አግባባዊ አጠቃቀምን ማረጋገጥ
6) በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትንና ፈጠራን ማሻሻል
7) የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ማሻሻል
8) የጤና መሰረተ ልማትን ማሻሻል
9) የጤና ፋይናንስ ስርዓትን ማሻሻል
10) አመራር እና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል
11) የጤና ዲጂታል ቴክኖሎጂን ማሻሻል
12) የባህላዊ ህክምናን ማሻሻል
13) ጤና በሁሉም ዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መካተቱን ማረጋገጥ (ዘርፈ ብዙ ትብብር
14) የግሉ ዘርፍ በጤና ዘርፍ ያለውን ተሳትፎና አስተዋጽኦ ማሳደግ

## VI. የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች

1) ጥራትና ፍትሃዊነት /Transformation in quality and equity of health care/
2) የመረጃ አብዮት / Information revolution/
3) ተነሳሽነት ያለዉ፣ብቃት ያለው እና ሩህሩህ የጤና ሰራተኛ መፍጠር / Motivated, competent and compassionate health workforce/
4) በጤና ፋይናንስ ለውጥ መፍጠር /Health financing/
5) የጤና አመራር መፍጠር /leadership/

## VII. በዝግጅት እና በትግበራ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች

### በዝግጅት ምዕራፍ፡

- ለዕቅድ የሚያስፈልጉ ቅደመ ዝግጅት ስራዎችን ማጠናቀቅ እነርሱም፡- የዕቅድ መርኃ ግብር ማዘጋጀትና በሚመለከታቸው አካላት ማፀደቅ፤
- ከአጋር ድርጅቶች የሚገኙ የሃብት ልየታ ስራ መስራት፤
- ለዕቅድ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ማሰባሰብ ማለትም በ2015 በጀት አመት የታቀዱትን ዒላማዎች የደረሱበት ደረጃ መለየት፤
- በዕቅድ ሂደት ላይ ዳሰሳ ማካሄድና በዳሰሳው የተገኙት ግኝቶች ለ2016 በጀት አመት በግብአትነት መጠቀም፤
- ለዕቅድ ዝግጅት የሚረዳ መመሪያና የዕቅድ መስሪያ ቅጾችን ማዘጋጀትና ለጥቅም ዝግጁ ማድረግ፤
- ዕቅድ የሚሰራበት ሶፍትዌር ከሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች ጋር በመቀናጀት እንዲሰራ ማድረግ፤
- አመላካች የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀትና በሚመለከታቸው አካላት ሰነዱ እንዲዳብር ማድረግ፤
- በተዋረድ ለዕቅድ አስተባባሪዎች ማብራሪያ መስጠት፤
- ለእቅድ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ማሰራጨት፤ለዕቅድ ዝግጅት የሚያስፈልጉ ፋይናንስ ማፈላለግና ለዞኖችና ለወረዳዎች ማሰራጨት፤

### በትግበራ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች

- በዕቅድ አዘገጃጀት ላይ በተዋረድ ማብራሪያ መስጠት እና ዕቅዱ ሲዘጋጅ ድጋፍ መስጠት፤
- የተዘጋጀውን ዕቅድ በየደረጃው የማጠቃለል ስራ መስራት፤
- በክልል ደረጃ የዕቅድ ማጠቃለል ስራ በመስራት ከዞኖችና ከወረዳዎች ጋር ማጣጣም፤
- በተጠቃለለው ዕቅድ መሰረት ረቂቅ አንኳር ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- ረቂቅ አንኳር ዕቅድ ለከፍተኛ አመራሮች በማቅረብ ማስተቸትና ማስፀደቅ፤
- የተዘጋጀውን አንኳር ዕቅድ ሰነድ በቢሮ ደረጃ በዞኖችና ወረዳዎች ጋር የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ፤

- ○ በጸደቀው አንኳር ዕቅድ መነሻ በተዋረድ ዝርዝር ዕቅድ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤
- ○ የተዘጋጀውን ዝርዝር ዕቅድ ሰነድ ከአጋር ድርጅቶች፤ በዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም በተጠሪ ተቋማት ጋር የማናበብ ስራ መስራት፤
- ○ በአገር አቀፍ ደረጃም የተናበበ ዕቅድ ሰነድ እንዲኖር ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር የማናበብ ስራ መስራት፤
- ○ የተናበበውን ዕቅድ ሰነድ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤
- ○ የዕቅድ ትግበራውን በየወቅቱ መከታተልና ድጋፍ የሚያስፈልገውም በወቅቱ ድጋፍ መስጠት፤

## VIII. በ2015 በጀት አመት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

### የነበሩ ጠንካራ ጎኖች

- ❖ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እና አጋር ድርጅቶች በመቀናጀት በጤና ዘርፉ የሚታዩትን ግብአቶች እንዲሟሉ ያላሰለሰ ጥረት ማካሄድ፤
- ❖ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን ከታችኛዉ መዋቅር ጋር በየጊዜው አስፈላጊ ውይይት በማካሄድ የጋራ አቅጣጫ እንዲያዝበት ማድረግ፡
- ❖ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ሌሎች የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የተቀናጀ ጥረት ማካሄድ፤
- ❖ ለጤና ተቋማት ግብኣት ለማሟላት እና የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት ማካሄድ፤
- ❖ በተለያዩ ፕሮግራሞች የሚሰሩ ባለሙያዎች ፕሮግራሙን ለማጠናከር ስልጠናዎችን መስጠት፤
- ❖ በአጠቃላይ ጥራት ያለውና ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ጥረት ማድረግ፤
- ❖ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ የጤና ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ፕሮፖዛሎችን በማዘጋት ፋይናንስ የማፈላለግና የተገኙትን ለየዘርፉ ማሰራጨት፤
- ❖ በሰው ሰራሽ ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ለሚያጋጥሙ የጤና ችግሮች መቀነስ የሚያስችሉ መሰረታዊ አቅርቦት ማቅረብ፤

### የታዩት ክፍተቶችና ተግዳሮቶች

- ➢ በተፈለገው ልክ በጤና ተቋማት የመድሃኒት ፍላጎትን ማሟላት አልተቻለም፤
  - ○ በነበረው አለም አቀፍ ችግርና አስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት የመድሀኒት እና የህክምና መሳሪያ አቅራቢዎች በተዋዋሉት ዋጋ በቶሎ አለማቅረብ፣
  - ○ በአንዳንድ ግብአቶች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ማሳየት፤

- የግዥ ሂደት መዘግየት እና ግብዓቶች በተፈለገው ጊዜ አለማቅረብ እና የመንግስት የግዥ ስርዓት ለመድሃኒት ምቹ አለመሆኑ፤

➢ የአገር ዉስጥ የመድሀኒት እና ህክምና መሳሪያ አምራቾች አቅርቦት አነስተኛ መሆኑና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ለጥሬ ዕቃ ባለ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና በተለያዩ ምክንያቶች መድሀኒቶችን አለማቅረብ፤

➢ በሀገራችን በተለያዩ ክፍሎች በተከሰተው ጦርነት ምክንያት፤

- ለድንገተኛ ህክምናው ያሉ ግብዓቶችና በጀቶች መዞራቸው የጤና ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ፤

➢ ሀኪሞችና የተለያዩ የጤና ባለሙያዎችን በዘርፉ በሚፈለገው መጠን ቀጥሮ አለማሰራት፤

- በሁሉም መዋቅሮች የበጀት ውስንነት መኖር፤ በርካታ ወደ ስራ ያልተሰማሩ ባለሙያዎች መኖር፤
- የባለሙያዎች ማበረታቻዎች አነስተኛ መሆንና በየተቋማቱ ወጥነት የጎደለዉ መሆኑ፤
- ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች የሰራተኞች ተነሳሽነት ላይ ጫና መፍጠሩ፤

➢ ለኮቪድ ወረርሽኝ በየደረጃው የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆንና የመከላከል መንገዶችን የመተግበርና ክትባትን በማህበረሰቡ የመውሰድ ሁኔታ አነስተኛ መሆኑ፤

➢ መረጃን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ የመያዝ ችግርና በሚፈለገው ፍጥነት አለማግኘት DHIS2 ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ባለመዋሉ አንዳንድ ሪፖርቶችን በአንዳንድ ዘርፎች ማውጣትና መጠቀም አለመቻል፤

➢ የግንባታ ግብዓቶች የገበያ ዋጋ ግሽበትና የሲሚንቶ እጥረት እና የሥራ ተቋራጮች የአቅም ውስንነት መኖር በፕሮጀክቶች ፍጥነት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፤

➢ በፋይናንስ ቢሮ እንዲፀድቅ የተጠየቀው በጀት በወቅቱ ፀድቆ አለመምጣት (መዘግየት) እንዲሁም ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶችና ከፋይናንስ ቢሮ በጀት በወቅቱ አለመለቀቅ፤

# IX. በ2016 በጀት አመት የታቀዱ ዒላማዎች፣ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

## 1. ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሻሻል፤

### 1.1 የስነ ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህጻናት፣ የህጻናት እና የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና

#### 1.1.1 የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

**ዒላማ**

- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መጠን ከ92% ወደ 95%(CAR) ማድረስ፤
- የድህረ ወሊድ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን ከ24% ወደ 30% ማድረስ፤
- የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን 27.8% ወደ 40% ማድረስ፤
- ምቹ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ከ44% ወደ 67% ማድረስ፤
- በአፍላ ወጣቶች የሚከሰተውን እርግዝና ከ13% ወደ 11% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በተለይ የድህረ ወሊድ አገልግለቱን ማጠናከር፤**
  - የቤተሰብ ዕቅድ የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች ለመተግበር በጤና ተቋማት ላይ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድና የተገኙትን ግኝቶች መተግበር፤
  - ቀድሞ የቤተሰብ እቅድ የጥራት ደረጃዎች በተተገበረባቸው የጤና ተቋማት አጠናክሮ መቀጠል፤
  - የቤተስብ እቅድ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ጤና ተቋማት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የማይሰጡ ጤና ጣቢያዎች እንዲሰጡ ማድረግ፤
  - ከፍተኛ የወሊድ አገልግሎት ካላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎችና እና ጤና ጣቢያዎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የድህረ-ወሊድ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ስልጠናና ግብአት በሟሟላት ስራ ማስጀመር፤
  - የቤተሰብ ዕቅድ አፈጻጸምን የተሻለ ለማድረግ በክልል እና ወረዳ ደረጃ World Contraception day ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎችን መስራት
  - በተለያዩ የመገናኛ ብዙኂን አማራጮችን ተጠቅሞ መልዕክት በማስተላለፍ የግንዛቤ መፍጠሪያ እና አዳዲስ የቤተሰብ እቅድ ተጠቃሚዎችን መፍጠር የሚያስችሉ ስራዎች መስራት፤
  - የቤተሰብ እቅድ ከመንግስት የሚመደበው በጀት ዝቅተኛ በመሆኑ ለክልሉ ም/ቤት፣ የፕሮግራሙ አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በበጀት አስፈላጊነት ላይ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ማዘጋጀት፤

- የ2030 እ.ኤ.አ የቤተሰብ ዕቅድ ቃልኪዳን ለማሳካት በበጀት አመቱ የቤተሰብ ዕቅድ ፍላጎት ግኸ ማዘዝ፣ ክትትል ማድረግ እና ፍላጎት ትንበያ መስራት፣
- የስነተዋልዶ ጤና ግብአቶች እና የፕሮግራም ማስፈፀሚያ በጀት በቋሚነት የማግኛ ስልት በመንደፍ ተገልጋዮችን መጨመር እና አገልግሎቱን ከሌሎች የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጋር የማቀናጀት ስራዎች መስራት፤
- በአጠቃላይ በቤተሰብ እቅድ ላይ ለባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት ጥራት ያለው የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ፣
- በዘርፉ ረጅም ጊዜ የሰሩ እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በመጠቀም የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት፤
- በDHIS2 የሚመጣውን መረጃ በመገምገም ወርሃዊ የቤተሰብ እቅድ አፈፃፀማቸው ከ60% በታች የሆኑ ወረዳዎችን በመለየት አፈፃጸማቸውን የተሻለ ለማድረግ በየወሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በወረዳዎች መካከል የሚታዩ የአገልግሎት ተደራሽነት መራራቅ ለማጥበብ ከባለድርሻ አካለት ጋር የውይይት መድረክ ማካሔድ፤
- ለቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የሚውሉ ሁሉም ግብአቶች በሁሉም ወረዳዎች በተገቢው መልኩ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ክትትል ማድረግ፤
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን ተደራሽነት ለማረጋገጥ በግልና በመንግስት ጤና ተቋማት መካከል ያለዉን የትብብርና የቅንጅታዊ ስራን መስራት፤
- Comprehensive የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ላይ ከጤና ተቋማት ለተወጣጡ ለ70 ባለሞያዎች ስልጠና መስጠት፤
- ድህረ ወሊድ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የአሰልጣኞች ስልጠና ከክልል ለተወጣጡ ለ12 ባለሙያዎች መስጠት፤
- አደድስ የእርግዝና መከላከያ ግብዓቶች ላይ በሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች ላይ የማስተዋወቅ ስራ መስራት፤
- በራስ አገዝ የሆነዉ በቆዳ ስር በመርፌ የሚሰጠዉን የእርግዝና መከላከያ አገልግሎት በሀዋሳ ከተማና መሰል ከተሞች አተገባበሩን መከታተል፣

- **ለድህረ ፅንስ ማቋረጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን ማሻሻልና ማስፋፋት፤**
  - ስለ ድህረ ፅንስ ማቋረጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን አፈፃፀምና ደረጃ የዳሰሳ ጥናት መስራት፣
  - ለድህረ ፅንስ ማቋረጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትና VCAT ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
  - በዳሰሳ ጥናት መሰረት ስለ ድህረ ፅንስ ማቋረጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ ወረዳዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
- **ያልተሟላ የቤተሰብ እቅድ ፍላጎትን ለመቀነስ ከPHCUs እና ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር ያለዉን ትስስርና ቅንጅት በማጠናከር የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ዘዴዎችን ስብጥርና ተጠቃሚነትን ማሻሻልና ማስፋፋት፤**
  - በደረጃ አራት የጤና ኤክስተንሽን ሰራተኞች የሉፕ አገልግሎት በጤና ኬላዎች ደረጃ የክትትል ሳጥን (Willows Box) ላይ 'smart start' model ጨምሮ ማስፋፋት፤
  - አፈጻጻማቸውን መገምገም እና የMentorship አገልግሎት ለሚሰጡ ለጤና ባለሙያዎች በአጠቃላይ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ላይ ስልጠና መስጠት፤

- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዝቅተኛ ሽፋን ያስመዘገቡ ወረዳዎች በመለየት ልዩ ድጋፍ በመስጠት አፈፃፀማቸውን ማሻሻል፤
- ወቅታዊ በቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ላይ የሚታዩትን አመለካከት ለመቀየር IEC/BCC መልእክት በሲዳምኛ ቋንቋ በማዘጋጀት ለወረዳዎችና ለጤና ተቋማት ማሰራጨት፤
- የቤተሰብ እቅድ ቅንጂታዊ አገልግሎት መመሪያ ላይ ለጤና አመራሮች በተመረጡ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት በወረዳ ደረጃ ኦረንቴሽን መስጠት፤
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች በቤተሰብ እቅድ ቅንጂታዊ አገልግሎት መመሪያ ላይ አቅማቸዉን መገንባት፤
- አገልግሎቱን እንዲሰጡ በተመረጡ ጤና ኬላዎች IUCD Kit ጨምሮ ሌሎች ግባቶችን ማሟላትና አገልግሎቱን ማስፋፋት፤

- **ከፍተኛ ተጽእኖ፣ የወጣቶች-ተኮር፣ የወጣቶች ፈተናና መጠነ ሰፊነትን መደገፍና ማመቻቸት፣ ውጤታማ እና ሰውን ማዕከል ያደረገ እንክብካቤ ለማሻሻል ወዳጃዊ እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ማጠናከር፤**
  - ምቹ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማስፋፋት፤
  - በክልል ደረጃ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ፎረም ማካሄድ፤
  - በተለያዩ የጤና ማእካላት፤ በኢንዱስት ፓርኮች እና በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ላይ ስልጠና መስጠት፤
  - በዩኒቨርሲቲ ክሊኒኮች የሚገኙትን ባለሙያዎች፤ በወጣቶች ማእከላት ዉስጥ በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ላይ ስልጠና መስጠት፤
  - በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ላይ ያተኮሩና በተለያዩ አካላት የሚተገበሩ ፕሮጅቶችን ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ፤
  - በመጀመሪያዎቹ የአፍላ ወጣትነት እድሜ ላይ ለሚገኙ ወጣቶች የሚሆን በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ምንጭ ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ማሰራጨት፤
  - የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና ፕሮግራምን በወረዳና በጤና ተቋማት ደረጃ ክትትል፤ ድጋፍና ግምገማ ማድረግ፤
  - የተሟላ የወሲብና የመራቢያ ጤና መረጃ፣ ምክርና አገልግሎት አሰጣጥ ንዝረት ማስፋትና ማጠናከር፤
  - መመሪያዎችን፤ የአገልግሎት ፓኬጆችን ማዘጋጀት፤

- **በጉርምስና ዕድሜ ላይ በሚገኙ ወጣቶች ዘንድ ጤናማ ባህሪ ማራመድ የሚያስችሉ ስራዎች (አመጋገብ፤ አካላዊ እንቅስቃሴ፤ የትምባሆ፤ የአልኮል ወይም የንጥረ ነገር አጠቃቀም) ማጠናከር፤**
  - የወጣቶችን ሞትና ጉዳት መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች መስራት፤
  - በህብረተሰቡ ስለ ወጣቶች ጤና እና አጋላጭ ሁኔታዎችን ላይ በቂ ግንዛቤ መፍጠር፤
  - የአፍላ ወጣትነት እርግዝና መጠን መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት፤
  - በወጣቶች የአደንዛዢ እጽ ተጠቃሚነት በመቀነስ የአዕምሮ ጤና ችግሮቻቸዉን መቀነስ፤
  - ከስርአተ ምግብ አለመመጣጠን በተለይም በአፍላ ወጣቶች የሚከሰተዉን የደም ማነስ ችግር እና በክብደታቸዉ መጨመር ምክንያት ለሚፈጠሩ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች እንዳይጋለጡ ማድረግ፤
  - የአዕምሮ ጤና ችግሮችን ቀድሞ በመለየትና በማከም አጠቃላይ የአዕምሮ ጤንነትን መጠበቅ፤

- ○ በጤና ተቋማት የሚሰጠዉን የምቹ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ማሳደግ፤

### 1.1.2 የእናቶች ጤና አገልግሎት

**ዒላማ**

- ➢ አራተኛውን እና ከዚያ በላይ የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ93% ወደ 95% ማድረስ፤
- ➢ በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጠውን የወሊድ አገልግሎት ከ82% ወደ 90% ማድረስ፤
- ➢ የድህረ ወሊድ ክትትል (በ7ቀናት ውስጥ) አገልግሎት 100% ላይ ማቆየት ፣
- ➢ ስምንት ጊዜ (contact -8) እና በላይ የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ11% ወደ 30% ማድረስ፤
- ➢ እናቶች በወለዱ በአንድ ደቂቃ ውስጥ uterotonics የተሰጣቸው እናቶች ሽፋንን ከ78% ወደ 90% ማድረስ፤
- ➢ በቀዶ ጥገና የሚወልዱ የእናቶች ቁጥር መጠንን ከ 5.1% ወደ 8% ማሳደግ፤
- ➢ የፍስቱላ ተጠርጣሪዎች ልዩታና ህክምና ቁጥር ከ30 ወደ 40 ማድረስ፤
- ➢ የማህጻን ዉልቃት የገጠማቸዉ እናቶች ልየታና ህክምና በቁጥር ከ394 ወደ 450 ማድረስ፤
- ➢ ሞተው የሚወለዱ ህፃናትን ከ1000 ከሚወለዱ ህፃናት መጠን ከ 4 ወደ 3 መቀነስ፤
- ➢ የእናቶች ሞት በተቋማትን በቁጥር ከ 34(27/100000) ወደ 25(21/100000) መቀነስ፤

### ስትራቴጂክ እርምጃና ዋና ዋና ተግባራት፤

- **ተደራሽና ጥራቱን የጠበቀ የቅድመ እርግዝና አገልግሎትን ማስጀመርና ማጠናከር፤**
  - ○ የቅድመ እርግዝና አገልግሎት መመሪያ የማስተዋዎቅ መድረክ ማካሄድ፤
  - ○ በቅድመ እርግዝና አገልግሎት ዙሪያ ኦሬንቴሽን መስጠትና ለአፈፃጸሙ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- **ጥራቱን የጠበቀ የቅድመ ወሊድ፤ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ተደራሽነቱን ማሻሻልና ማጎልበት፤**
  - ○ በእርግዝና ወሊድ እና ድህረ ወሊድ አገልግሎት ዙሪያ የተዘጋጁ መመሪያዎችን ፕሮቶኮሎችን የማስተዋዎቅ መድረክ ማካሄድ፤
  - ○ በተመረጡ ማሻሻያ ባደረጉ ጤና ኬላዎች (comprehensive health post) በእናቶች ጤና ፕሮግራም እና ጤና ኬላ ጤና ጣቢያ ትስስር ስራዎች ድጋፋዊ ጉብኝት ማድረግ፤
  - ○ ከጤና ተቋማት ለተወጣጡ ባለሙያዎች የፅንስ ክትትልና ህክምና በተዋረድ ስልጠና ለመስጠት ድጋፍ ማድረግ፤
  - ○ በተመረጡ አጥብያ መሰረት ያደረገ የክሊኒካል የማስተባበር ስራ የሚያከናወኑ ሆስፒታሎች ዳሰሳ ማካሄድ፤
  - ○ የክልሉ ጤናማ እናትነትን ወር ማክበር እና አፈፃፀሙን መገምገም፤
  - ○ በእናቶች ጤና ፕሮግራም ላይ (MPDSR) ያካተተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ማካሄድ፤
  - ○ በእናቶች ጤና ፕሮግራም አፈፃፀም ሩብ አመት ግምገማ ማካሄድ፤
  - ○ በእናቶች ጤና ፕሮግራም አዳዲስ አሰራሮች የተዋረድ ኦሬንቴንሽን መስጠት፤

- ከወሊድ በኋላ በከፍተኛ የደም መፍሰስ ምክንያት የሚከሰተውን የእናቶች ሞት ለመቀነስ የተዘጋጀውን ጥሪ ለትግበራ ክትትል እና ግምገማ ፍሬምዎረክ ለመተግበር እና የቴክኒክ ድጋፍ ለሁሉም ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ማድረግ፤

- **በጤና ተቋማት የእናቶች ጤና ግብዓቶችን ማሻሻል፤**
  - ለ2016 የእናቶች ጤና አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶችን ፍላጎት ትንበያ እና ክትትል በመስራት ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፤
  - በኤግዘምትድ አገልግሎት የሚወጡ ወጪዎችን እንዲመለሱ የወጣዉን የህግ ማዕቀፍ ወደ ታች ማዉረድና ተፈጻሚነቱን መደገፍና መከታተል፤
- **የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትን በጤና ተቋማት ማጠናከርና ማስፋፋት፤**
  - VCAT (Value clarification & attitude transformation) ስልጠና ለባለሙያዎችና ለአመራሮች መስጠት እና አስፈላጊ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - የአሰራርና የስልጠና ማንዋሎችን ማሰራጨት፤
  - ስራዎችን መገምገምና ግብረ መልስ መስጠት፤
- **ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ እና የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸው እናቶች ልየታ እና ህክምና አገልግሎቱን ማሻሻል፤**
  - በየጊዜው በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰሩ ተግባራት ጋር ልየታውን ለማቀናጀት የማስተባበር ስራዎች መስራት፤
  - በዘመቻ መልክ የሚሰሩ ህክምና ስራዎችን በየደረጃው የማስተባበር ስራዎችን መስራት፤
  - ቀጣይነት ያለው የፊስቱላ እና የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸው በተቀመጠው ስትራቴጂ መሰረት ለመከታተል አመቺ የሆነ የዳሰሳ ጥናት መስራት፤

### 1.1.3. የጨቅላ ሕፃናት እና የሕፃናት ጤና አገልግሎት ማሻሻል፤

**ዒላማ**

- የአተነፋፈስ ችግር አጋጥሟቸው በአምቡባግ እና ማስክ ሪሳሲቴት (resuscitated) ተደረገው የሚድኑ ጨቅላ ህጻናት ሽፋን ከ84% ወደ 87% ማድረስ፤
- በጨቅላ ሕጻናት ኢንፌክሽን በሽታ (NNS or VSD) ተይዘው የሚታከሙ ህጻናት ሽፋን ከ50% ወደ 65% ማድረስ፤
- በሳምባ ምች ታመው በፀረተዋህሲያን የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሽፋን ከ50% ወደ 70% ማድረስ፤
- በተቅማጥ ይጠቃሉ ተብለው ከሚታሰበው ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የህይወት አድን ህክምናን (ORS & Zinc or ORS) አገልግሎት ያገኙ ከ9% ወደ 15% ማድረስ፤
- በተቋማት የጨቅላ ህጻናት ሞት ምጣኔን ከ-4/1000 ወደ 3/1000-መቀነስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በጤና ተቋም የሚሰጠውን የጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት ጤና አገልግሎት ሽፋን እና ጥራት ማሻሻል፤**
  - በጨቅላ ህፃናት ጤና ዙሪያ እና የጤና አገልግሎት መሻት ዙሪያ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶችን ማድረግ፤
  - በክልል ስር ካሉ ጤና ተቋማት ለተወጣጡ ሚድዋይፎች በneonatal advanced life support (NALS) ስልጠና መስጠት፤

- በ EENC,NICU,NICU Device Mx በጤና ተቋም ለሚሰሩ ባለሙያዎች የክፍተት ማሟያ ስልጠናዎች መስጠት፤
- በጤና ተቋማት ለሚሰሩ ባለሙያዎች በካንጋሮ እናት እንክብካቤ አያያዝ (KMC), በክሎርሄክሲዲን አጠቃቀም እና Neonatal Resuscitation ዙሪያ የማነቃቅያ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- በተመረጡ ተቋማት የ NICU ሜንተርሽፕ ስራ ማስጀመር፤ ከ RMNCH ጋር አቀናጅቶ መስራት፤
- በተቋም ላይ በሚሰጡ አገልግሎቶች ዙሪያ የመስክ ድጋፋዊ ጉብኝት ማድረግ፤
- በተቋም ላይ በሚሰጡ አገልግሎቶች አተገባበር የፕሮግራም አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፤
- የ DHIS-2 የመረጃ ቋትን በመጠቀም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠት፤
- ለጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት ጤና አገልግሎቶች የሚውሉ የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦትን አግባባዊ አጠቃቀም ለማረጋጥ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- አዳዲስ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የጥናት ግኝቶችን ለውሳኔ መጠቀም፤

- **የመጀመሪያ/ቀዳማይ/ ልጅነት እድገት ማጠናከር እና ማስፋፋት፤**
  - በRMNCAH-N ፕሮግራሞች ዉስጥ ቀዳማይ ልጅነት እድገትን ማካተት፤
  - ወላጆችንና ማህበረሰቡን ያካተተ አሳታፊ እንክብካቤን በማህበረሰብ ደረጃ ማስፈን፤
- **ማህበረሰብ አቀፍ የጨቅላ ህፃናት እና ህፃናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፤**
  - የተከለሰዉን IMNCI በተዋረድ ስልጠና ለባለሙያዎች መስጠት፤
  - ዝቅተኛ የህጻናት ጤና አፈጻጸም ያላቸዉን ወረዳዎች መለየትና የPRCMM HP Open house ስልጠናዎችን መስጠት፤
  - ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸዉ ጤና ኬላዎችን መለየት እና ለባለሙያዎች በተከለሰዉ ICMNCI ላይ የክህሎት ስልጠና መስጠት፤
  - የህጻናት እና ጨቅላ ህጻናት ግብዓት ትንበያ እና ምጠና መስራት፤
  - ለሚዲያ ባለሙያዎች ዋና ዋና የጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ገዳይ በሽታዎች ላይ ኦረንቴሽን መስጠት፤
  - በዓመት ሁለት ግዜ ፕሮግራም ተኮር ድጋፍ እና ክትትል የአፈጸጸም ግምገማ ለሁሉም ወረዳዎች ማካሄድ፤

### 1.1.4. የክትባት አገልግሎት

**ዒላማ**

- የፔንታ ቫለንት ሶስት ክትባት ሽፋን በ100% ማስቀጠል፣
- የኩፍኝ 1 መከላከያ ክትባት ሽፋን በ100% ማስቀጠል፤
- የሮታ ቫይረስ ሁለት ክትባት ሽፋን በ100% ማስቀጠል፣
- ሁሉንም ዓይነት ክትባት ያገኙ ህፃናት ሽፋን በ100% ማስቀጠል፤
- የማህጸን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት 1 ሽፋን በ100% ላይ ማስቀጠል፤
- የኩፍኝ 2ኛው ዶዝ መከላከያ ክትባት ሽፋንን ከ93% ወደ 97% ማሳደግ፤
- የፔንታ ቫለንት 1 ከፔንታ ቫለንት ሶስት ማቋረጥ ከ2.7% ወደ 2% መቀነስ፤
- የኩፍኝ 1 ፔንታ ቫሌንት -1 መጠነ ማቋረጥ ከ7.4% ወደ 6% መቀነስ፤
- የኩፍኝ 1 የኩፍኝ 2 መጠነ ማቋረጥ ከ9.1% ወደ 8% መቀነስ፤
- ከመንጋጋ ቆልፍ በሽታ ተጠብቀዉ የተወለዱ ጨቅላ ህጻናት ሽፋን በ100% ማቆየት፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት፤

- **በክትባት ዙሪያ የህብረተሰብ ተኮር መልእክቶችን በመንደፍ፤ በማሰራጨት፤ ተሳትፎን በማሳደግ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለመጨመር እና የክትባት ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤**
  - በክልል ደረጃ በመደበኛ ክትባት ዙሪያ እና በዘመቻ ለሚሰጡ ክትባቶች የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ በቲቪ እና ሬድዮ መልዕክት ማስተላለፍ
  - በመደበኛ ክትባት፤ Covid 19 ክትባት ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የፓናል ውይይት ማካሄድ፤
  - የአፍሪካ የክትባት ሳምንትንና የፖሊዮ ቀንን ማክበር፤
  - በክትባት ዙሪያ አድቮኬሲ ስራዎችን መስራት፤
- **በክትባት የምንከላከላቸው በሽታዎችን ለመቆጣጠር በመደበኛው እና በዘመቻ መልክ የሚሰጡትን የክትባት አገልግሎቶችን ማጠናከር፤**
  - ዝቅተኛ የክትባት አፈፃፀም ያላቸውን ወረዳዎች በመለየት ለሁሉም ያልተከተቡ ህጻናት ክትባት እንዲሰጥ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
  - በትምህርት ቤት፣ በጤና ተቋምና በጊዜያዊ የክትባት መስጫ ጣቢያዎች በ2 ዙር የሚሰጠውን የማህጸን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት ማካሄድ፤
  - የክትባት አገልግሎትን በሁለተኛው እድሜ ወለል ላይ (2YL) ከሌሎች የእናቶች እና ህፃናት አገልግሎት ጋር በቅንጅት እንዲሰጥ ማድረግ፤
  - ለወረዳ ለጤና ተቋማት የሚሰጡ የክትባት ሥልጠናዎችን ጥራት መከታተል እና ድጋፍ ማድረግ፤
  - በአመት ሁለት ግዜ በክትባት አገልግሎት ላይ ድጋፍ፤ ክትትል እና ግምገማ ማካሄድ፤
  - በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚተላፈዉ ፕሮግራም መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶችን በዘመቻ መልክ (ፖሊዮ፤ኩፍኝ፤ የመሳሰሉትን) ማካሄድ፤
- **አዳዲስ ክትባቶችን በመደበኛ የክትባት መርኃ ግብር የማስጀመር እና ያሉትንም ክትባቶች ጥቅም ላይ የመዋል ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የኩፍኝ ሁለተኛው ዶዝ እና የሰርቫይካል ካንሰር መከላከያ ክትባት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክትባት የኅንዮሽ ጉዳት አስተዳደር ስርዓትን መስራት፤
  - በክትባት ፕሮግራም ስራ ሂደት ላይ መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ መስጠት፤
- **ለክትባት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብአቶች ለማሟላት የሚያስችሉ ስራዎች፤ የቅዝቃዜ ሰንሰለትን አጠባበቅ፤ አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓትን ማጠናከር፤**
  - የ2016 በጀት ዓመት የክትባት ግብአቶችን ትንበያ መስራት፣ ስርጭቱንና አጠቃቀሙን መከታተል፤
  - ዓመታዊ የክትባት ግብዓት መጠይቅ ማዘጋጀትና መላክ፤
  - በክትባት ዘመቻ ፕሮግራም ወቅት የCOVID-19 ስርጭት ለመከላከል የሚያስፈልጉ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛዎችን ማሰራጨት፤
  - በክትባት ዘመቻ ፕሮግራም ወቅት ወደ ተቋም ተሰራጭተዉ ከአገልግሎት የተረፉ የክትባት ግብዓቶችን አግባባዊ የክምችት ሂደትን ጠብቆ በማሰባሰብ በድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ መከታተልና መደገፍ፤
  - ለክትባት ፕሮግራም የሚስፈልጉ የታተሙ ህትመቶች ማሰራጨት፤

- በ2016 በጀት ዓመት የቅዝቃዜ ሰንሰለት መሳሪያዎች ቆጠራ በማካሄድ በዳታቤዝ እንዲገባ ማድረግ፤
- የጥገና መለዋወጫ እቃዎችን ጥያቄ ማቅረብ፤ የስርጭት መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ እንዲሰራጩ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መከታተል፤

- **የCovid 19 መከላከያ ክትባት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል በዘመቻ እና በመደበኛ እንዲሰጥ ማድረግ፤**
  - የCovid 19 መከላከያ ክትባትን በቋሚነት እና በዘመቻ መልክ ማካሄድ፤
  - ጥራቱን የጠበቀ የኮቪድ 19 ክትባት ግብዓት ትንበያ፤ ስርጭት እና ክትትል ስራ መስራት፤
  - የኮቪድ 19 ክትባት መረጃ ስርዓትን በሁሉም ወረዳዎች ማስፋፋት፤
  - ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የኮቪድ 19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት አስተዳደር ስርዓትን መስራት፤

## 1.2 የሥርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ

**ዒላማ**

- በየወሩ የእድገት ክትትልና ማበልጸግ የሚደረግላቸው እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን ከ88% ወደ 90% ማሳደግ፣
- በጤና ተቋም ከተወለዱ ህጻናት ውስጥ ክብደታቸው ከ2500 ግራም በታች የሆኑ ህፃናት ከ1.34% ወደ 1% ዝቅ ማድረግ፤
- የቫይታሚን ኤ ካፕሱል ሁለት ጊዜ ያገኙ እድሜያቸው ከ6-59 ወራት የሆኑ ህፃናት ሽፋን 75% ወደ 85% ማሳደግ፣
- በአመት ሁለት ጊዜ የፀረ አንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና እንክብል የወሰዱ እድሜያቸው ከ24-59 ወራት ያሉ ህጻናት ሽፋን ከ72% ወደ 85% ማድረስ፣
- ከ90 በላይ የደም ማነስ መከላከያ የአይረን ፎሌት ኪኒን የወሰዱ ነፍሰጡር እናቶች ሽፋን ከ 84% ወደ 100% ማሳደግ፤
- ከእርግዝና 12 ሳምንታት በኂላ የአንጅት ጥገኛ ትላትል ህክምና ክኒን እደላ ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ሽፋን ከ84% ወደ 90% ማድረስ፤
- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች ሽፋን ከ75% ወደ 85% ማሳደግ፤
- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ ወጣቶች ሽፋን ከ2% ወደ 10% ማሳደግ፤
- የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን ከ66% ወደ 88% ማሳደግ፤
- በከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን ችግር ታክመው የዳኑ ህፃናት ሽፋን (SAM cure rate) 85% ወደ 95% ማሳደግ፤
- መካከለኛ የምግብ አለመመጣጠን ችግር ታክመው የዳኑ ህፃናት ሽፋን (MAM cure rate) 80% ወደ 85% ማሳደግ፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **ለአፍላ ወጣቶች፣ እናቶች፣ ጨቅላ እና ታዳጊ ህፃናት ሥርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማሻሻል የሚስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የሥርዓተ-ምግብ፣ የጥቃቅን ንጥረ-ምግቦች የትግበራ መመሪያ፣ ስልጠና ማኑዋል ማስታዋወቅ፤
    - የትምህርት መርጃ እና ፈጣን ማጣቀሻ ፅሑፎች ማኑዋል፣ማስታዋወቅ ማሰራጨት
    - አመጋገብን ለማሻሻል የሚያግዙ መልዕክቶችን ማሰራጨት፤
    - በሥርዓተ-ምግብ ለባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እና በተዋረድ እንዲሰጥ የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
    - የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት ለማጠናከር የተቀናጀ ድጋፋዊ ጉብኝት እና የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፣
    - የወጣቶች እና አፍላ ወጣቶች ሳምንታዊ የአይረንፎሊክአሲድ እንክብል እደላ በስፋት ለማስቀጠል የውይይት መድረክ መፍጠር እና የቀጣይ እቅድ ማዘጋጀት፣
    - የሥርዓተ-ምግብ መልዕክቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የሞባይል መተግበሪያ (Mobile-app) በመክፈት መረጃዎችን ማሰረጨት፣
    - በሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት ላይ መልካም ተሞክሮ ካላቸው የተመረጡ ወረዳዎችና ጤና ተቋማት ጋር በተገኘው መልካም ተሞክሮ መሰረት ወደ ለሎች ወረዳዎች ማስፋት፤
    - የአለም ጡት ማጥባት ሳምንትን በተለያዩ ዝግጅቶች በደመቀ ሁኔታ ማክበር፤
    - ጤና ተቋማትን ለጡት ማጥባት ምቹ ለማድረግ በሁሉም ወረዳዎች ለሚገኙ ሆስፒታሎች የሚሰሩ ባለሙዎች ለማሰልጠን የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
    - ሁሉም ጤና ተቋማት የእድገት ክትትል እና ማበልፀግ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ልዩ ክፍል ለማዘጋጀት ጥረት ማድረግ፤
    - የሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት እቅድ፣ ድጋፋዊ ጉብኝት እና የአፈፃፀም ግምገማ እንዲካሄድ ለሁሉም ወረዳዎች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
    - የተዘጋጀውን የአጥቢያ ዙሪያ የሥርዓተ-ምግብ ሜኒተርሽፐ ትግበራ መመሪያ መሰረት ስልጠና መስጠት፤
- **ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች አሰጣጥን ማጠናከር፣**
    - ሥርዓተ-ምግብ ለተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከል እና ህክምና ክልላዊ ሰነዶች እንዲካተት በቅንጅት መስራት፣
    - የሚሰጡ ስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶችን በቅንጅት ለመስጠት የጋራ እቅድ ማዘጋጀት፣
    - የተላላፊ በሽታዎች እና ሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት ዝርዝር ደረጃ ማዘጋጀት እና ማጋራት፣
    - የሥርዓተ-ምግብ ልየታ እና ምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ያላሰለሰ ጥረት ማካሄድ፤
    - ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና ሥርዓተ-ምግብ አገልግሎት አሰጣጥን ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
    - የሥርዓተ-ምግብ ልየታ እና ምክር አገልግሎት ግብዓቶችን ማሟላት (ሚዛን፣ የላይኛው ክንድ እኩሌታ ሜትር፣ የቁመት መለኪያ፣ የትምህርት መርጃ ፅሑፎች)፣

- ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ህክምና የምግብ መመሪያ(ሜኑ) የተዘጋጀዉን ማሰራጨት፣

- **የምግብና ስርዓተ-ምግብ ስትራቴጂውን አፈፃፀም ለማሻሻል የዘርፈ ብዙ ቅንጅታዊ አሰራሩን ማጠናከር፤**
  - የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ማካሄድ፤
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ትግበራ መመሪያውን ማስተዋወቅና ወደ ትግበራ ማስገባት፤
  - ለከፍተኛ አመራሩ Advocacy መድረክ ማዘጋጀት፤.
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ቴክኒካል ኮሚቴ እና ስቲሪንግ ኮሚቴ TOR ማስፈረም፤
  - በመደበኛነት የምግብና ስርዓተ-ምግብ ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባ ማካሄድ፤
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ስቲሪንግ ተክኒካል ኮሚቴ መከታተል፤
  - ለምግብና ስርዓተ-ምግብ ስትራቴጅዉ ትግበራ የተመደበውን የሀብት መጠን መሰብሰብ፤ መተንተን እና መጠቀም፤
  - በበጀት የተደገፈ የዘርፈ ብዙ ምግብና ስርዓተ-ምግብ የጋራ እቅድ በክልልና በወረዳ ደረጃ ማዘጋጀት፤
  - የተቀናጀ የዘርፈ ብዙ የምግብና ስርዓተ-ምግብ ድጋፋዊ ጉብኝት ማካሄድ፤
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ስትራቴጅ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ፤
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ትግበራውን ለማጠናከር የአድቮከሲ ቱል ማዘጋጀት፤
  - የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ቅንጅታዊ አሰራሩን ለማጠናከር በክልል ደረጃ ድጋፍ የሚያደርጉ ቴክኒካል ባለሙያዎች እንዲቀጠሩ ማድረግ፤
  - የስርዓተ-ምግብ ትግበራዉን የሚያግዝ የሰው ሃይል እና አግባብነት ያለዉ አደረጃጀት እንዲፈጠር የግንዛቤ መድረክ ማዘጋጀት፤
  - የዘርፈ-ብዙ ምግብና ስርዓተ-ምግብ አፈጻጸም መመሪያ እና መከታተያ ስኮር ካርድ ስልጠና መስጠት፤
  - ሴክተሮች በዘርፈ-ብዙ ምግብና ስርዓተ-ምግብ እሰኮር ካርድ መለኪያ መሰረት ሪፖርት እንዲያደርጉ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
  - ሪፖርት መተንተን፤ መጠቀም እና ግብረ መልስ መስጠት፤

- **የአጣዳፊ የምግብ አለመመጣጠን መከላከልና ህክምና አገልግሎትን ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - ከአምስት ዓመት በታች ላሉ ህጻናትና ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የሥርዓተ-ምግብ ልየታ በየወሩ እንዲሰራ የገንዘብና የቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ፤
  - በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች እናቶችና አሳዳጊዎችን በመጠቀም የ Family MUAC ሙከራ ደረጃን በመስክ በመገኘት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

- **በመካከለኛ እና ከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፤**
  - በሁሉም ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች የከፍተኛ ምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተኝቶ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ተቋማትን መለየት፣ በመተንተን፣ አገልግሎት እንዲጀምሩ እቅድ ማዘጋጀትና ለትግበራው ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

- ተኝተው ለሚታከሙ ህጻናት የሚንከባከኩ እናቶች ወይም አሳዳጊዎች በጤና ተቋም ቆይታቸው ምግብ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በተዘጋጀዉ መመሪያዉን መሰረት ወደ ስራ ማስገባት፤
- የስርዓተ ምግብ አገልግሎቶች በተቀናጀና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚሰጥ አንድ የልህቀት ማዕከል (Center of Excellence) የሆኑ ሁለት የጤና ተቋም ማደራጀትና ማቋቋም፤
- መካከለኛ እና ከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በመለየት ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግና አስፈላጊውን የሪፈራል ስርዓት እንዲጠናከር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- በሁሉም ወረዳዎችና ተቋማት የአስተኝቶ ህክምና አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የpschosocial stimulation ቦታና ቁሳቁሶችን እንዲኖራቸዉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

- **በሰው ሰራሽ እና ድንገተኛ አደጋዎች ምክንያት የሚከሰት የሥርዓተ-ምግብ አለመመጣጠን ምላሽና ህክምና አገልግሎትን ማጠናከር፤**
  - የድንገተኛ አደጋዎች በሚከሰቱባቸው አካባቢዎች የአጣዳፊ የምግብ አለመመጣጠን ህክምናን ለመስጠት የሚውል የጸደቀ መመሪያን (Simplified and combined approach) ሙከራውን በተቀመጡ ወረዳዎች ማስጀመር፤
  - የውስጥ ተፈናቃዮች የህብረተሰብ ክፍሎች የስርዓተ ምግብ ልየታና ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤
- **በመካከለኛ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ህክምና በመደበኛ የሥርዓተ-ምግብ ጤና አገልግሎት ተካቶ እንዲተገበር ማስቻል፤**
  - በመካከለኛ ደረጃ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ ህጻናትና እናቶች በመደበኛ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አካቶ መሰራት፤
  - አጣዳፊ ከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን ህክምና መመሪያ ላይ በተሰጠው ስልጠና ላይ የድህረ ስልጠና የመስክ ዳሰሳና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
  - በከፍተኛና በመካከለኛ የአጣዳፊ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ እናቶችና ህጻናትን የስርዓተ-ምግብ ልየታና ህክምና በተመለከተ የተለያዩ መረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ መተንተንና ለወረዳዎች ግብረ-መልስ መስጠት፤
  - የ"Simplified and combined approach" ጥናቶችን ላይ መሳተፍና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶችን ለውሳኔ መጠቀም፤

## የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ

**ዒላማ**

- በዘርፈ ብዙ በስኮር ካርድ ሪፖርት የሚያደርጉ ወረዳዎችን ቁጥር ከ10 ወደ 18 ማሳደግ፤
- የማሕበረሰብ ሰርቶ ማሳያ እና መማማሪያ (Community Lab) ከ2 ወደ 10 ወረዳዎች ማሳደግ፤
- የሰቆጣ ቃልኪዳን የUNISE ሌሎች የመረጃ ቴክኖሎጂ ከ2 ወደ 10 ወረዳዎች ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **ምግብና ስርዓተ-ምግብ ስትራቴጅውን እና የሰቆጣ ቃልኪዳን የማስፋፋት ምዕራፍ ትግበራ አፈፃፀም ለማሻሻል የዘርፈ ብዙ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፤**
  - የምግብ ስርዓትና ስርዓተ-ምግብ ምክር ቤት በ10 ሰቆጣ ወረዳዎች ማጠናከር እና በቀሪ ወረዳዎች ባሉት ማቋቋሚያ ደንብ ዝግጅት ማጠናቀቅ፤ ለውሳኔ ማቅረብ እና ማፀደቅ ሥራዎች ላይ ድጋፍ መስጠት፤
  - በክልል ደረጃ ለከፍተኛ አመራሩ በምግብና ስርዓተ-ምግብ እና ሰቆጣ ድክላረሽን ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ (ሪቪታላዜሽን) ማካሄድ፣
  - የምግብና ስርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ለማቋቋም በክልል፣ በገጠር ወረዳዎች እና በ6 ከተማ አሰተዳሮች ባለሙያዎችን መቅጠር፤
  - የዘርፈ ብዙ ምግብ-ሥርዓትና ሥርዓተ-ምግብ ትስስር እና ቅንጅት ማጠናከር ፕሮጀክት በክልል ደረጃ በሚዘጋጅ መድረክ ይፋ ማድረግ፤
  - የምግብ ስርዓትና ስርዓተ-ምግብ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ማካሄድ፤
  - ለክልልና ወረዳዎች ከፍተኛ አመራሮች በዘርፈ ብዙ ምግብ ስርዓትና ስርዓተ-ምግብ ትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር ላይ የመማማሪያ ጉዞ ማዘጋጀት (learning journey)፤
  - ጨውን በአዮዲን (ፖታሼም አዮዴት) የማበልፀግ ስራ ላይ ለተሰማሩ የጨው ማቀነባባሪያ ፋብሪካዎች በየወሩ ሪፖርት ማሰባሰብ እና ወርሃዊ ድርሻቸውን ማሰራጨት፣
- **የምግብና ሥርዓተ-ምግብ መዋቅራዊ አደረጃጃት እና ማስተባባሪያ ጽ/ቤቶች በሁሉም ፈጻሚ የክልል እና ወረዳ ሴክተሮች ማጠናከር፤**
  - በአዲስ መልክ የተቋቋመውን የሥርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ለክልልና ለሁሉም ወረዳዎች ማስተዋወቅ እና በተዋረድ በሁሉም ደረጃ ተመሳሳይ መዋቅር እንዲፈጠር የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣
  - የማህበረሰብ መማማሪያ እና ሰርቶ ማሳያ በሁሉም ወረዳዎች ላይ መመስረት፤
- **ምግብና ስርዓተ-ምግብ ስትራቴጅውን እና የሰቆጣ ቃልኪዳን የማስፋፋት ምዕራፍ ትግበራ አፈፃፀም ለማሻሻል የዘርፈ ብዙ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፤**
  - የሀብት ማሰባሰብ እቅድ (Resource mobilization plan) እንዲጠናቀቅ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
  - የግል ባለሀብት እና ለጋሽ ድርጅቶች የሀብት ማሰባሰብ መድረክ ማዘጋጀት፤
  - የምግብ እና ሥርዓተ-ምግብ ክላስተር ስብሰባ ማካሄድ፤
  - አዳዲስ አጋሮችን መለየት እና ትስስር መፍጠር፤
  - በዘርፈ ብዙ ቅንጅታዊ አሰራር የመቀንጨር ቅነሳ ፕሮጀክት(Multisectoral Approach for Stunting Reduction Project) ትግበራ ማጠናከር፤
  - ወደ ስራ ያልገቡ ፕሮጀክቶች የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ላይ ክትትልና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ (የዲዛይንና ጥናት መገምገም፣ የጨረታ ሰነድ መገምገም፣ ክፍያ እንዲተላለፍ መከታተል፤
  - በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ንዑስ-ፕሮጀክቶችን እንዲጠናቀቁ በመስክ ደረጃ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
  - ወደ ተግባር ለገቡ ንዑስ ፕሮጀክቶች በወቅቱ ክፍያ እንዲተላለፍ ድጋፍ ማድረግ፤

- **የማህበረሰብ ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችል የተግባቦት ስራን ማጠናከር፤**
    - ለአፍላ ወጣቶች፣ እናቶች፣ ጨቅላ እና ታዳጊ ህፃናት የሥርዓተ-ምግብ ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችል የተግባቦት ስራን ማሻሻል፤
    - የተለያዩ ሚድያ አካላትን በመጠቀም በታዳጊ ህጻናት ስርዓተ ምግብ ዙሪያ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤
    - የወጣቶች እና አፍላ ወጣቶች አመጋገብ ለማሻሻል መልዕክቶችን በማዘጋጀት በማህበራዊ ሚዲያ እና ሌሎች አማራጮች ማሰራጨት፣
    - የመጀመሪያዎቹ 1000 ቀናት ባሻገር የማህበረሰብ ባህሪ ለውጥ ተግባቦት መመሪያን ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፤
- **የሥርዓተ-ምግብ አቅርቦቶች (Nutrition Supplies) ትንበያ፤ ግዥ፤ ክምችት፤ ስርጭትን እና ተጠቃሚነትን ማጠናከር፤**
    - ለSC እና OTP የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በአጋር አካላት አቅራቢነት ለወረዳዎች መሰራጨታቸውን በሚመለከት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
    - የስርዓተ ምግብ ግብዓቶች ትንበያ ክለሳ ማድረግ፣ በትንበያው መሰረት የአመቱን የግብዓት ፍላጎት ልየታ ማከናወን፣ ግዥ ማስጀመርና የግዥ ሂደቱ ላይ ክትትል ማድረግ፤
    - የስርዓተ ምግብ የግብዓት አስተዳደር ወደ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት እንዲሸጋገር አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ከባለድርሸ አካላት ጋር መስራት፤
    - የስርዓተ ምግብ ግብዓቶች ወደ መሰረታዊ የመድኃኒቶች ዝርዝር (Essential Medicine List) ውስጥ እንዲካተት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራትና አፈጻጸሙን በቅርበት መከታተል፤
    - የስርዓተ ምግብ ግብዓቶች አግባባዊ አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን መስራት፣ የሚስተዋሉ አግባባዊ ያልሆኑ አጠቃቀሞችን (mis-use) ለማስተካከል ከሚመለከታቸው የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤መምራትና ማስተባበር፤
    - የስርዓተ ምግብ ግብዓቶች ለህብረተሰቡ ያለ ክፍያ የሚቀርቡበትን አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማመቻቸት፤
    - ለመከላከል ተኮር የስርዓተ ምግብ ፕሮግራም የሚውሉ ግብዓቶች ግዢና ስርጭት መከታተል፤
    - የቫይታሚ ኤ ካፕሱል አቅርቦቱን በቋሚነትና ሳይቆራረጥ ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ከሚመላከታቸው ጋር ምክክር ማድረግ፤
- **የስርአተ ምግብ መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥን እና ፈጠራዎችን ማሻሸል፤**
    - የብዝሃ ሴክተር እና ሰቆጣ ቃል ኪዳን ድጋፍ፤ ክትትል፤ ግምገማ፤ ተጠያቂነት እና መማማሪያ ስርዓትን ማጠናከር፤
    - የሩብ፤ የግማሽና አመታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት የአፈፃፀም ግምገማ (Performance review meeting) ማካሄድ፤
    - የብዝሃ ሴክተር እና ሰቆጣ ቃልኪዳን የከፍተኛ አመራሩ(ኢንተር ሚኒስቴሪያል) አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፤
    - አመታዊ የብዝሃ ሴክተር ምግብና ስርዓተ-ምግብ እና ሰቆጣ ቃል ኪዳን ግምገማ ማካሄድ፤
    - የብዝሃ ሴክተር፣ ሰቆጣ እና ምግብና ስርዓተ-ምግብ ተኮር ድጋፋዊ ጉብኝት እና የመረጃ ጥራት ማካሄድ፤
    - ዩኒስ በተጀመረባቸው የሰቆጣ ቃል ኪዳን የማስፋፋት ወረዳዎች በ የዩኒስ መረጃ ተንትኖ እንዲጠቀሙ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
    - የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፤

## 1.3 የበሽታ መከላከልእና ቁጥጥር ማሻሻል

### 1.3.1 ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቁጥኝና ሄፓታይተስ ከመከላከልና መቆጣጠር

*1.3.1.1 ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ጽንስ /ልጅ/ እንዳይተላለፍ መከላከል፤*

**ዒላማ**

- የነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አገልግሎት ሽፋን ከ100% በላይ የሆነዉን በዚያዉ በ100% ላይ ማስቀጠል፤
- የኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የሚገኝባቸው ነፍሰጡር፣ ወላድ እና የሚያጠቡ እናቶች የጸረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎት ሽፋን ከ24%(192) ወደ 93%(726) ማድረስ፤
- ኤች አይ ቪ ካለባቸው እናቶች ለተወለዱ ሕፃናት የቅድመ መከላከል (Dual prophylaxis) ህክምና ሽፋን ከ24%(164) ወደ 78%(624) ማድረስ፤
- ኤች አይ ቪ ካለባቸው እናቶች ለተወለዱ ሕፃናት (CPT prophylaxis) ህክምና ሽፋን ከ18%(144) ወደ 81%(647) ማድረስ፤
- ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ ነፍሰ-ጡር እናቶች የሚወለዱ ህጻናት ከተወለዱ እስከ 12 ወራት ውስጥ የሚከናውነውን የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ (Virological test) ሽፋን ከ 33%(198) ወደ 85%(679) ማሳደግ፣
- በቅድመ ወሊድ ክትትል የቂጥኝ (Syphilis) ምርመራ የተደረገላቸው እናቶች ሽፋን ከ81% ወደ 83% ማድረስ፤
- ለነፍሰጡር እናቶች የጉበት በሽታ (HBV) ምርመራ አገልግሎት ሽፋን ከ59%(42618) ወደ 62% (99,702) ማድረስ፤

### ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **የነፍሰ ጡር እናቶች የኤች አይ ቪ፤ ቂጥኝ እና ሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ ምርመራን ማጠናከር፤**
    - የኤች አይ ቪ፣ የቂጥኝ እና የጉበት ቫይረስ/HBV/ ምርመራ ሽፋንን ለነፍሰ ጡር እና ጡት ለሚያጠቡ እናቶች ለመስጠት አዉደ ጥናት ማካሄድ፤
    - ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ እናቶች የኤች አይ ቪ እና የቂጥኝ ምርመራ ሽፋንን ለማሳደግ የጥምር (dual) የኤች አይ ቪ እና የቂጥኝ ምርመራ የማስተዋወቂያ መድረክ ማካሄድ፤
    - ለሚዲያ ባለሙያዎች ስለ PMTCT የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት፤
    - የኤች አይ ቪ፤ የቂጥኝ እና የጉበት ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ የሬድዮ/ቲቪ መልእክት ማሰተላለፍ፤
    - ለአመራሮችና ለባለደርሻ አካላት ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ፕሮግርራም ትኩረት እንዲሰጡ የAdvocacy Visit work shop ማካሄድ፤
    - የPMTCT ግብአትን የየወሩን stock status በመከታተል ለዞኖችና ወረዳዎች የማሳወቅና የመከታተል ስራ መስራት፤
    - በተከለሰው የPMTCT training ማሰልጠኛ ማንዋል መሰረት የcomprehensive PMTCT የአስልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
- **ቂጥኝ እና ሄፓታይተስ ቢ. መከላከያ ህክምና መስጠትን /Prophylaxis/ እንዲሁም የነፍሰ ጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የኤች አይ ቪ ህክምናን ማሻሻል፤**
    - PMTCT አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ማስፋፋት፤
    - የPMTCT mentorship ለማጠናከር ለጤና ባለ ሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤

- የመረጃ ጥራትን ለማሻሻል የPMTCT cohort ክትትል ላይ ማብራሪያ/ orientation መስጠት፤
- የ MSG ፕሮግራምን ለማጠናከር ከክልል የPMTCT አስተባባሪዎች እና የተመረጡት MSG ጋር አውደ ጥናት ማካሄድ፤
- የኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ አገልግሎት ለማጠናከር ዝቅተኛ አፈፃፀም ያለባቸው ወረዳዎችና የመረጃ ጥራት ችግሮች ባሉባቸው ጤና ተቋማት የተቀናጀ ድጋፋዊ ጉብኝት ማካሄድ፤
- ከስትራቴጂክ ጉዳዮች ጋር በመተባበር የመረጃ ጥራት ማሻሻያ አውደ ጥናት ማካሄድ፤
- የ2015 የPMTCT አመታዊ አፈፀፃም ግምገማ እና የ2016 እቅድ ማስማማት መድረክ ማዘጋጀት፤
- በግማሽ አመት የPMTCT ፕሮግራሞችን አፈጻጸም መገምገም፤
- የወረዳዎችን የ PMTCT አፈፃፀም በዳሽ ቦርድን ትግበራዉን ማከናወን፤
- የወረዳዎችን የ PMTCT አፈፃፀም በዳሽ ቦርድን በመጠቀም ትንተና በመስራት ለወረዳዎች መላክ፤
- ወቅታዊ የ PMTCT አፈፃፀም ለማሻሻል (CQI) በሁሉም ወረዳዎች በቀጣይነት ተግባረዊ እንዲሆን ክትትል እና ድጋፍ ማጠናከር፤
- ኤችአይ ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ነፍሰጡርና ለሚያጠቡ እናቶች የቫይራል ሎድ ምርመራ ለማጠናከር POC VL የሚሰሩ ጤና ተቋማትን ማስፋፋት፤
- ኤችአይ ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ነፍሰጡርና ለሚያጠቡ እናቶች የቫይራል ሎድ ምርመራ ለማጠናከር POC VL የተጀመረባቸው ጤና ተቋማትን መከታተልና መደገፍ፤
- ኤችአይ ቪ. በደማቸው የተገኘባቸው ነፍሰጡርና ለሚያጠቡ እናቶች የቫይራል ሎድ ምርመራ ወቅቱን ጠብቆ መሰራቱን መከታተል፤
- ከ PMTCT ክትትል የጠፉ ኤችአይ ቪ. በደማቸው ያለባቸው ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች በተመለከተ ጥናት ማጠናቀቅ (PMTCT Lost to follow up study) ፤

- **የኤች አይ ቪ. ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን ምርመራ እና የመከላከል ህክምና (Prophilaxis) የመስጠት ስራ ማጠናከር፤**
  - ከኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከአጋሮች ጋር በመተባበር GeneXpert ማሽንን በመጠቀም የ POC EID አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ማስፋፋት እና ያሉትን ተቋማት አገልግሎታቸውን ማጠናከር፤GeneXpert ማሽንን በመጠቀም የEID አገልግሎት የሚሰጡ የPOC EID ተቋማት ለጤና ባለሙያዎች የተሀድሶ ስልጠና መስጠት፤
  - ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የEID ማሻሻያ እቅድ አፈጻጸምን ለመከታተል የስራ ግምገማ ማካሄድ፤
  - በተመረጡ POC EID ጣቢያዎች ከአጋሮች ጋር የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ጋር በመቀናጀት ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የPMTCT refreshment (IRT) ስልጠና መስጠት፤ኤች አይ ቪ. በደማቸው ከሚገኝ እናቶች ለተወለዱ ህፃናት በሚደረገው የምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ውጤት ላላቸው ህጻናት የማጣራት(HIV positive infant audit) ስራ መስራት፤
  - የመረጃ ጥራት ለማሻሻል ለHMIS focal እና የPMTCT አስተባባሪዎች አመላካቾች (PMTCT indicators) የተሃድሶ ስልጠና (refresher training) እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - የ MSG ፕሮግራም የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ማስፋፋት፤

- የPMTCT **ምርመራ እና ህክምና ግብዓቶች አቅርቦትን ማጠናከር፤**
    - የኤች አይ ቪ፣ የሄፓታይተስ እና የቂጥኝ መመርመሪያ ኪት አቅርቦት ማረጋገጥና ስርጭቱን መከታተል፤
    - ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚገኝ እናቶች ለተወለዱ ህፃናት Prophylaxis እና ምርመራ ለማሻሻል የእናቶች ለእናቶች ቡድን (MSG) ማጠናከር፤

### 1.3.1.2 ከእርግዝና ውጭ ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠር፤

**ዒላማ**

- የመጀመሪያ 95 ለማሳካት ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ይኖራል ተብሎ ከሚጠበቁ አዋቂዎችና ህጻናት ውስጥ ተመርምረው ውጤታቸውን ያላወቁ **6,077** ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸውን አዲስ ሰዎች በማግኘት የመጀመሪያውን 95 ከ51% (11477/22362*100) ወደ 72% (17,553/24,306*100) ማድረስ፤
- የመጀመሪያ 95 ለማሳካት ኤች አይቪ በደማቸው ይኖራል ተብሎ ከሚጠበቁ ህጻናት ተመርምረው ውጤታቸውን ያላወቁ **621** ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸውን አዲስ ህጻናት በማግኘት የመጀመሪያው 95 ከ14% (348/2484*100) ወደ 39% (969/2484*100) ማድረስ፤
- ሁለተኛውን 95 ለማሳካት ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው አዋቂዎችና ህጻናት የፀረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎትን ሽፋኑን ከ59%(10359/17553*100) ወደ 92%(16,132/17553*100) ማሳደግ፤
- ሁለተኛውን 95 ለማሳካት ተመርምረው ቫይረሱ በደማቸው መኖሩን ካወቁ ህፃናት (320) የፀረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎትን ከ 33% (320/969*100) ወደ 60% (920/1534*100)ማሳደግ፤
- የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት ከሚወስዱ አዋቂዎችና ሕፃናት ውስጥ **90%** (15,008) የሚሆኑት የቫይረስ መጠን ልኬት ምርመራ በተገቢው ወቅት እንዲሰራላቸው ማድረግ፤
- የሶስተኛው 95 ማለትም የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ከሚወስዱ አዋቂዎችና ሕፃናት ውስጥ በደማቸው ያለው የኤች አይቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ50 ኮፒ በታች የሆኑት አሁን ካለበት 95% ወደ 96% ማድረስ፣
- የሶስተኛው 95 ማለትም የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ከሚወስዱ ሕፃናት በደማቸው ያለው የኤች አይቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ50 ኮፒ በታች የሆኑት 87% ወደ 95% ላይ ማድረስ፤
- 87,081(62%) ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎች የቫይራል ሄፓታይተስ ቢ ልየታ በማድረግ እራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
- 51,000 ለሚሆኑ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የሄፓታይተስ ሲ ምርመራ በማድረግ እራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
- የቫይራል ሄፓታይተስ ቢ እንዳለባቸው እራሳቸው ካወቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ መስፈርቱን ለሚያሟሉ 3659(58%) ሰዎች ህክምናውን እንዲያገኙ ማድረግ፤

- የቫይራል ሄፓታይተስ ሲ እንዳለባቸው እራሳቸው ያወቁ 1581 የህብረተሰብ ክፍሎች ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- 2,036 ለሚሆኑ ወላጆቻቸውን በኤድስ ምክንያት ላጡና ለችግር ለተጋለጡ ህጻናት የትምህርት ቁሳቁስ፣ የምግብና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣,1,252 ለሚሆኑ ኤችአይቪ በደማቸው ለሚገኝ ማህበረሰብ ክፍሎች የምግብና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
- ለ1,252 ለሚሆኑ ኤችአይቪ በሽታ ታማሚዎች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ እና 100% የኤች አይቪ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑና በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የኤች.አይ.ቪ መከላከል ስራን ማስፋትና ማጠናከር፤**
    - ከፍተኛ የኤችአይቪ ስርጭት ያለባቸውን አንድ የዞን ከተማ፣ ስድስት ከተማ አስተዳደሮችና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ትኩረት ያደረገ የኤች.አይ.ቪ መከላከል ስራ ማስፋትና ማጠናከር፤
    - በስትራቴጂክ እቅዱ ተለይተው የተቀመጡ ይበልጥ ተጋላጭና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማ/ብ ክፍሎችን ዒላማ አድርገው የሚተገበሩ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ለፕሮግራሙ አስፈላጊ ስትራቴጂክ መረጃዎች ለማመንጨት የሚያስችሉ ቅኝት ጥናቶች (PWID IBBS…)መደገፍና መከታተል፤
    - ይበልጥ ተጋላጭና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማ/ሰብ ክፍሎችን በኤችአይቪ መከላከል የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ፕሮግራሞች መድረስ፤
    - አደንዛዥ እጽ በመርፌ የሚጠቀሙ ሰዎችን ኤችአይቪን የመከላከል ስራዎች ለመተግበር የሚያስችሉ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ኮንሰፕት ኖት በማዘጋጀት በበላይ ሀላፊዎች ማጸደቅና ወደስራ መግባት፤
    - በአደንዛዥ እጽ በመርፌ በሚጠቀሙ ሰዎች ኤችአይቪን የመከላከል ስራዎች ለመተግበር የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ማጽደቅ ወደ ስራ መግባት፤
    - በትምህርት ገበታ/ት/ቤት ያሉ አፍላና ወጣቶችን በኤችአይቪ መከላከል የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ፕሮግራሞች መድረስ፤
    - ከት/ቤት ውጭ ያሉ አፍላና ወጣቶችን በኤችአይቪ መከላከል የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ፕሮግራሞች መድረስ፤
    - የወጣቶች ማዕከል ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል ፓኬጅ መከለስና ወቅታዊ ማድረግ፣
    - አካል ጉዳተኞችን ሌሎች መለዮ ለባሾችን በኤችአይቪ መከላከል የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ፕሮግራሞች መድረስ፤
    - ሁለተኛውን የኤችአይቪ መከላከል ፍኖተ ካርታ የተለያዩ መድረኮች በመጠቀም ማስተዋወቅ፣ አሳትሞ ማሰራጨት፤
    - ለተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ምቹና የተሟላ የስነ-ተዋልዶና ኤች አይቪ መከላከል አገልግሎት (KPP friendly) የሚሰጡ ተቋማትን ማስፋፋት፤
    - ማህበረሰቡ በኤችአይቪ መከላከልና መቆጣጠር ያለውን ተሳትፎ ለማጠናከርና የዘርፈብዙ ምላሹን በባለቤትነት እንዲይዘው የማህበረሰብ ንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤

- ይበልጥ ተጋላጭ እና አጠቃላይ ማህበረሰብን ትኩረት ያደረገ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበርና ማነቃቃት የሚችሉ የኤች.አይ.ቪ. መከላከል መልእክቶችን በቴሌቪዥን እና በሬዲዮን ማስተላለፍ፤
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ብሮሹር ማሳተምና ማሰራጨት፤
- የኤች አይ ቪ ቅድመ መጋለጥ መከላከል ህክምና (PrEP) አገልግሎቱ ተደራሽ በማድረግ ማስፋፋት፤

▪ **የአባለዘር በሽታዎች መከለከልና ሕክምናን ማጠናከር፤**

- የአባላዘር በሽታዎች ህክምና እና ቁጥጥር ላይ ህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን የሚተላለፍ አጭር መልእክት ማዘጋጀት እና ማሰራጨት፤
- የአባላዘር በሽታዎች መከላከልና ህክምና አገልግሎት በ syndromic approach መተግበር መተግበሩን በድጋፋዊ ጉብኝት መዳሰስ እና መደገፍ፤
- የአባላዘር በሽታ በsyndromic approach ከሁሉም ወረዳዎች ለተውጣጡ ጤና ባለሞያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
- የአባላዘር በሽታ መረጃ ጥራት እና መረጃ አጠቃቀምን ለማሻሻል የአባላዘር በሽታ ህክምና እና ሁሉም በሽታው የተገኘባቸው የኤችአይቪ ምርመራ ማድረጋቸውን በDHIS2 የሚላክ ሪፖርት አፈጻጸም በመገምገም ለወረዳዎች ግብረ መልስ መስጠት፤
- የአባላዘር በሽታ ህክምና ውጤታማነትን በሰርቬይ ማረጋገጥ፤

▪ **የመጀመሪያውን ዘጠና አምስት ለማሳካት የተለያዩ የላቀ ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ስልቶችን የመለየትና የመተግበር ስራዎች ማጠናከር፤**

- የተለያዩ የላቀ ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ስልቶችን ማጠናከርና መተግበር፤
    - ተጋላጭ ተኮር የኤች.አይ.ቪ. ምርመራና ምክር አገልግሎት (targeted HIV testing) ውጤታማነት የማጠናከር ስራ መስራት፤የIndex Case Testing ምርመራ አገልግሎትን ማጠናከር፤
    - ራስን በራስ ኤች አይ ቪ ምርመራን ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲያገኙ ማድረግ፤
    - የSocial Network Strategy (SNS) የምርመራ አገልግሎትን በ-pilot ማስጀመር፤(ሃዋሳ እና ይርጋለም ከተማ)
- የ Pediatric HIV Program Acceleration intiative ትግበራን በሁሉም ወረዳዎች በተጠናከረ መልኩ መተግበሩን ክትትል ማድረግ በሁሉም ወረዳዎች የDHTS (Diffrentiated HIV Testing Service) ትግበራን መደገፍ እና መከታተል፤
- የኤች አይ ቪ ምርመራን (ራስን በራስ ምርመራን ጨምሮ) በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ አጫጭር የሬድዮና የቴሌቪዥን መልዕክቶች አዘጋጅቶ ማሰራጨት፤
- ተመርምረው ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው መገኘቱን ያወቁ ሰዎችን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤

▪ **የፀረ-ኤች ቪ ህክምና አገልግሎት በማጠናከር ሁለተኛውን 95 ማሳካት የሚያስችሉ ስራዎች ማጎልበት፤**

- ሕፃናትና ታዳጊ ወጣቶች ስለ ኤች አይቪ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ አጫጭር የራድዮና የቴሌቪዥን መልዕክቶች አዘጋጅቶ ማሰራጨት፤

- በአገር አቀፍ ደረጃ ጥራቱን የጠበቀ የአዎቂዎች እና የህፃናት ጸረ-ኤች ቪ. ህክምና በሁሉም ክልሎች መተግበር፤
- የማህበረሰብ Differentiated HIV Service Delivery Model (DSD) ጨምሮ የተለያዩ DSD በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የፀረ- ኤች አይ ቪ. ህክምና በሚሰጡ ጤና ተቋማት ላይ መተግበር፤
- DSD አፈፃጸምን ለማሻሻል የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- DSD አገልግሎት ከኤች አይ ቪ. አገልግሎት ወጪ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር አቀናጅቶ መስራት እና ድጋፍ ማድረግ፤
- የሶስተኛ ደረጃ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ ለመተግበር ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
- የሕጻናት ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ፤ ህክምና እና ክብካቤ አገልግሎት አሰጥጥ ለማጠናከር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በህፃናት የፀረ ኤች አይ ቪ. ህክምና እና ክብካቤን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ በወረዳዎች መሀከል ማድረግ፤
- ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ለሚገኝ ሕፃናትና አፍላ ወጣቶች የሚሰጠውን የሥነ ልቦና ድጋፍ ያካተተ የDSD አገልግሎት መተግበርና ማስፋፋት፤
- የክሊኒካል ሜንተሪንግ ፕሮግራም ትግበራን በሁሉም ጠና ተቁዋም መደገፍ እና ክትትል ማድረግ፤
- የጥራት ማሻሻያ በሁሉም ወረዳዎች መተግበር፤
- የቲቢና የኤችአይ ቪ. የመከላከል ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ በሁሉም ወረዳዎች መተግበሩን ማረጋገጥ፤
- የቲቢ. መከላከያ ህክምናን የጸረ-ኤች ቪ. ህክምና እየውሰዱ ላሉና አዳዲስ ህክምና ለሚጀምሩ አዎቂዎች እና የህፃናት ሽፋኑን ከፍ ለማድረግ ትግበራውን ማጠናከርና መከታተል፤
- የኤችአይቪ. ጤና አገልግሎትን ቅንጅታዊ አሰራር ከሌሎች የስራ ሂደቶች (MH & NCD) ጋር የሚሰሩ ተግባራትን ማጠናከር፤
- ህክምና ጀምረው የሚያቋርጡ ታካሚዎችን ቁጥርን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎችን ማጠናከርና መተግበር፤

- **የሦስተኛውን 95 ለማሳካት የቫይራል ሎድ ምርመራ ሽፋን ለማሳደግ እና የጸረኤችአይቪ. መድሃኒት ተጠቃሚዎች በደማቸው ያለው የቫይረስ መጠን መቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማጠናከር፤**
  - የቫይራል ሎድ ምርመራ አፈጻጸምን ለማሻሻል የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤
  - በሁሉም የጸረኤችአይቪ. መድሃኒት የምስጡ ተቋማት የጸረኤችአይቪ. መድሃኒት ተጠቃሚዎች የቫይራል ሎድ ምርመራ አገልግሎት መመሪያ በሚያዘው መሰረት ጊዜውን ጠብቆ መከናወኑን መከታተልና መደገፍ፤
  - የኤች አይ ቪ. መጠን ምርመራን በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማሳደጊያ Job aids መከለስ እና አሳትሞ ለሁሉም የጸረኤችአይቪ. መድሃኒት የምስጡ ተቋማት ማሰራጨት፤
  - ከፍተኛ ቫይረስ መጠን ውጤት ላላቸው ታካሚዎች ጥራት ያለው ህክምና እንዲያገኙ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

- የህጻናት የቫይራል ሎድ ምርመራ አፈጻጸምን ለማሻሻልና ግንዛቤ ለማሳደግ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
- ከፍተኛ የቫይረስ ልኬት በደማቸው ለተገኘባቸው (>50copy/ml) ታካሚዎች የEAS እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ማጠናከር፤

▪ **የቫይራል ሄፓታይተስ መከላከል፣ ምርመራና እና ህክምና ስራዎችን ማጠናከር፤**

- የቫይራል ሄፓታይተስ መከላከል ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎችን መስራት፤
- የቫይራል ሄፓታይተስ ቢ እና ሲ ልየታ ስራዎችን በሁሉም ወረዳዎች በሚገኙ ጤና ተቋማት ማስጀመር፤
- የቫይራል ሄፓታይተስ ቢ እና ሲ የቫይራል ሎድ ምርመራ ከኤችአይቪ ምርመራ ጋር በቅንጅት እንዲሰራ መከታተል፤
- በሁሉም ወረዳዎች በተመረጡ ተቋማት የቫይራል ሄፓታይተስ ህክምና ማስጀመር፤
- በሁሉም ወረዳዎች በሚገኙ በተመረጡ ጤና ተቋማት የቫይራል ሄፓታይተስ ፕሮግራም አፈፃፀምን መከታተል እና መደገፍ፤

▪ **የኤች አይ ቪ እና የቫይራል ሄፓታይተስ ምርመራ እና ህክምና ግብዓቶች አቅርቦትን ማጠናከር፤**

- ተጋላጭ ተኮር ሰዎችን መመርመር የሚያስችል የፈጣን ኤች አይ ቪ መመርመሪያ ኪት አቅርቦት ማረጋገጥና ስርጭቱን መከታተል፤
- ለህሙማን ህክምና የሚውል የኤች.አይ.ቪ. መድኃኒቶችና የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ትንበያና ምጠና መስራት፤የግዢ ሁኔታና ስርጭት መከታተል፤
- የሄፓታይተስ ምርመራ እና ህክምና ግብዓቶች በግዢ እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- የአባላዘር በሽታ ህክምና አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው በቂ የመድሃኒት አቅርቦት ማመቻቸትና የኪት ስራ እና ስርጭቱን መከተታተል፤
- የኬሚስትሪ፤የሄማቶሎጂ እና ሲዲ4 ግዥና ስርጭት ሂደት መደገፍ፤
- ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ከሚገኙ ሰዎች የምግብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የፕላምፒነት ግዥና ስርጭት መደገፍ፤

▪ **በኤችአይቪ ምክንያት የሚከሰት አድሎና ማግለልን መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**

- አድሎና ማግለልን ለመቀነስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አቅም መፍጠር፤
- አድሎና ማግለል ያለበትን ደረጃ ለመፈተሽ በተጠናው ጥናት/ Stigma index ግኝቶችን መሰረት በማድረግ አድቮኬሲ ማካሄድ፤
- የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ዒላማ ያደረጉ አድሎና ማግለልን ለመቀነስ የሚረዳ መልዕክት ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣
- በየደረጃው ያሉትን ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ማህበራት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- በዘርፈ ብዙ የኤችአይቪ/ኤድስ ምላሽ ያለቸውን ተሳትፎ የማጠናከር ስራ መስራት፣

▪ **በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ህጻናት የሚሰጡ ድጋፍና ክብካቤ ተግባራትን ማጠናከር፤**

- የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረትን የማጠናከር ስራ መስራት፤
- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤

▪ **የኤችአይቪ/ኤድስ አጋርነትና ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር፤**

- በዘርፈ ብዙ ኤችአይቪ/ኤድስ ምላሽ ውስጥ የክልል ህዝብ ተወካዮች እና የዞን ም/ቤት ተሳትፎን የማጠናከር ስራ መስራት፤

- በዞንና እና በወረዳዎች የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግን ሥራዎችን የማጠናከር ስራ መስራት፤
- የኤችአይቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ትግበራን ለማጠናከር ከስትራቴጂክ ሴክተር አመራሮች ጋር ውይይት ማድረግ፣
- የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ፎረሞችን የማጠናከር ስራ መስራት፤
- በኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር፤

- **የኤች.አይ.ቪ. አመራርን እና ማስተባበር ስራን ማጠናከር፤**
  - የኤድስ ምክር ቤት ጉባኤ ማካሄድ፤
  - ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማድረግ፤
  - አጋር ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት በዘርፈ ብዙ ምላሹ የሚኖራቸውን ሚና ለማጠናከር የሚያስችል የጋር ምክክር ማድረግ፤
- **የግሎባል ፈንድ እና CDC ግራንት ትግበራ የተፋጠነ እና ውጤታማ እንዲሆን መደገፍ፤**
  - የተፋጠነና ውጤታማ የግራንት ትግበራ እንዲኖር መደገፍ፤
  - ለጋሽ ድርጅቱ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ NFM-4 Fund request write up ተጠናቆ እንዲቀርብ ድጋፍ ማድረግ፤
  - በወረዳዎች፣ በሲቪክ ማህበራትና በክልል ደረጃ ያለውን የግሎባል ፈንድ አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ፤
- **የኤች አይ ቪ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክትትልና ግምገማን ማጠናከርና የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ማሻሻል፤**
  - ወቅታዊ የመረጃ ጥራትን በሁሉም ጤና ተቋማት በየደረጃው ማረጋገጥ ግብረመልስ መስጠት፤
  - ማህበረሰብ መር የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋትና መከታተል፤
  - ከኤች አይቪ ጋር በተገናኘ በተጨማሪም የPMTCTን ዳሽ ቦርድን የመረጃ ጥራት ማሻሻል እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ክትትል እና ድጋፍን ማድረግ፤

### 1.3.2 ሌሎች በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር

#### 1.3.2.1 የቲቢ ሥጋ ደዌና ሌሎች የሳንባ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር

**ዒላማ**

- አጠቃለይ የቲቢ ልየታ መጠን ሽፋን 100% ላይ ማቆየት፤
- የማህበረሰብ አቀፍ የቲቢ ልየታ እና ህክምና ሽፋን ከ32% ወደ 50% ማሳደግ፤
- ከቲቢ በሽታ የመዳን ምጣኔን ከ85% ወደ 89% ማድረስ፤
- የቲቢ ህክምና ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ (TSR) ህሙማን ከ97% ወደ 100% ማሳደግ፤
- መድሀኒት የተላመደ ቲቢ ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ ህሙማን መጠንን ከ69% ወደ 75% ማሳደግ፤
- የግሉ የጤና ተቋማት የቲቢ ምርመራና ልየታ ሽፋንን ከ22% ወደ 25% ማሳደግ፤

### ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **የማህበረሰብ አቀፍ የቲቢና ሥጋ ደዌ በሽታዎች የመከላከል እና መቆጣጠር ስራን ማጠናከር፤**
  - የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በቲቢ በሽታ ልየታ፤ ሕክምና እና መከላከል ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን መስራት፤

- በጤና ኬላ በቲቢ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ስራዎችን ለማከናወን የሚረዱ ግብአቶችን ሟሟሏት፤
- የቲቢ ስርጭት ከፍተኛ በሆነባቸው ወረዳዎች ላይ የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን ማከናወን፤
- በቲቢ እና ሌሎች የሳንባ በሽታዎች ላይ አጠቃላይ የማህበረሰብ ትምህርት እና ንቅናቄ ተግባራትን ማከናወን፤
- የቲቢ መከላከል እና መቆጣጠር ተግባራትን ከት/ቤት ጤና ፕሮግራም ጋር በማቀናጀት መተግበር፣ የክትትል እና ግምገማ ስራዎችን ማከናወን፤

- **የቲቢና ሌሎች የሳንባ በሽታዎች ልየታ፣ የምርመራ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፤**
  - ሁሉን አቀፍ (ጂንኤክስፐርት፣Urine LAM፣ mWRDA) የቲቢ ምርመራ አገልግሎት ማስፋፋትና መተግበር፤
  - ፈጣን የቲቢ መመርመሪያ ጣቢያዎች የናሙና ቅብብሎሽ አማራጮችን ማስተዋወቅ እና እንዲተገበሩ ማድረግ፤
  - የቲቢ የማይክሮስኮፒ ምርመራ አገልግሎትን ማስፋፋትና ትግበራውን ማከናወን፤
  - የፈጣን የቲቢ መመርመሪያ ዘዴዎችን አጠቃቀም ሽፋን (Gene xpert and others utilization) ሽፋን ማሳደግ፤
  - የቲቢና የወባ በሽታ የላቦራቶሪ የውጫዊ ጥራት ቁጥጥር (EQA) በአንድነት እንዲሰራ ማጠናከር፤
  - ለቲቢ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ማህበረሰብ ክፍሎች ያተኮረ ስልታዊ የቲቢ ልየታና እና ምርመራ አገልግሎትን ማስፋፋት እና ማጠናከር፤
  - ይበልጥ የቲቢ ተጋላጮችን ቦታዎች መለየት እና ዒላማ ያደረገ ልየታ እና ወቅታዊ Periodic active screening አገልግሎትን ማስፋፋት እና ማጠናከር (በትምርት ቤቶች፣ በስራ ቦታዎች፣ ማረሚያ ቤቶች)
  - ለቲቢ ህሙማን ቤተሰቦች የቲቢ ልየታ ፣ ምርመራ እና ወቅታዊ ክትትል አገልግሎትን ማጠናከር
  - ይበልጥ የቲቢ ተጋላጭ በሚኖሩባቸው በጤና ተቋማት፣በዩንቨርስቲ፣ በማረሚያ ቤቶች ፣ በተፈናቃዩች መንደር፣ በስራ ቦታዎች ...ወዘተ የቲቢ ብክለት መከላከል ሥራዎች ትግበራን ማጠናከር፤

- **የቲቢ ሥጋ ደዌ እና መድሃኒት የተላመደ ቲቢ ምርመራ እና ህክምና ግብዓቶች አቅርቦትን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
  - የቲቢ መከላከል ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒቶችና የመመርመሪያ ግብዓቶች አቅርቦት ማረጋገጥና ስርጭቱን መከታተል፤
  - ለአዲስ እና ነባር መድኃኒት የተለማመደ ቲቢ ታካሚዎችን ለማከም የሚያስችሉ መድኃኒቶችና የመመርመሪያ ግብዓቶች እንዲሁም የጎንዮሽ ህመሞች ማከሚያ መድኃኒቶች አቅርቦት ማረጋገጥና ስርጭቱን መከታተል፤
  - ለቲቢ፤ መድሃኒት የተላመደ ቲቢ ምርመራ እና ህክምና ግብዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ትንበያና ምጠና መስራት፤

- **ህጻናት ቲቢ ልየታ እና ህክምና ሽፋንን ማጠናከር፤**
  - በወረዳዎች የህፃናት ቲቢ ፕሮግራም አገልግሎት እና አሰራር ስርዓት ማጠናከር፤

- በአዲሱ WHO guideline መሰረት የተጀመረዉን የህፃናት እና አፍላ ወጣቶች ቲቢ ስልጠና ማኑዋል መሰረት ትግበራው ክትትል ማድረግ፤
- የህጻናት ቲቢ ልየታና ህክምና ላይ ከ OPD ፣ IMNCI ፣ high load pediatric Hospitals እና ከሁሉም ወረዳዎች ለተውጣጡ ባለሞያዎች ስልጠና መስጠት፤
- ለቲቢ ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት የቲቢ ልየታ፣ ምርመራ እና የቅድመ መከላከል ህክምና አገልግሎትን ማጠናከር፤
- ከቲቢ ሕሙማኑ ጋር አብረው የሚኖሩና ሰዎችን ልየታ እና የምርመራ ክትትል በየጊዜዉ ማድረግ፤
- የቲቢ መከላከያ መድኃኒት በ 3HP full scale up አፈፃፀም ክትትል ማድረግ፤
- የበለጠ ለቲቢ ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የቲቢ ቅድመ መከላከል ህክምና እገልግሎት ማሰጀመር፤
- ከ 15 ዓመት በታች ለሆኑ ከቲቢ ህሙማን ጋር ቅርርብ ለነበራቸው የቅድመ ቲቢ መከላከል ህክምና አገልግሎትን ሽፋን ማሻሻል፤
- የበለጠ ለቲቢ ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎችን የቲቢ ቅድመ መከላከል ህክምና አገልግሎት ማስጀመር፤
- የቲቢ መከላከል ህክምና አገልግሎት ሽፋን (TPT) ማጠናከር እና ማሳደግ፤

- ***መድሀኒት የተላመደ ቲቢ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች ማጠናከር፤***
  - መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህክምና መስጫ ተቋማት BPaLM/BPaL የ6 ወር novel treatment regimen ትግበራውን ማስጀመር እና መከታተል፤
  - የመድሃኒት የተላመደ ቲቢ በሽታ ልየታን active DR TB case finding ስልቶችን መተግበር፤
  - መድሃኒት የተላመደ ቲቢ የህክምና ጥራትን ትግበራ ማከናወን፤
  - መድሐኒት የተላመደ ቲቢ የበሽታ ቅኝት መረጃ ማስፋፋት እና ማጠናከር (MDR_tracker)

- **በግል ጤና ተቋሟት እና ሌሎች መንግስታዊ በሆኑ ጤና ተቋሟት የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን ማጠናከር፤**
  - በሁሉም ደረጃ የPPM-TB አመራር ማጎልበት፤
  - በበጀት ዓመቱ 15 አዳድስ የPPM-TB ተቋማት ማስፋፋት፤
  - የPPM-TB ጤና ተቋማት የግብዓት አቅርቦት ስርዓት እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፤
  - የPPM-TB ጤና ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - የPPM-TB ጤና ተቋማት መረጃ ስርዓትን ማጠናከር፤
  - በመንግሥታዊ እና በግል ጤና ተቋማት የቲቢ ህሙማን፣ ልየታ፣ ምርመራ እና የመድሐኒት ክትትል አገልግሎት ቅብብሎሽ ማጠናከር፤
  - በግል ጤና ተቋማት የቲቢ ልየታ ተግባራት እንዲጠናከር ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

- **የቲቢ/ ኤች አይ ቪ እና ሌሎች በሽታዎች የተቀናጀ ስራዎች ማጠናከር፤**
  - የቲቢ ታካሚዎችን ሙሉ በሙሉ የኤች አይ ቪ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - በቲቢ ህክምና ላይ እያሉ ኤች አይ ቪ በምርመራ ለተገኘባቸው በሙሉ ኤ አር ቲ እንዲጀምሩ ማድረግ፤
  - የቲቢ ብክለት መከላከል በጤና ተቋማት በማጠናከር የቲቢ ስርጭትን በተለይም በጤና ተቋማት እና ሰዎች ተፋፍገው በሚኖሩባቸው ተቋማት መተግበር፤

- በሁሉም ጤና ተቋማት (ሆስፒታል፣ጤና ጣቢያ፣ጤና ኬላ) አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የተጠናከረ እና ጥራት ያለው የቲቢ ምልከታ ልየታ TB screening ስራዎችን መስራት፤
- የተቀናጀ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፤
- በሁሉም ወረዳዎች እና በተመረጡ ተቋማት የመስክ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- ወቅቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ግምገማ ማከናወን፤

- **ሌሎች የሳንባ በሽታዎች መቆጣጠርና መከላከል ሥራዎችን ማጠናከር፤**
  - የተቀናጀ የቲቢ እና COVD19 የጋራ ሥራዎችን መስራት፤
  - የአስም እና ስር የሰደዱ የመተንፈሻ አካል በሽታዎች ክብካቤ አገልግሎትን ከተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና ትኩረት ከሚሹ ሀሩራማ በሽታዎች ፕሮግራም ክፍሎች ጋር ቅንጅታዊ ትብብር መፍጠር፤

### 1.3.2.2 የሥጋ ደዌ በሽታ ቁጥጥርን ማጠናከር

**ዒላማ**

- የሥጋ ደዌ በሽታ ልየታና ህክምና መጠንን ወደ 95% ማድረስ፤
- በሥጋ ደዌ በሽታ ምክንያት ሁለተኛ ደረጃ የሚደርሰውን አካል ጉዳት መጠን ከ25% ወደ 8% ማውረድ፤
- በሥጋ ደዌ የሚያዙ የህጻናት መጠን ከ10% በታች ማዉረድ፤
- ሕክምና በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁ የሥጋ ደዌ ታማሚዎች ከ90% በላይ ማድረስ፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **ስጋ ደዌ ህሙማንን የመለየትና ህክምና ሽፋን ማጠናከርና ማሻሻል፤**
  - የማህበረሰብ አቀፍ የሥጋ ደዌ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠርን እንድሁም ግንዘቤን መፍጠር፤ የቤት ለቤት ዘመቻን ማከናወን፤
  - ሀገርና ክልል አቀፍ የበሽታው ስርጭት ያለባቸውን ወረዳዎች (ቦታዎች) በመለየት የመከላከል እና የመቆጣጠር ስራ መስራት፤
  - የሥጋ ደዌ ልየታ፤ ምርመራ፣ ህክምና እና ክብካቤን ማጠናከር እና የህሙማን ሥቀይ መቀነስ፤
  - ለስጋ ደዌ ህመምተኞች የሚሆን መድኃኒቶች አቅርቦት ማረጋገጥና ስርጭቱን መከታተል፤
  - የኂልዮሽ በአምስት ዓመት ውስጥ ከሥጋ ደዌ ህሙማን ጋር የነበሩ ሰዎች ላይ የስጋ ደዌ ህመም ምልከት ልየታ (contact secreening) መስራት
  - የበሽታው ስርጭት ባለባቸው አካባቢዎች የመከላከል እና መቆጣጠር ተግባራትን በመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሀድ ደረጃ ከት/ቤት ጤና ፕሮግራም ጋር በማቀናጀት እንዲተገበር ማድረግ፤
  - ለስጋ ደዌ ህሙማን ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች የቅድመ መከላከል ህክምና አገልግሎት ማስጀመር እና ማስፋፋት፤
- **የቲቢና ሥጋ ዴዌ በሽታዎች መከላክላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም አመራርንና ቅንጅታዊ አሰራርን በየደረጃው ማጠናከር፤**
  - ለጤና ቢሮ፣ዞን ጤና መምሪያ እና ለወረዳ ጤና ጽ/ቤት አመራሮች እና ባለሙያዎች በቲቢ እና ስጋ ደዌ በሽታ መካላከል እና መቆጣጠር የአመራርና መረጃን የመተንተን፤ መጠቀም ላይ ስልጠና መስጠት፤

- ከጤና ውጭ ያሉ ሴክተር መሰሪያ ቤቶች እና አጋር አካላት ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከር፤
- በደረጃው ያሉ የቲቢ መከላከል እና መቆጣጠር አመራሮች በሀብት አጠቃቀም እና አሰባሰብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤

### 1.3.2.3 የወባ በሽታን መከላከል እና መቆጣጠር

**ዒላማ**

- በወባ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን ምጣኔ ከ27/1000 ወደ 12/1000 መቀነስ፤
- በወባ በሽታ ምክንያት የሚሞቱ ህሙማንን ከ0.12/100,000 ወደ 0.06/100,000 ማድረስ፤
- ወባማ በሆኑ አካባቢዎች ለርጭት የተመረጡ 478,172 ቤቶችን የፀረ-ትንኝ ኬሚካል መርጨት፤
- 23,214 የመኝታ አጎበር በማሰራጨት ሽፋኑን ባለበት 100% እንዲቆይ ማድረግ፤
- የወባ ማስወገድ eligible index case and foci investigation ከ28% ወደ 65% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በወባ ማስወገድ ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሻሻል ስራዎች ማጠናከር፤**
  - ሕብረተሰቡን ጨምሮ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የወባ ሳምንትን በየደረጃው ማክበር፤
  - የወባ መልዕክቶችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በሆነ በክልል ደረጃ በሚተላለፍ ብዙኃን መገናኛ ማስተላለፍ፤
  - ክልሉን ነባራዊ ሁኔታ እና የወባ ማስወገድ ላይ በመመስረት የተዘጋጀውን የቴሌቪዥንና የሬዲዮ መልዕክቶች በአከባቢ መገናኛ ብዙኃን እንዲተላለፉ የበጀት ድጋፍ ማድረግና መከታተል፤
  - የወባ ስርጭት ባለባቸው ወባማ አካባቢዎች ሞባይል ቫንን በመጠቀም እና የማህበረሰብ ንቅናቄ በማካሄድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤
  - የአጎበር አጠቃቀምን ለማሻሻል በማህበረሰብ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽንና የጤና የጎጥ ጤና መሪዎች Village Health Leader (VHL) እና የሴቶች የጤና ልማት ቡድን በመጠቀም የህበረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበትና መከታተል፤
  - ክልል ጤና ቢሮ በወባ ማስወገድ ቅንጅታዊ አሰራርንና አጋርነትን ለማጎልበት ከትምህርት፣ ከግብርና ሌሎች ሴክተሮች፣ ከየሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ግለሰቦችን፣ ወዘተ ጋር የማህበረሰብ ንቅናቄ እንዲካሄድ የሙያዊና የበጀት ድጋፍ ማድረግና መከታተል፤
- **የወባ ትንኝና (ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች) ቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የላርቫ ሶርስ ማናጅመንት (LSM) ስራዎችን ማጠናከር፤
  - የአጎበር ስርጭት ዘመቻ ማድረግ፤
  - የተሰራጩ አጎበር አጠቃቀም ክትትል ማድረግ፤
  - በፀረ-ወባ ኬሚካል ርጪት በታቀዱ ቤቶች ማካሄድ፤
  - ላርቪሳይድ ኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤
  - የተቀናጀ የትንኝ ቁጥጥር ስራዎች ላይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፤
  - የትንኝ ቁጥጥር ስራዎችና ተግባራት ላይ ጥናቶችን ማድረግ፤

- **የወባ በሽታ ምርምራና ህክምናን አገልግሎትን ማጠናከር፤**
    - በበጀት ዓመቱ የሚያሰፈልጉ የወባ ምርመራና ህክምና መድኃኒቶች ዕቅድ ማቀድ፣ ስርጭቱንና አጠቃቀሙን መከታተል፤
    - ለወባ በሽታ ምርመራ እና ህክምና የተገዙ መድሃኒቶች በአግባቡ ህብረተሰቡ ጋር መድረሱን የሚያረጋግጥ ከቅርንጫፎቹና ከተጠቃሚ ጤና ተቋማት ጋር መገምገም፤
    - በተከለሰው የወባ ምርምራና ህክምና አሰጣጥ መመሪያ ላይ ከወረዳዎች ለተወጣጡ ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠት፤
    - በ2016 በጀት አመት በክልሉ ውስጥ በ10 የግል ጤና ተቋማት የወባ በሽታ ምርመራ እና ህክምና ማስጀመርና የአገልግሎት አሰጣጡን መከታተል፤
    - በተዘጋጀው የወባና ቲቢ የተቀናጀ የላብራቶሪ ምርመራ መመሪያ መሰረት ጥራትና ቁጥጥር ማካሄድ፤
    - በልማት ኮሪደሮች የወባ በሽታ ምርመራና ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - የወባ በሽታ የላብራቶሪ ምርመራ ጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጫ (external quality assurance)ማካሄድ፤
- **የወባ ማስወገድ እና ቅኝትን ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የወባ ማስወገድ የCase እና foci investigation and Response አፈጻፀምን በማሻሻል የወባ ማስወገድ ቅኝትን ስራ መስራት፤
    - የወባ ማስወገድ ፕሮግራም አፋጻጸምን ለማጠናከር ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፣
    - በማህበረሰብና በጤና ኬላ ደረጃ የወባ ማስወገድ ሪፖርትንና በeCHIS ወረዳዎች የeCHIS መረጃ አያያዝ ማጠናከር፤
    - የወባ ማሰወገድ ፕሮግራም አፋጻጸምን ለማጠናከር ከዞኖች፣ ከወረዳዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መገምገም፤
    - የወባ ማሰወገድ ፕሮግራም አፈጻጸምን ለማሻሻል በየደረጃው Taskforce እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ፤
    - በየሳምንቱ የሚመጡ መረጃዎችን በመተንተን ለዞኖችና ለወረዳዎች ግብረ መልስ መስጠት፤
- **ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎችን መከላከል እና ህክምና አገልግሎትን ማጠናከር፤**
    - በክልል ደረጃ የማህበረሰቡ የጤና ችግር የሆኑትን ሌሎች ቬክተር ቦርን በሽታዎችን መለየት፤
    - የሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች መከላከል፣ ምርመራ እና ህክምናን መስጫ መመሪያ ማዘጋጀት፤
    - በሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች የሚከሰቱ ወረርሺኞችን በመለየት መስራት፤
- **የክትትልና ግምገማ ስራዎች እንዲሁም የግሎባል ፈንድ በጀት አጠቃቀምን ማሻሻል፤**
    - ለበጀት ዓመቱ የተመደበውን የግሎባል ፈንድ በጀት ዝርዝር ስርጭት ማዘጋጀትና ከወረዳዎች ጋር መፈራረም፤
    - የፕሮግራም፣ የፋይናንስና የማኔጅመንት አፈጻጸምን የሚመለከት ዓመታዊ ሪፖርት PU/DR ለጤና ሚኒስቴር መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር መላክ፤
    - ከፌምና (PHEM) ከዲኤችኤስ 2 (DHIS2) የሚገኙ የወባ መረጃዎችን ማደራጀት፣ መተንተንና ለዉሳኔ አሰጣጥ ዝግጁ ማድረግ፤

- ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ቋት የሚመጡ የወባ እና ተያያዥ ሪፖርቶች መረጃን በማናበብ ጥራት ማሻሻል፤
- የAn.stephensi ስርጭት፣ ባህሪ እና በወባ በሽታ ስርጭት ላይ ያለው ሚና ላይ ጥናት ማካሄድ፤

### 1.3.2.4 ትኩረት የሚሹ የቆላ በሽታዎችን መቆጣጠር

**ዒላማ**

- በሁሉም ለተላላፊ የዝሆኔ በሽታ ተጋላጭ በሆኑ 2 ወረዳዎች ለሚገኙ ሰዎች 262,571
  - ህክምና መስጠት እና አፈጻጸሙንም ከ65% በላይ ማድረግ፤
- ለቢልሃርዝያ በሽታ ተጋላጭ በሆኑ 12 ወረዳዎች የሚገኙ እድሜያቸው በመማር እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ለ537,344 ልጆች የማህበረሰብ አቀፍ መድሃኒት እደላ ማድረግ እና አፈጻጸሙንም ከ75% በላይ ማድረስ፤
- ለአንጀት ትላትል በሽታዎች ተጋላጭ በሆኑ 38 ወረዳዎች የሚገኙ እድሜያቸው በመማር እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ለ2,957,469 ልጆች የማህበረሰብ አቀፍ መድሃንት እደላ ማድረግ እና አፈጻጸሙንም ከ75% በላይ ማድረስ፤
- ለትራኮማ በሽታ ተጋላጭ በሆኑ 25 ወረዳዎች ለሚገኙ ለ2,908,405 ሰዎች የማህበረሰብ አቀፍ መድሃት ህክምና ማደረግ እና አፈፃፀሙን ከ80% በላይ ማድረስ፤
- ለትራኮማ ተጋላጭ በሆኑ ወረዳዎች በትራኮማ አማካኝነት የአይን ቆብ መቀልበስ ችግር ላጋጠማቸው ሰዎች የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና አገልግሎት ከ8,691 ወደ 10,777 ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የትራኮማ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የማህበረሰብ አቀፍ ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ወረዳዎች የመድሀኒት ስርጭት ማካሄድ፤
  - ከጤና ሚኒስቴርና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ወቅቱን የጠበቀ የትራኮማ ዳሰሳ ጥናቶች (ኢምፓክት ሰርቬይ እና ሰርቪላንስ) ማካሄድ፤
  - በተመረጡ የገጠር ከተሞች የትራኮማ በሽታ ስርጭት መነሻ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
  - የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና በተገቢው ጥራት አገልግሎትን መሰጠት፤
  - የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና የሚሰጡ ባለሙያዎችን ማሰልጠን፤
  - ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የድጋፍ፤ ክትትል እና ጥራት ቁጥጥር የሚሰሩ ባለሙያዎችን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማካሄድ፤
  - ከቀዶ ህክምና በኂላ ዳግም የአይን ቆብ መቀልበስ ችግር ላጋጠማቸዉ ሰዎች አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን እና ተቋማትን በመለየት ባለሙያዎችን ማሰልጠን እና አገልግሎቱን ማስጀመር፤
  - የትራኮማ በሽታን ለማጥፋት የተቀመጠዉን መስፈርት ያሚሉ ወረዳዎች የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና እንዲሰጡ ድጋፍ ማድረግ፤
  - የፊት ንፅህና እና የአከባቢ ንፅህና አጠባበቅ ማበልጸግ ስራዎችን ወደ መደበኛ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲሻገሩ በማድረግ መተግበር፤
  - በትራኮማ ፕሮግራም ለተሻለ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ማህበረሰቡን ማሳተፍ፤
  - በትራኮማ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ለፕሮግራሙ የሚጠቅሙ ካሉ ዳሰሳ በማድረግ ትግባራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

- በትራኮማ ክትባት ፊጠራ ላይ የክልላችን ዩኒቨርስቲዎች እና የምርመር ተቋማት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ግንኙነት መፍጠር፤

- **የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች እና የብልሀርዝያ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - በክልል ደረጃ በሁለት ዙሮች ሲደረግ የነበረው የብልሀርዝያ እና የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መድኃኒት እደላን ለመደገፍ የሚሰራውን የበሽታዎች ልየታ ጥናት ማካሄድ፤
  - ለቢልሃርዚያ እና የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች የማህበረሰብ አቀፍ የመድኃኒት ስርጭት የሚያስፈልጉትን መድኃኒቶች፤ በጀት እና ሌሎችም ግብዓቶች ማሰባሰብ እና ማሰራጨት፤
  - የበሽታ ዳሰሳ ቅኝት ማድረግ እና ለወረዳዎች እና ለተቋማት ድጋፋዊ ጉብኝት ማካሄድ፤
  - ወቅታዊ ግብረ መልስ ለወረዳዎች፤ ለተቋማት እና ለድጋፍ ሰጭ አካላት መስጠት፤

- **የተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆነው የዝሆኔ በሽታዎች መከላከል እና መቆጣጠር የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**
  - አመታዊ የማህበረሰብ አቀፍ የመድሃኒት እደላ ማካሄድ፤
  - ህክምናው በሚሰጥባቸው ጤና ተቋማት ለጤና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
  - የማህበረሰብ አቀፍ የመድሃኒት እደላ ለጨረሱ ወረዳዎች የበሽታ ዳሰሳ ቅኝት ማድረግ፤
  - የተቋማት ድጋፋዊ ጉብኝት ማካሄድ፤
  - መረጃ መሰብሰብና ጥራት መቆጣጠር እና ወቅታዊ ግብረ መልስ ለወረዳዎች መስጠት፤

- **የሊሽማኒያሲስ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**
  - ምርመራ እና ህክምናው በሚሰጥባቸውና ጤና ተቋማት ለጤና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
  - ወቅታዊ የሆነ ትንብያ መስራትና እና የግብዐቶችን ስርጭት መከታተል፤
  - የበሽታ ዳሰሳ ቅኝት እና የተቋማት ድጋፋዊ ጉብኝት ማካሄድ፤
  - የሊሽማኒያሲስ መረጃ መሰብሰብና ጥራት መቆጣጠር እና ወቅታዊ ግብረ መልስ ለወረዳዎች መስጠት፤

- **የጊኒዎርም በሽታን ማጥፋት ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የህብረተሰቡን ባህሪ ሊያሻሽሉ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት፤
  - በሰዎችና በእንስሳት ላይ የሚደረገውን ሰርቬላንስ ማጠናከር እና ማስፋፋት፤

- **ትኩረት የሚሹ ሀሩራማ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሴክተሮችን ቅንጀታዊ አሰራር ማጠናከር፤**
  - የተቀናጀ የውሃ ሳኒቴሽን እና ትኩረት የሚሹ ሀሩራማ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ቅንጂታዊ አሰራርን መፍጠር፤
  - የንጹህ ውሃ እና ሳኒቴሽን ስራዎች በአመራሮች ትኩረት እንዲያገኝ እና ግኝቶች እንዲኖሩ በማስቻል ማስተዋወቅና ማስፋፋት፤
  - የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤
  - በመረጃ ላይ የተመሰረተ የማህበረሰብና የትምህርት ቤት የውሃ ንጽህናና ሳኒቴሽን መሰረተ ልማቶች እንዲኖሩ ማስቻልና ማስፋፋት እገዛ ማድረግ፤

### 1.3.2.5 ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር

**ዒላማ**

- ዕድሜአቸው ከ30-49 እድሜ ክልል የሆኑ ሴቶችን ቅድመ ካንሰር የማህፀን በር ምርመራ ለ58,595 አገልግሎትን በመስጠት ሽፋኑን ከ29% ወደ 42% ማድረስ፤
- የቅድመ ካንሰር ምልክት ያለባቸው ሴቶች ለ3,516 የህክምናውን አገልግሎት በመስጠት ከተመረመሩት ሽፋኑ ከ80% ወደ 90% ማድረስ፤
- እድሜያቸው ከ30 አመት በላይ ከሆኑት ማህበረሰብ ውስጥ 866,438 (61%) የከፍተኛ ደም ግፊት ልየታ ማድረግ፤
- የከፍተኛ ደም ግፊት ህክምና ለ51,336 (50%) አዳዲስ ታማሚዎች መስጠት፤
- የደም ግፊት ህክምና ከሚከታተሉ ሰዎች በቁጥጥር ስር የዋለ ሽፋን 25,668 (50%) ማድረስ፤
- እድሜያቸው ከ40 አመት በላይ እንዲሁም ሌሎች ለስኳር ህመም ተጋላጭ ከሆኑት ማህበረሰብ ውስጥ ለ25,609 (19%) ለስኳር ህመም ልየታ ማድረግ፤
- የስኳር ህመም ህክምና አገልግሎት ለ794 (50%) አዲስ ታማሚዎች መስጠት፤
- በስኳር ህመም ህክምና ከሚከታተሉ ህመምተኞች የስኳር መጠኑ በቁጥጥር ስር የመዋል ሽፋን (50%) ማድረስ፤
- የካታራክት ቀዶ ህክምናን ለ3,826 ታካሚዎች መስጠት፡ (የካትራክት ሰርጅካል ሬት አሁን ካለበት ከ414 ወደ 800/1,000,000 ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የማህፀን በር የቅድመ ካንሰር ልየታ፤ ህክምና እና ሪፈራል አገልግሎት በሁሉም የህክምና መስጫ ደረጃዎች ማስፋፋትና ማጠናከር፤**
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ዙሪያ የህ/ሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የአድቮኬሲ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት የሚሠጡ አዳዲስ ተቋማትን ማስፋፋትና አገልግሎቱን ማስጀመር፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና የሚውሉ ግብዓቶችን ማሟላት፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና ላይ ለባለሙያዎች የአሰልጣኞ ስልጠና እና መሰረታዊ ስልጠና መስጠት፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት በሚሠጡ ጤና ተቋማትን ለማጠናከር አዲስ ጤና ተቋማት አገልግሎቱን ማስጀመር፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ የሜንተርሽፕ መመሪያ መተግበር፤
    - የማህፀን በር ካንሠር አገልግሎት ለማጠናከር ለክልሎች በጀት በማስተላለፍ የአገልግሎት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - አገልግሎቱን ለመከታተል፤ ለመገምገም የሚረዱ መዛግብት እና ቅፆችን ማሳተም እና ማሰራጨት፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ ሜንተርሽፕ ለመስጠት የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤

- የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ በተመረጡ ጤና ተቋም ላይ የሜንተርሺፕ አገልግሎት መስጠትና ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ የክልል ጤና ቢሮዎች የሜንተርሺፕ አገልግሎት በተቀናጀ መልኩ እንዲያከናውኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - የኤች አይቪ ቫይረስ በደማቸው ለሚገኝ ሴቶች (እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ) የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ማስፋፋት እና ማጠናከር፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር፤
    - የማህፀን በር ካንሠር ቅድመ ልየታ ምርመራ እና ህክምና የሪፈራል አገልግሎትና የመረጃ ጥራትን ማጠናከር፤
- ስር የሰደዱ የመተንፈሻ አካል በሽታዎች(አስምና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የመተንፈሻ አካል በሽታ) ልየታ፣ ምርመራ፣ ህክምናና ሪፈራል አገልግሎት በሁሉም የህክምና መስጫ ደረጃዎች ማጠናከርና ማስፋፋት፤
    - ስር በሰደዱ የመተንፈሻ አካል በሽታዎች ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና ለ4 አጠቃላይና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች መስጠት፤
    - ስልጠና የወሰዱ ጤና ተቋማትን ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ፤
- የከፍተኛ ደምግፊትና ሌሎች የልብና ደም ስር በሽታዎች ልየታ፣ ምርመራ፣ ህክምና እና ሪፈራል አገልግሎት በሁሉም የህክምና አገልግሎት መስጫ ደረጃዎች ማጠናከርና ማስፋፋት፤
    - የደም ግፊትና ሌሎች የልብና ደም ስር በሽታዎች ልየታ ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደጊያ ስራዎችን ማጠናከር (በጤና ኤክስቴንሽን፣ በተቋማት የጤና ትምህርት፣ በትምህርት ቤት ጤና፣ በሚዲያ...... )
    - የደም ግፊት ማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደጊያ፣ ምርመራና ህክምና የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ማስፋፋት፤
    - በከፍተኛ ደም ግፊት ልየታ፣ ምርመራ፣ ህክምናና ጤናማ የኑሮ ዘይቤ የምክር አገልግሎት ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና ለ10 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች መስጠት፤
    - በከፍተኛ ደም ግፊት ልየታ፣ ምርመራና ህክምና፣ ጤናማ የኑሮ ዘይቤ የምክር አገልግሎት ላይ ያተኮረ ለ20 ጤና ጣቢያዎች የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
    - የትምባሆ ሱስ ህክምና ላይ ያተኮረ መሰረታዊ ስልጠና ከመጀመሪያ ደረጃና ከጤና ጣቢያዎች ለተውጣጡ 10 ጤና ባለሙያዎች መስጠት፤
    - ለ952 hotline counsellors ትምባሆ ስለማቆም የቴሌፎን የምክር አገልግሎት ስልጠና ለ 5 ተሳታፊዎች መስጠት፤
    - የልብና ደም ስር በሽታዎች ምርመራና ህክምና አገልግሎት ቀድመው የጀመሩና በዚህ አመት ስልጠና የወሰዱ ጤና ተቋማትን በድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤
    - የልብና ደም ስር በሽታዎች መርሀግብር አፈጻጸምን በተመለከተ አንድ ግምገማዊ ስብሰባ (Review Meeting) ማካሄድ፤

- የከፍተኛ ደም ግፊት መረጃ መመዝገቢያና ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችና፣ ፕሮቶኮሎች በጤና ተቋማት ማሟላት፤
- በከፍተኛ ደም ግፊት በሽታ ቅድመ ምርመራ፣ ህክምናና የልብ ህመም ተጋላጭነት ትንበያ መረጃ ላይ ያተኮረ ስልጠና ለ50 ጤና ባለሙያዎች መስጠት፤
- የልብና ደም ስር በሽታዎች ህክምና መድሃኒቶችና የደም ግፊት መመርመሪያ መሳሪያዎች ለጤና ተቋማት እንድገዛ ማድረግና መሰራጨታቸውን መከታተል፤
- የልብና ደም ስር በሽታ ተጋላጭነት ትንበያና ህክምና ላይ ያተኮረ ስልጠና ለ30 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች መስጠት፤
- በልብና ደም ስር በሽታ ተጋላጭነት ትንበያና ህክምና ላይ ያተኮረ ለ35 ጤና ጣቢያዎች የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
- የልብ ህመም ተጋላጭነት ትንበያ ቻርቶችን በ40 ጤና ተቋማት ማሟላት፤
- በሪውማቲክ የልብ ህመም መከላከልና ህክምና ዙሪያ ለ4 አጠቃላይ እና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
- በሪውማቲክ የልብ ህመም መከላከልና ህክምና ዙሪያ ስልጠና የወሰዱ ጤና ተቋማትን ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤
- ከሁሉም ዞኖች(ክፍለከተሞች) ለተውጣጡ 10 የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መርሃግብር ተጠሪዎች program management ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
- በአገር አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ደም ግፊት እና ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና አጋላጭ መንስኤዎቻቸዉ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- የልብና ደም ስር በሽታዎች የሚሰጡት አገልግሎቶች ፕሮቶኮሉን በጠበቀ መልኩ እንዲሰጡ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

▪ **የስኳር ህመም ልየታ፣ ምርመራና ህክምና እና ክትትል አገልግሎት በሁሉም የህክምና መስጫ ደረጃዎች ማጠናከርና ማስፋፋት፤**

- ለስኳር ህመም ስኳር ህመም ልየታ ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደጊያ ስራዎችን ማጠናከር (በጤና ኤክስቴንሽን፣ በተቋማት የጤና ትምህርት፣ በትምህርት ቤት ጤና፣ በሚዲያ...... )
- ለስኳር ህመም ስኳር ምርመራና ህክምና የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ማስፋፋት፤
- ለ15 ባለሙያዎች የስኳር ህመም ልየታና ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል ላይ የአሰልጣኞ ስልጠና መስጠት፤
- ለ25 ባለሙያዎች የስኳር ህመም ልየታና ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል ላይ የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
- የስኳር ህመም ልየታ፤ ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል የመረጃ አያያዝና አጠቃቃም ስርዓት ለማጠናከር ለ25 ጤና ባለሞያዎች ስልጠና መስጠት፤
- የስኳር ህመም ልየታ፤ ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል የመረጃ አያያዝና አጠቃቃም ስርዓት ለማጠናከር የተዘጋጁት መዛግብት፤ ቅጾችን ማሳተም እና ማሰራጨት፤
- የስኳር ህመም ፕሮግራም አፈጻጸምን ከባለድርሻዎች ጋር ምክክርና ግምገማ ማካሄድ፤
- በስኳር ህመም ለስኳር ህመም የሚሰጡ ፕሮግራም አፈጻጸምን ከባለድርሻዎች ጋር ምክክርና ግምገማ ማካሄድ፤

- **የዓይን ጤና ምርመራና ህክምና አገልግሎት ማጠናከርና ማስፋፋት፤**
    - የአይን ሞራ ቀዶ ህክምና ክምችትን (Cataract Backlog) ለመቀነስ ቀዶ ህክምና በዘመቻ ለመተግበር ወረዳዎችን መደገፍ፤
    - የዓይን ጤና አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል የተለያዩ አጋዥ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፤
    - የዓይን ጤና አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል የካታራክት ስረጀሪ ኦዲት ማንዋል ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሰራጨት፤
    - የሁለተኛ እና የሶስተኛ ደረጃ የዓይን ጤና ተቋማት የዓይን ጤና ላይ ለ2 ጤና ባለሞያዎች የባዮሜትሪ ስልጠና መስጠት፤
    - ለ4 የመጀመሪያ ደረጃ የዓይን ጤና ተቋማት ለተውጣጡ የአይን ጤና ባለሞያዎች IPEC ስልጠና መስጠት፤
    - በአለም ጤና ድርጅት የመጀመሪያ ደረጃ የአይን ጤና ልየታ ማንዋል መሰረት የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት (ለሁለተኛ ደረጃ እና ሶስተኛ ደረጃ ላይ ለሚሰሩ የአይን ጤና ባለሞያዎች ስልጠና መስጠት)፤
    - የዓይን አገልግሎትን ከሌሎች የህክምና አገልግሎቶች ጋር በማቀናጀት ማጠናከር እና ማስፋፋት (ከስኳር ህክምና ክሊኒክ እና ከአምስት አመት በታች ተመላላሽ ህክምና መስጫ በ1 ዓይን ጤና መስጫ ተቋም ማቀናጀት)፤
    - በትምህርት ቤት ጤና ፕሮግራም የዓይን ጤና ችግር ልየታን ማጠናከር እና ማስፋፋት (በ4 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የትምህርት ቤት የአይን ችግር ልየታ ለመተግበር ለ6 መምህራን ስልጠና መስጠት)፤
    - በመነጽር ለሚስተካከል የዓይን ጤና ችግር ላለባቸዉ ሰዎች ምርመራ መስራትና በመነጽር ማከም(ለ 4,324 የዓይን ህሙማን)፤

### 1.3.2.6 የአእምሮ የነርቭ እና የሱስ ችግር ህመም መከላከል እና መቆጣጠር

**ዒላማ**

- የአእምሮ ህመም ህክምና አቀናጅተው የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ሽፋን ከ35% ወደ 40% ማድረስ፤
- የከባድ አእምሮ ህመም (psychosis) ህክምና አገልግሎት ሽፋን ወደ 65% ማድረስ፤
- ድባቴ (Depression) የህክምና አገልግሎት ሽፋን ወደ 16% ማሳደግ፤
- ባይፖላር (Bipola cases) የህክምና አገልግሎት ሽፋን ወደ 25% ማሳደግ፤
- የአልኮል ሱስ ህክምና አገልግሎት ሽፋን (AUD) ወደ 9% ማሳደግ፤
- የሚጥል አእምሮ በሽታ (Epilepsy-GTC) የህክምና አገልግሎት ሽፋን ወደ 45% ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምዎችጃ እና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የማህበረሰብ አቀፍ የአእምሮ፣ የኒውሮሎጂ እና የሱስ ህመም መከላከል እና መቆጣጠር ስራን ማጠናከር፤**
    - በየደረጃው ባሉ የጤና መዋቅሮች ስለአዕምሮ የነርቭ እና የሱስ ችግር፣ ህመም መከላከል፣ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት ላይ የአድቮኬሲ ስራ ማካሄድ፤
    - ለአእምሮ ህመም የነርቭ እና የሱስ ችግር አጋላጭ ሁኔታዎች ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደጊያ ስራዎችን ማጠናከር፤
    - በዋና ዋና የአእምሮ፣ ህመም መከላከል እና ህክምና አገልግሎት ላይ ያተኮሩ የተግባቦት መልእክቶችን ማዘጋጀት እና ማስተላለፍ፤

- የአዕምሮ ጤና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል አጋዥ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት (ለትምህርት ቤት፣ለሃይማኖት ቦታዎች፣ እና ለትላልቅ ልማት ኮሪደር)፤
- በትምህርት ቤት ጤና ፕሮግራም የአእመሮ፣ የነርብ እና የሱስ ችግር ህመም ልየታን ማስጀመር፤
- የባለ ድርሻ አካላትን ባሳተፈ እና ምቹ ሁኔታዎችን (የዓለም አእመሮ ጤና ቀን፣ የአእምሮ ጤና ግንዛቤ ወር እና የዓለም የኢፒለፕሲ ቀንን) በመጠቀም ማህበረሰቡ ስለ አእምሮ ጤና፣ የነርብ እና የሱስ ህመም እና ጤና ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፤

▪ **የሱስ ችግር ህመምን የመከላከል እና የመቆጣጠር ትግበራን ማጠናከር፤**
    - አንድ የአእምሮ ጤና ሆስፒታሎች የአስተኝቶ ማከም የሱስ ህክምና አገልግሎት አካተው እንዲሰጡ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
    - የአእምሮ ጤና ባለሙያዎችን የስራ ላይ ስልጠና በመስጠት የሱስ ህክምና አገልግሎት ጥራትን ማሻሻል፤
    - ከ HIV-AIDS መከላከል ዘርፍ ጋር በመተባበር ለድራግ ኢንጀክሽን የሱስ ችግር ላለባቸው ሰዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ የሚሆን ማቴሪያል ማዘጋጀት፤

▪ **በጤና ስርዓት የአእምሮ እና የነርብ ህመም ህክምና እና ማገገሚያ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማጠናከር እና ማስፋፋት፤**
    - የአእምሮ ጤና አገልግሎትን በየደረጃው ባሉ ተቋማት ለማስፋፋት ከክልል እና በየደረጃው ካሉ የጤና ጽ/ቤት አመራሮች ጋር የአዲቮኬሲ የውይይት መድረክ ማካሄድ፤
    - ከጤና ሚንስተር ጋር በመተባበር በmhGAP-IG ስልጠና አዳዲስ የጤና ተቋማት የተቀናጀ የአእምሮ ጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፤ የአእምሮ ጤና ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት የሳይኮቴራፒ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፤
    - ለአእምሮ ጤና እና የሱስ ችግር ህመም ማገገሚያ ማዕከላትን ማጠናከር እና ማስፋፋት፤
    - የአእምሮ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን አቅም በማጠናከር የአእምሮ፣ የነርብ እና የሱስ ችግር ህመም ህክምና አገልግሎት ጥራትን ማሻሻል፤
    - የአዕምሮ ህመም ህክምናን ከሌሎች የማይተላለፉና የሚተላለፉ በሽታዎች ጋር የማቀናጀት ስራ ማጠናከር (ከኤች.አይ.ቪ ህክምና፣ ከካንሰር ህክምና ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፤
    - የአዕምሮ ጤና ህክምና ከሌሎች የማይተላለፉና የሚተላለፉ በሽታዎች ጋር የማቀናጀት ስራ መስራት፤
    - የጤና ባለሙያዎችን ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን የእናቶች የአእምሮ ህመም በወቅቱ የመለየት እና ሪፈር የማድረግ አቅም ማሳደግ፤
    - የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት የmhGAP-Intervention Guidline ስልጠና ለሚሰጣቸው ጤና ተቋማት የመድሃኒት እና የህክምና ግብአት ወረዳዎች እንዲያሟሉላቸው ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
    - ራስን የማጥፋት ሙከራ ላደረጉ ህሙማን የሚሰጥ የኢመርጀንሲ ህክምና አገልግሎት ከአእምሮ ህመም ህክምና ጋር በጤና ተቋማት ለማቀናጀት የሚያስችል መመሪያ ማሰራጨት፤
    - የመከላከያ ሰራዊት ጤና ተቋማት የአእምሮ ጤና አገልግሎት አቀናጅተው እንዲሰጡ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤

- **በጤና ስርዓት ጤና፣ የነርቭ እና የሱስ ችግር ህመም መከላከል እና መቆጣጠር ፕሮግራም ድጋፍ እና ክትትል ማጠናከር፤**
  - የአእምሮ ጤና ህክምና አገልግሎት እና የmhGAp ትግበራ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤
  - የክልል እና የከተማ መስተዳድር ማረሚያ ቤቶች እና የአእምሮ ጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - የአእምሮ ጤና ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ከባለ ድርሻ አካላት በተገኙበት ማካሄድ፤
  - የአእመሮ ጤና ህክምና አገልግሎቶች ላይ የመረጃ አያያዝ ጥራት እና ለውሳኔ የመጠቀም ስርዓትን ማጠናከር፤

## 1.4 የህክምና አገልግሎት መሻሻል

### 1.4.1 የህክምና አገልግሎት

**ዒላማ**

- የተመላላሽ ህክምና ተጠቃሚዎች ሽፋን ከ1.05 ወደ 1.5 ማሳደግ፤
- አልጋ የመያዝ መጠን ከ57% ወደ 65% ማሳደግ፤
- አማካይ የተኙቶ ህክምና ቆይታ ጊዜ ከ3.7 ወደ 3.5 ቀን ማውረድ፤
- የተኙቶ ታካሚዎች ሞት መጠን ከ1.3% ወደ 1.2% መቀነስ፤
- በሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራት አራተኛ ዙር(EBC) ከ58.3% ወደ 65% ማሳደግ፤
- የኢትዮጰያ የሆሰፒታሎች ሪፎርም ትግበራ (EHSTG) ከ71.6% ወደ 75% ማሳደግ፤
- በሆስፒታሎች አዲሱ ክልኒካል ኦድት ትግበራ አሁን ካለበት 4.7% ወደ 71% ማሳደግ፤
- ደህንነቱ የጠበቀ ቀዶ ህክምና አገልግሎት አጠቃቀም (SSCU) አሁን ካለበት 89.3% ወደ 95% ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ጥምረት ለጥራትን ማጠናከር፤**
  - ለአስተባባሪ ሆስፒታሎች የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤
  - የአራተኛ ዙር የማጠናቀቂያና ዕዉቅና አሰጣጥ የቫልዴሽን ግምገማ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎችን ማከናወንና የተሻለ አፈጻጸም ያላቸዉ በክልል ደረጃ እዉቅና መሰጠት፤
  - በጥምረቱ የትኩረት አጀንዳ ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀም ያላችው ሆስፒታሎች Benchmark መማማሪያ መደረክ እንዲያደረጉ ማስተባበር፤
- **የክሊኒካል አመራር ማሻሻያ ፕሮግራም እና የክሊኒካል ኦዲት ቅንጅታዊ ትግበራን ማጠናከርና ማሻሻል፤**
  - መደበኛ የሆነ ጉብኝትን ማካሄድ የተገኘ ጥሩ ተሞክሮ ላላቸዉ የልምድ ልዉዉጥ መድረክ ማዘጋጀት፤
  - የአፈጻጸም ግምገማ እና በክሊኒካል አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ውጤታማ በሆኑ የክሊኒካል ኦዲት ፕሮጀክቶች ላይ መማማሪያ መድረክ ላይ እዉቅና መሰጠት፤
  - የክሊኒካል ኦድት ስራ የውጤት ትንተና፤ስትራቴጂክ እርምጃ ማሻሻያ ማድረግና እና አዲሱን ክልኒካል ኦድት ያልጀመሩ ሆስፒታሎች ወደ ትግበራ እንድገቡ መደገፍ፤
  - የተለያዩ ባለሙያዎችን በማዋቀር በተመረጡት ሆስፒታሎች ላይ ሜንተርሽፕ ማድረግ፤

- በEHAQ መሪ ሆስፒታሎች በክሊኒካል ኦዲት ትግበራ ላይ በስራ ቦታ ላይና ከስራ ቦታ ዉጭ የስልጠና ድጋፍ ማድረግ፤

- **የተሃድሶ ህክምና አገልግሎትን ማስፋፋትና ማጠናከር፤**
  - የተሀድሶ ህክምና ዙሪያ በአመራርና ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
  - የተሀድሶ ህክምና አገልግሎትና አጋዥ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማካሄድ፤
  - በተሀድሶ ህክምና ዙሪያ የመገናኛ ብዙሀን መልዕክቶችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤
  - ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የተሀድሶ ህክምና እና የመጀመሪያ አሀድ የጤና አገልግሎት ቅንጅታዊ አሰራር መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፤
  - ለተሀድሶ ህክምና ማዕከላት/ሆስፒታል ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ፤

- **የስፔሻሊቲ ህክምና አገልግሎት ፍኖተ-ካርታ ትግበራን ማጠናከር፤**
  - ሆስፒታሎች እንደየሆስፒታል ደረጃ የእንክብካቤ አገልግሎት OPD/IPD/ED ስፔሻሊቲ ህክምና አገልግሎቶች እንዲሰጡ ማስተባበር፤
  - ሆስፒታሎች እንደ የሆስፒታል ደረጃ ስታንዳርድ አስፈላጊ መሠረተ ልማት እና ስፔሻሊቲ ህክምና ባለሙያዎችን እንዲያሟሉ መደገፍ፤
  - በዩኒቨርስቲ ሆስፒታል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን፣ ምርምሮችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የፍጆታ ዕቃዎችን ላይ እንዲመራመሩ እና እንዲያመርቱ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤
  - የስፔሻሊቲ ህክምና ባለሙያዎችን በብቃት ለመጠቀም የተቋቋመ የM&E ፍሬምወርክ እንዲኖር መደገፍ፤

- **የማስታገሻ ህክምና እና የካንሰር ህክምና አገልግሎት ማስፋፋት እና ማጠናከር፤**
  - የማስታገሻ ህክምና /Palliative care/ አገልግሎት በ 1 ተቋም ማስጀመር፤
  - የቤት ለቤት ማስታገሻ ህክምና /Palliative care/ አገልግሎት በ1 ተቋም ማስጀመር፤
  - የማስታገሻ ህክምና አገልግሎት በ1 ጤና ጣቢያ ማስጀመር፤
  - በሁሉም ሆስፒታሎች የህመም ስቃይ ማስታገስ/Pain management አገልግሎት እንዲሰጥ መደገፍ፤
  - ለህመም ማስታገሻ አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን/ኦፒዮይድስ አቅርቦትን ሆስፒታሎች ለማሻሻል ድጋፍ ማድረግ፤
  - የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የካንሰር ህክምና አገልግሎት ማስጀመርና ማጠናከር፤

- **የኢትዮጵያ ሆስፒታል ሪፎርም እና መረጃ አያያዝን ማጠናከር፤**
  - የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያዉን ትግበራ ማከናወን፤
  - የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያ አፈጻጸም መከታተያ ዳታቤዝ ለክልል ጤና ቢሮ ባለሙያዎችና ለሆስፒታሎች ማስተዋወቅ፤
  - የሆስፒታል አገልግሎት ማሻሻያ መመሪያዉን ከፌደራል በሚሰጠን ኮታ መሰረት ለሆስፒታሎች ማሰራጨት፤
  - የቁልፍ አፈፃፀም መለኪያ አተገባበር መመሪያ ከክልልና ከሆስፒታሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራዎች ማከናወን፤
  - በሪፎርምና መረጃ አያያዝ ላይ በአስተባባሪ ሆስፒታሎች ድጋፋዊ ጉብኝት ማድረግና ግብረ-መልስ መሰጠት፤

- የሆስፒታሎች ቁልፍ አፈጻጸም መለኪያ DHIS2 ቴክኖሎጅን በመጠቀም በየወሩ መረጃ መተንተንና ዉሳኔ መሰጠት፤

- **በአገር አቀፍ ደረጃ የI-CARE Program ትግበራን እና ውጤታማነቱን ማጠናከር፤**
  - ከሆስፒታሎች ለተውጣጡ ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች በህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ማሻሻያ ስልቶች እና የተቀናጀ ዘላቂ ተቋማዊ ለውጥ አስተዳደር ስልጠና መስጠት፤
  - የህክምና አገልግሎት መረጃ አያያዝ፣ ትንተና እና አጠቃቀም ዙሪያ ላይ የተጠና ችግር ፈቺ የቴክኒክ፣ ዝቅተኛ አፈፃፀም ላላቸው ሆስፒታሎች ድጋፍ ማድረግ፤
  - ቅንጅታዊ አሰራርን፣የልምድ ልውውጦችን እንዲሁም ውስን የሆኑ ሃብቶችን በጋራ የመጠቀም እና የማልማት ሥራዎችን በቴክኒክ መደገፍ፤
  - በክልል ደረጃ ስኬታማ የሆነ ስራዎች ለመስራት እንዲተገበር ከለጋሽ ድርጅቶች በቂ የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፎችን ማሰባሰብ፤
- **የዲያግኖስቲክ አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት ማሻሻል፤**
  - የኢሜጅንግና የፓቶሎጂ ላብራቶሪ ከህክምና ጥራት አኳያ ያለው አስተዋጾኦ ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤
  - የኢሜጅንግና የፓቶሎጂ ላብራቶሪ አተገባበር መመሪያዎችን ማስራጨት፤
  - የኢሜጅንግ እና የፓቶሎጂ ላብራቶሪ አገልግሎትን ስርዓት ዝርጋታና ጥራት ማሻሻያ ስልጠና መስጠት፤
  - የኢሜጅንግ እና የፓቶሎጂ ላብራቶሪ አገልግሎት ማሻሻያ ላይ የሜንተርሽፕ ማካሄድ፤
- **የሜድካል ኦክስጅን አገልግሎት ማሻሻል፤**
  - ኦክሰጅን አገልግሎት አሰጣጥ ያለዉን አስተዋጾኦ ላይ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስልጠና መሰጠት፤
  - የሆስፒታሎች ሜድካል ኦክስጅን አጠቃቀም ላይ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፤

### 1.4.2 የድንገተኛ ሕመም፣ የአካል ጉዳት አዳጋ እና ጽኑ ህክምና አገልግሎቶች

**ዒላማ**

- የአንቡላንስ አገልግሎት ያገኙ ከ80% ወደ 90% ማሳደግ፤
- የድንገተኛ ሞት ምጣኔ ከ0.23% ወደ 0.15% መቀነስ፤
- የፅኑ ህክምና ሞት ምጣኔ ከ26.7% ወደ 20% መቀነስ፤
- ድንገተኛ ክፍል ከ24 ሰዓት በላይ የሚቆዩ ህሙማን ከ12.4% ወደ 5% ማዉረድ፤
- የሶስተኛ ወገን አገልግሎት የሚሰጡ ሆስፒታሎች አሁን ካለበት ከ42.8% ወደ 100% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በድንገተኛ እና ጽኑ ህክምና የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር፤**
  - የማህበረሰብን የድንገተኛ ህክምና የአጥቢያ ስኮድን ማቋቋም፤
  - የማህበረሰብ የድንገተኛ አደጋ እስኳድ የስራ ግምገማ ማካሄድ፤
  - የተማሪዎች የድንገተኛ ህክምና ቡድን/መማክርት ማቋቋም፤
  - የተዘጋጅውን የማህበረሰብ የድንገተኛ ስኮድን ዶክመንት ማስራጨት፤
  - የድንገተኛ ህክምና መስጫ ክፍሉን ዝግጅት ላይ ድጋፍና ክትትል ማካሄድ፤
- **የቅድመ ጤና ተቋም እና የህሙማን ቅብብሎሽ አገልግሎትን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
  - ለወረዳዎችና ሆስፒታሎች ለሚደረገው የአንቡላንስ ውስጣዊ ይዞት ማሻሻልና ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት፤

- ለአንቡላንስ ባለሙያዎች (BLS እና ATLS) ስልጠና መስጠት፤
- የጥሪ አያያዝ እና ኮሚኒኬሽን ፕሮቶኮል አሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤
- የቅድመ ጤና ተቋም የማህበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴ በይፋ ማስተዋወቅ እና ትግበራውን መከታተል፤
- የአንቡላንስ ጥሪ እና ስምሪት ማዕከል በቴክኖሎጂ ማደራጀት፤
- የማህበረሰብ የመጀመርያ ደረጃ ህክምና እርዳታ (CFAR) ስልጠና መስጠት፤
- በተመረጡ የድንገተኛ አደጋዎች ላይ ማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ ማካሄድ፤
- ከወረዳ ጤ/ጽ/ቤት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የአንቡላንስ አጠቃቀም ላይ ንቅናቄ መድረክ ማዘጋጀት፤
- የአንቡላንስ መመሪያውን መሰረት በማድረግ ማህበረሰቡን ያካተተ የክትትል ዘዴ ማበጀት፤
- የአንቡላንስ አገልግሎት ላይ የተቀመጡትን ጠቋሚዎች መረጃ አሰባሰብ ማሻሻል፤
- አዲስ ተሻሽሎ በወጣው የህሙማን ቅብብሎሽ መመሪያ ላይ እና በበይነመረብ ላይ ለላይዘን ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤

- **የድንገተኛና ጽኑ ህክምና አገልግሎትን ማጠናከር፤**
  - በሆስፒታሎች የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ላይ ዳሰሳ ማካሄድና በተለዩ ክፍተቶች ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤
  - የመሰረታዊ ድንገተኛ ህክምና እና ቱሊ ክቲ (BEC training & toolkits) በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
  - ED QI ትግበራን በተጀመረባቸዉ ሆስፒታሎች ላይ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
  - በድንገተኛ ህክምና ፕሮቶኮል (Emergency treatment protocol) ላይ ከተመረጡ ሆስፒታሎች ለተወጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
  - በተመረጡ ተቋማት ላይ ለሚገኙ ባለሙያዎች የተግባር ላይ ስልጠና መስጠት፤
  - አዲስ ለሚቋቋሙ የጽኑ ህክምና ተቋማት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን መስራት፤
  - ለነባርና አዳዲስ የፅኑ ህሙማን ህክምና አገልግሎት ለሚሰጡ ሆስፒታሎች በተግባር ላይ ሜንተርሺፕ እና ኮቺንግ ማከናወን ፤
  - የፅኑ ህክምና የሚሰጡ ሆስፒታሎችን በHub and Spoke Model ማስተሳሰር፤
  - የሞት ምጣኔ ከፍተኛ በሆነባቸው ሆስፒታሎች ላይ በተለዩ ክፍተቶች መሰረት የጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት መስራት፤
  - ከመድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ስራ አስፈፃሚ ጋር በመሆን የፅኑ ህክምና እቃዎች የጥገና ዘመቻ ማካሄድ፤

- **የአደጋ መከላከልና ህክምና አገልግሎትን ማጠናከር፤**
  - ለአደጋ መከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር አጋርነትን መፍጠር፤
  - አደጋ መከላከል ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፤
  - Trauma care training ከሆስፒታሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች መስጠት፤
  - ከአደጋ ጋር የተያያዘ የጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት በሆስፒታሎች ማስተግበር፤
  - የአደጋ ህክምና መዝገብን በተመረጡ ሆስፒታሎች ማስተግበር፤
  - የአደጋ ህክምና መዝገብ በሚተገብሩ ተቋማቶች ላይ ግንዛቤ እንዲጨምር ማድረግ፤
  - ከፖሊስ ከመድን ፈንድና ከሆስፒታሎች የሚመጡ የአደጋ መረጃ ስርዓትን ወጥ ማድረግ፤
  - ለቃጠሎ ህክምና ለባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
  - በሀዋሳ ዩንቨርስቲ ሆስፒታል የቃጠሎ ህክምና ዩኒት በሆስፒታል ማቋቋም፤

- የጥሪ ማዕከሉን ለህብረተሰቡ እንዲተዋወቅ ማድረግ፤
- ከሆስፒታሎችና ከወረዳ የተዉጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ ህክምና አገልግሎት የጀመሩ ጤና ተቋማት ተግባራዊነት መከታተል፤
- የተቀላጠፈ የትራፊክ ተጎጅዎች የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ተቋማዊ አሰራር ስርዓትን በክልላችን ባሉ ተቋማት ማስተዋወቅ፤
- በክልል ደረጃ የአስቸኳይ ህክምና ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት፤

- **የዋና ዋና ከተሞች የድንገተኛ አደጋና የፅኑ ህክምና አገልግሎት ማሻሻያ ፕሮጀክት ትግበራን ማጠናከር፤**
  - በክልሉ ከተማ የተጀመረዉን ስራ የፕሮግራም አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተግባራዊነት መከታተል፤
- **የጅምላ አደጋዎች ዝግጁነትና ምላሽን ማጠናከር፤**
  - ክልል ጤና ቢሮ እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሁሉን አቀፍ ተጋላጭነት በመለየት የወረርሽኝ የጅምላ አደጋ እና ድንገተኛ አደጋ ምላሽ እቅድ ማዘጋጀት፤
  - የተዘጋጀውን የድንገተኛ ዝግጁነት እና ምላሽ እቅድ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ፤
  - ለጅምላ አደጋ ህክምና ከሆስፒታሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣
  - በሆስፒታሎች የጅምላ አደጋ ህክምናን ለማሻሻል አደጋ ለሚበዛባቸው ለተመረጡ ሆስፒታሎች ለሚገኙ ድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በመስክ የተደገፈ ስልጠና መስጠት፤
  - በተመረጡ ሆስፒታሎች የጅምላ አደጋ እቅድ ምላሽ ላይ የተግባር ፍተሻ ድጋፍ ማድረግ፤
  - በክልላዊ ደረጃ ለሚከናወኑ ህዝባዊ ትይንቶች እና ክብረ በዓላት ላይ የድንገተኛ ምላሽ መስጠት፤
  - በክልላዊ የጅምላ አደጋ ህክምና ቡድን የመስክ ልምምድ ማድረግ፤

### 1.4.3 የጤና ስርአት ኢኖቬሽን፤ ጥራት፤ ፍትሃዊነትን እና አመራርን ማሻሻል፡

**ዒላማ**

- የህሙማን ዕርካታ መጠን ከ81% ወደ 82% ማሳደግ፤
- የተኝቶ ታካሚዎች ሞት ምጣኔ ከ1.3% ወደ 1.2% መቀነስ፤
- የሆስፒታል አመራር እና አስተዳደር ስኮር ከ75% ወደ 80% ማሳደግ
- የCASH ኦዲት ስኮር ከ82% ወደ 84% ማሳደግ፤
- አዲሱ ክሊኒካል ኦዲት በመስራት የጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የሰሩ ሆስፒታሎች አሁን ካለበት 4.7% ወደ 50% ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የጤና ጥራት እና ፍትሃዊነት መረጃ አያያዝ እና የእዉቀት ሽግግር ማጠናከር፤**
  - የጤና ጥራት እና ፍትሃዊነት ስትራተጂ አፈጻጸም መሪ ኮሚቴ በአዲስ መልክ ማዋቀር፤
  - የጤና ክብካቤ ጥራት እና ደህንነት የግማሽ አመት የስራ አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ፤

- የተመረጡ መለኪያዎችን በመለየት ለሆስፒታሎች በየሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ግምገማ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙን መከታተል፤
- የጤና ክብካቤ ጥራት እና ደህንነት ጉባኤ ማዘጋጀት፤

- **ተደራሽነትን ባገናዘበ መልኩ የጥራት እና ደህንነት ማዕከላትን መፍጠር የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - ተቋማዊ ሞትን ግምገማ ለጥራት ማሻሻል በመጠቀምን ሥርዓትን በ5ቱ አጠቃላይና 1 ሪፈራል ሆስፒታል ተግባራዊ ማድረግ፤
  - በክልሉ ያሉ ሆስፒታሎች ጥራት እና ደህንነት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ማደረግ፤
- **የጤና ጥራት እና ደህንነት ልኬትን ማሻሻል**
  - በጥራት እና ደህንንት የተቃኙ መለኪያዎችን ትግበራ ሰነድ ማሰራጨት፤
  - በጥራት እና ደህንነት የመማማሪያ መድረኮችን ማዘጋጀትና ዉጤት ላመጡ ተቋማት የእዉቅና ሽልማት መሰጠት፤.
- **የጤና ክብካቤ ደህንነትን ማጠናከር**
  - የዓለም የህሙማን ደህንነት ቀን ማክበር፤
  - የጤና ክብካቤ ደህንነት ማሻሻያ በተመረጡ 10 ሆስፒታሎች ስልጠና መስጠት፤
  - SBFR በሚተገብሩ ሆስፒታሎች የቀዶ ህክምና አገልግሎት እና በሌሎች ትኩረት በሚሹ ክፍሎች ደህንነትን ለማስጠበቅ ክትትል ማድረግ፤
- **የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር ተግባራት ማጠናከር፤**
  - የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር እቅድና ግምገማ በማጠናከር በSBFR ሆስፒታሎች  በIPC FLAT በመጠቀም በቦታዉ ላይ ድጋፍ መስጠት፤
  - የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር ዙሪያ በጤና ተቋማት የሚተገበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በማዘጋጀት ለተቋማት ማሰራጨት፤
  - የተከለሰዉን የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር ማንዋል (Reference manual) ሶፍት ኮፒ ለሁሉም  ጤና ተቋማት ማሰራጨት፤
  - ኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር የጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ በSBFR በታቀፉ ተቋማት ሜንተር ማድረግ፤
  - በጤና ተቋማት የሚከሰቱ ኢንፌክሽን የቅኝት ስርአት መመርያ (HAI's Surveillance guideline) ማሰራጨት፤
  - በኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር ትኩረት ያደረገ አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ማድረግ፤
  - የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር የልህቀት ማዕከላትን በ2ቱ መማማሪያ ሆስፒታሎች ማስጀመር፤

- ለተመረጡ የኢንፌክሽን መከላከል እና መቆጣጠር ተግባራት ስታንዳርዶችን እና የኦዲት ቱሎችን (SOPs and Audit tools) ማሰራጨትና ክትትል ማድረግ፤

- **በሁሉም የጤና አገልግሎት ሥርዓት ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፤**
  - ክልላዊ የጤና ፍትሀዊነት ስትራቴጂ ላይ ከፍተኛ የአድቮኬሲ ስራ ማካሄድና ትግበራ መከታተል፤
  - በሁሉም ወረዳዎች ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘባ የጤና ፍትሃዊ ስትራቴጂ ዝግጅት ላይ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
- **በጤና ፍትሀዊነት ትንተና መሳሪያ (HEAT & HEAT PLUS) ማስጀመር**
  - የጤና ፍትሀዊነት ትንተና መሳሪያ(HEAT & HEAT PLUS) ለባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- **መረጃ ላይ የተመሰረተ ብሄራዊ የጤና ፍትሀዊነት ስርዓት ማጠናከር፤**
  - በክልል አቀፍ ደረጃ የጤና ፍትሀዊነት ጉባኤ ማካሄድ፤
  - የጤና ፍትሃዊነት እና አመራር አፈጻጸም ዓመታዊ ግምገማ ማካሄድ፤
  - በወረዳዎች ዝቅተኛ አፈፃፀም ባላቸው ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- **ተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ (Mobile Health Team Service) ተደራሽነትን ማሻሻል፤**
  - ተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎት (Mobile Health Team Service) የአተገባበር መመሪያ በክልል ደረጃ ማስተዋወቅ፤
  - ለተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎት(Mobile Health team Service) በፕሮቶኮል መሰረት መተግበር፤
- **የጤና ኢ-ፍትሃዊነትን ለማጥበብ ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል፤**
  - ጤና ኢ-ፍትሃዊነትን ለማጥበብ ከሌሎች ሲክተሮች ጋር በመቀናጀት የሪዚሊየንስ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- **በመረጃ ላይ የተመሰረት የጤና ቁጥጥር ስርዐት የማሻሻያ ትግበራን ማጠናከር፤**
  - የጤና ቁጥጥር ስርዓት የረጅም ጊዜ ዉጤት ግምገማ(impact assesement) ማካሄድ፤
  - በመረጃ ላይ የተመሰረት የጤና ቁጥጥር ስርዓት የማሻሻያ ትግበራን ማጠናከር፤
  - የህክምና መሳሪያ የጥገና እና አስተዳደር ስርዓትን ማጠናከር፤
- **በመረጃ ላይ የተመሰረተ የህክምና አገልግሎት ስርዓትን ማጠናከር፤**
  - ለSBFR ሆስፒታሎችን የተከለሰው የሆስፒታል ክሊኒካል ኦዲት ቱሎች ማስተዋውቅና ወደ ትግበራ ማስገባት፤
  - SBFR በሚተገብሩ ጤና ጣቢያዎች ላይ የክለኒካል ኦዲት ትግበራ ማስጀመር፤

- በተከለሰዉ ክሊኒካል ኦዲት መመሪያ ጤና ጣቢያዎችን ማስጀመር እና ለሚጀምሩ ተቋማት የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፤

- **የጤና ስርዐት ኢኖቬሽን ላብ ማቋቋም እና ስራ ማስጀመር፤**
  - የኢኖቬሽን ከፍተኛ የቴክኒክ ቲንክ ታንክ ቡድን ማቋቋም፤
  - የኢኖቬሽን ጋይድ ላይን በክልል ደረጃ መተግበር፤
  - የጤና ኢኖቬሽን ላብ ማቋቋም እና መተዳዳሪያ መመሪያ ማዘጋጀት፤
  - በጥናት በተለዩ ስትራተጂክ ጉዳዮች ላይ የጤና ኢኖቬሽን ላብ ስራ ማስጀመር፤
- **ክልል አቀፍ የሜዲካል ቱሪዝም መዳረሻ ፕሮጀክት መቅረፅ እና መተግበር**
  - በተመረጠ 1 የመንግሥት ሆስፒታል የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ መደገፍ፤
  - የሜድካል ቱሪዝም መዳረሻ የክትትል እና ድጋፍ ስራዎችን መተግበር፤

- **በተመረጡ 3 ሆስፒታሎች የሥርዓት ማነቆዎች ላይ ያተኮረ (SBFR) የሙከራ ሪፎርም መተግበር፤**
  - የሥርዓት ማነቆች ላይ ያተኮረ (SBFR) የሙከራ ሪፎርም ትግበራ ወደ 6 ሆስፒታሎች ማሳደግ፤
  - የሆስፒታሎች ሁለተኛ ዙር የትግበራ ዕቅድ መተግበር፤
  - የክትትል እና ድጋፍ ሰራዎችን ማከናወን፤
  - የቦታ ላይ የእርስበርስ የተግባር ልምድ ልውውጥና መማማሪያ (Onsite Collaborative Experiential learning) ፕሮግራሞችን መተግበር፤
  - የተቋማት የድንገተኛ ምልከታ ማድረግ፤
  - በየሩብ አመቱ የግምገማ መድረክ ማዘጋጀት፤
  - የSBFR አፈጻጸም ኦዲት ቱል መተግበር፤
  - ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸዉን ተቋማት በምዘና በመለየት እና እውቅና መስጠት፤
  - ክልላዊ የሲኒየር ፎርም ማዘጋጀት፤
- **በመጀመሪያ አሀድ ተቋማት የሥርዓት ማነቆዎች ላይ ያተኮረ (SBFR) የሙከራ ሪፎርም መተግበር፤**
  - የሙከራ ትግበራ በ16 ተመጣጣኝ ልማት በሚሹ ክልሎች እና በ15 በሌሎች ክልሎች በተመረጡ ወረዳወች መተግበር፤
  - በተመረጡት የጤና ተቋማትን የሙከራ ትግበራዉን ማስጀመር፤
  - SBFR በሚተገበሩ ሆስጤና ጣቢያ፤ ጤና ኬላ የመጀመሪያ አሀድ ጤና በተመረጡ ተቋማት የክትትልና ደጋፍ ስራ ማካሄድ፤
  - ሀገር አቀፍ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ ማዘጋጀት፤
- **በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ SBFR መተግበር**
  - በክልል ጤና ቢሮ የሥርዓት ማነቆችን በጥናት መለየት፤

- የሪፎርሙን ሰነድና የክትትል እና ግምገማ ፍሬም ወርክሾ ማዘጋጀት፤
- የሪፎርሙን ትግበራ ማስጀመር፤
- የክትትል እና ድጋፍ ስራ ማከናወን፤

- **በመንግስት ሆስፒታሎች ሥር የሚቋቋም ኢኖቬቲቭ የክሊኒካል አገልግሎት የግል ህክምና ማዕከል ማስጀመር፤**
  - በመንግስት ሆስፒታሎች ሥር የሚቋቋም የግል ማዕከል አዋጪነት ጥናት ማከሄድ፤
  - በዉጤት ላይ የተመሰረተ የፋይናንስ ስርዓት ለመዘርጋት እና የማበረታቻ ስልት ለመፍጠር ድጋፍ ማድረግ፤
- **ውጤታማ የጤና አመራርና አስተዳደርን** (High Impact Leadership Improvement Program(HiLIP) **ማጠናከር፤**
  - የጤና ተቋማት የስራ አመራር ቦርድ መመሪያን የተከለሰዉን ማስራጨት፤
  - የጤና ተቋማት የስራ አመራር ቦርድ ማትጊያ ፓኬጅ ማዘጋጀት ማሰራጨት ትግባራዊነቱን መከታተል፤
- **የክሊኒካል አመራር ማሻሻያ ፕሮግራም** (CLIP)**ን ማጠናከር፤**
  - የክሊኒካል አመራር ማሻሻያ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ ማከሄድ፤
  - የክሊኒካል አመራር ማሻሻያ የሜንተርሽፕ ድጋፍ ማካሄድ፤
  - የክሊኒካል አመራር ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የመረጃ ቋት እንድያሰገቡ ማድረግ፤
- **አመራር እና አስተዳደርን** (LMG-LIP) **ማሻሻል**
  - የአመራር እና አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ ማከሄድ፤
  - በተመረጡ ወረዳዎች የአመራር ተጠያቂነት ፕሮግራም (MAPS) በየደረጃው ላሉ ሓላፊዎች ስልጠና በመስጠት ትግበራውን ማስጀመር፤
  - ቀድመው የአመራር ተጠያቂነት ፕሮግራም ትግበራ የጀመሩ ወረዳዎችን መደገፍና የክትትል ስራ መስራት፤
  - የተዘጋጀውን የጤናው ዘርፍ የማህበረሰብ ተጠያቂነት ስትራቴጂ በማስተዋወቅ ወደስራ ማስገባት፤
  - በጥራት እና ደህንነት ላይ የአመራሩን አቅም መገንባት፤
- **ሴቶችን ወደ አመራርነት እንዲመጡ ማስቻል፤**
  - የሴቶችን አመራርነት ፕሮግራም ዳሳሳ ጥናት ማካሄድ፤
  - የሴቶችን አመራርነት ፕሮግራም ሰነድ ማዘጋጀት እና መተግበር፤

### 1.4.4 የላቦራቶሪ ህክምና እና ሌሎች ዳያግኖስቲክ አገልግሎቶችን ጥራት ማሻሻል

**ዒላማ**

- የISO ስታንዳርድ (ISO 15189 or 17025) እውቅና ያገኘ 1 የሆስፒታል ላቦራቶሪ መፈጠር፤
- በሆስታሎች ደረጃ SLIPTA ደረጃ 3 የደረሱ ሆስፒታሎችን 5 ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የላቦራቶሪዎችን መሰረታዊ የላብራቶሪ ጥራት ማሻሻያ ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - የላቦራቶሪዎችን የጥራት ደረጃ ማሻሻል (SLIPTA) ፕሮግራም ስራዎች ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - የላብራቶሪ መሰረተ ልማት አቅርቦት ማሻሻል እንዲሁም በብሄራዊ ደረጃ ባዮሴኩሪቲ እና ባዮሴፍቲ አቅምን ማሳደግ፣
    - መሰረታዊ የላቦራቶሪ ጥራት ስራ አመራር መዘርጋት፤
    - ላቦራቶሪዎች የISO 15189 እና/ወይም የ17025 እውቅና እንዲያገኙ ማስቻል፤
    - ክልላዊ ብቃት መመርመሪያ/ውጫዊ የጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን ድጋፍ ማድረግ፤
    - የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከርና የአቅም ግንባታ ስራን መስራት፤
    - የክሊኒካል ኬሚስትሪ ላቦራቶሪ ምርመራዎች በISO የጥራት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማስቻል፤
- **የላቦራቶሪ አገልግሎት ስራዎች ማጠናከርና ማስፋት፤**
    - ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ የላቦራቶሪ ምርመራ እንድሰጡ ክትትል ማድረግ፤
    - የላቦራቶሪ አገልግሎት የጥራት አስተዳደር ሥርዓት መተግበር፤
    - የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ አወጋገድ ለማሻሻል ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- **መሠረታዊ ዲያግኖስቲክ አገልግሎት እና የናሙና ቅብብሎሽ ግንኙነትን ማጠናከር፤**
    - የናሙና ቅብብሎሽ ግንኙነትን እና መጠባባቂያ አገልግሎቶችን የማሻሻል ስራ መስራት፤
    - የላቦራቶሪ ቴክኖሎጂን እና የናሙና ምራመራ ግብዓቶች ለመመዘንና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ አቅም ማጠናከር፤

### 1.4.5 የደም ባንክ አገልግሎት

**ዒላማ፤**

- ከበጎ ፍቃደኛ የሚሰበሰበውን የደም ልገሳ አሁን ካለበት 7113(80%) ዩኒት ወደ 8818 ማሳደግ፤
- የደም ተዋፅኦ ዝግጅት ከ11% ወደ 27% ማሳደግ፤
- ድህረ ደም ልገሳ ምክር አገልግሎት ከ3% ወደ 10% ማሳደግ፤
- ደም ተጠቃሚዎች እርካታ አሁን ካለበት ከ68% ወደ 70% ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **ከበጎ ፈቃደኞች የሚሰበሰበውን ደም ለማሳደግ የማህበረሰብ ቅስቀሳ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - ለግንዛቤ ማስጨመጫ የሚረዱ ማቴሪያሎች ማዘጋጀት፤
    - የተዘጋጁ ማቴሪያሎች የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለህብረተሰብ እንዲደርስ ማድረግ፤
    - የማህበረሰብ ቅስቀሳ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤

- በሚፈጠረው ግንዘቤ መሰረት ሕብረሰተሰቡ የበኩሉ ድርሻ ማድረጉን ማረጋገጥ፤

- **የደግ ልግሳ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ለሟሟላት የሚያስችሉ ስራዎች እና የአገልግሎት ትብብርን ስርዓትን ማጠናከር፤**
  - የደም ለጋሾችን ምልመላ ምዝገባ፣ አያያዝ ማዘመን፤
  - የደም ትራንስፊውዥን አገልግሎት ትብብርን ስርዓት ማጠናከር፤
  - በደም ማስተላለፍ ወቅት ሊተላለፉ ለሚችሉ ተህዋሲያን የመለየት ስራ መስራት፤
  - የደም ዓይነት እና ተስማሚነትን ለመወሰን ምርመራ ማካሄድ፤
  - የደም ተዋጽዖ ዝግጅት እና የትራንስፖርት ስርዓትን በተገቢው መንገድ ማከናወን፣
  - ከደም ማሰባሰብ እስከ ደም ጥቅም ላይ እስኪውል ባለው ሂደት አስፈላጊ ክትተል ማድረግ፤
  - የደም አገልግሎት ጥራት የማረጋገጥ ስራ መስራት፤

## 1.5 ሀይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎት

**ዒላማ**

- ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን ከ40% ወደ 53% ማሳደግ፤
- መሰረታዊ የሳኒቴሽን መገልገያ ያላቸዉ ቤተሰቦች ሽፋን ከ38% ወደ 50% ማሳደግ፤
- መሰረታዊ የእጅ መታጠቢያ ፋሲሊቲ ያላቸው ቤተሰቦች ሽፋን ከ8% ወደ 31% ማሳደግ፤
- ከመኖሪያ ክፍል የተለየ የማብሰያ ክፍል ያላቸው ቤተሰቦች ሽፋን ከ23% ወደ 26% ማሳደግ፤
- ከመኖሪያ ክፍል የተለየ የእንስሳት መኖሪያ ያላቸው ቤተሰቦች ሽፋን ወደ 26 % ማሳደግ፤
- ጭስ አልባ ምድጃ የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ሽፋን ወደ ከ6.9% ወደ 15% ማሳደግ፤
- የደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ ቤተሰቦች ሽፋን 32% ወደ 50% ማሳደግ፤
- የፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ ቤተሰቦች ሽፋን ከ11% ወደ 30% ማሳደግ፤
- ውሀን በአግባቡ አክመው የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ሽፋን ወደ 20% ማሳደግ፤
- የውሀ አገልግሎት የተሟላላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን ወደ ከ25% ወደ 40% ማሳደግ፤
- መሰረታዊ የሳኒቴሽን ፋሲሊቲ የተሟላላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን ከ85% ወደ 90% ማሳደግ፤
- መሰረታዊ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ያላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን ከ64% ወደ 70% ማሳደግ፤
- የውሀ ጥራት ክትትል እና ቅኝት የሚተገበርባቸው የውሀ መገኛዎች ሽፋን ወደ 20% ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የእጅ፤ የፊት እና የአፍ እና የወር አበባ ንጽህና የአጠባበቅ ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የእጅ ንጽህና ግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶች በብዙሀን እና ማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤
  - የፊት እና አፍ ንጽህና የግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶችን በብዙሀን እና ማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤
  - ሀገር አቀፍ የእጅ መታጠብ ቀንን በክልል ደረጃ በማክበር የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፤
  - በት/ቤቶች የወር አበባ ንጽህና አገልግሎት መስጫ እንዲኖር መደገፍ፤
  - የወር አበባ ንጽህና ግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶችን በብዙሀን እና ማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤

- የፊት እና አፍ ንጽህና አጠባበቅ ስልጠና መስጠት፤

- **የሳኒቴሽን ግብይት ማዕከላትን ማስፋፋት እና የሀይጅንና ሳኒቴሽን ፋይናንሲንግ ትግበራ ማጠናከር፤**
  - በዋን ዋሽ በጀት ድጋፍ የሚደረግላቸዉ ወረዳዎች ውስጥ ሳኒቴሽን ግብይት ማዕከላትን ማቋቋም፤
  - በሳኒቴሽን ግብይት ማዕከላት አዳዲስ ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ እና ማቅረብ ስራዎችን ማጠናከር፤
  - ግብይት ማእከላት በሌላቸው ወረዳዎች ሳኒቴሽን ግብይት ላይ ስልጠና መስጠት፤
  - ግብይት ማእከላት በሌላቸው ወረዳዎች የበጀት ድጋፍ ማድረግ፤
  - በቤተሰብ ደረጃና ሳኒቴሽን ግብይት ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አማራጮች ብድር እንዲያገኙ የአድቮኬሲ ስራ መስራት፤

- **ሜዳ ላይ መጸዳዳትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች ማጎልበት፤**
  - ቀበሌዎችን ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ ለማድረግ የንቅናቄ ስራዎች እንዲሰሩ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
  - የመጀመሪያ ደረጃ ODF የሆኑ ቀበሌያት ሁለተኛ ደረጃ ODF እንዲሆኑ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
  - በዋን ዋሽ እና ኮዋሽ ፕሮግራሞች የሚደገፉ ወረዳዎች ቀበሌያት ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ እንዲሆኑ የንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን፤
  - ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎችን ወደ ኃላ እንዳይመለሱ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
  - ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎችን ወደ ኃላ የተመለሱትን መልሶ ነጻ የማድረግ ስራዎችን ማከናወን፤

- **የፅዱ ኢትዮጵያ ፕሮግራሞን የመምራት እና የማስተባበር ስራዎች ማሻሻልና ማጠናከር፤**
  - የጽዱ ኢትዮጵያ ፕሮግራምን ማስጀመርና መዋቅር መዘርጋት፤
  - በሁሉም ክልሎች ማስታወቅያ መድረክ እንዲካሄድ መደገፍ፤
  - የጽዱ ኢትዮጵያ ዘመቻ ፕሮግራም አተገባበር ማኑዋል ማጠናቀቅ፤
  - የጽዱ ኢትዮጵያ ዘመቻ ላይ አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ስልጠናዎችን መስጠት፤
  - በፕሮግራሙ የአዲቮከሲ መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠት፤

- **የከተማ ሳኒቴሽንን ስራዎች፤ የውሀ እና የምግብ ደህንነት፤ ንጽህ፤ አያያዝ እንዲሁም የአጠባበቅ ትግበራን ማጠናከር፤**
  - የቤት ዉስጥ የዉሃ አያያዝና ህክምና የተግባቦት መርጃ መሳሪያዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማዘጋጀት እና ማሰራጨት፤
  - የቤት ዉስጥ የዉሃ አያያዝና ህክምና ግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶችን ማዘጋጀት እና በብዙሀን እና ማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤
  - በከተሞች የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻዎች አሰባሰብ እና አወጋገድ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት ስራን ማጠናከር፤
  - የምግብ ንጽህና ግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶችን ማዘጋጀት እና በብዙሀን እና ማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት፤
  - በሁሉም ከተሞች የከተማ ሳኒቴሽንና ሐይጅን ስራዎችን እንዲሰራ ጥረት ማድረግ፤
  - የህዝብና የጋራ መጸዳጃ ቤቶች መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠት፤

- በከተሞች በዋን ዋሽ ፕሮግራም የህዝብና የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ መከታተል፤
- ለወረዳ ባለሙያዎች የዉሃ ጥራት ክትትል ስልጠና መስጠት፤

- **የተቋማት እና በጤና ተቋማት የዉሃ፣ ሃይጅንና ሳኒቴሽን (WASH) ትግበራን ማስፋፋትና ማጠናከር፤**
    - የተዘጋጀው WASH FIT ቱል በተመረጡ ጤና ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ፤
    - በማረሚያ ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት እና በጤና ተቋማት የሃይጅንና አከባቢ ጤና አጠባበቅ መመሪያን ተግባራዊ ለማድረግ ስልጠናዎችን መስጠት፤
    - ለማረሚያ ቤት እና ሃይማኖት ተቋማት የተዘጋጀውን መመሪያ ተፈፃሚነት ከባለድርሻ አካላት ጋር የድጋፍና ክትትል ስራዎችን መስራት፤
    - በዋን ዋሽ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች የሚሰሩባቸው ወረዳዎች በሚገኙ ጤና ተቋማት የሚገነቡ የዋሽ ተቋማት ግንባታ መከታተልና መደገፍ፤
    - በዋን ዋሽ ወረዳዎች በሚገኙ ጤና ተቋማት የተሻለ አፈፀፀም ባላቸው ወረዳና ተቋም ላይ ልምድ ልውውጥ ማድረግ፤
    - በዋን ዋሽ ወረዳዎች ላይ የዕቅድ አፈፀፀም ግምገማ ማካሄድ፤
    - በወረዳ እና በከተማ ጤና ተቋማት ላይ የሃይጅን እና አካባቢ ጤና ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - በተዘጋጀው የጤና ተቋማት የውሃ፤ሳኒቴሽን እና ሃይጅን የስልጠና ማኑዋል መሰረት ለጤና ተቋማት ስልጠና መስጠት፤
- **የስራ ላይ ደህንነት እና ጤንነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ የቅንጅት ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - በስራ ላይ ጤንነትና ደህንነት ፓኬጅ ላይ ለጤና ተቋማት ባለሙያዎች በተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
    - ከባለድርሻ አካላት ጋራ የድጋፍና ክትትል ስራዎችን መስራት፤
- **የቤት ውስጥ እና የአከባቢ አየር ብክለት በጤና ላይ የሚያደርሰውን የጤና ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የህብረተሰብ ግንዛቤ የሚያሳድጉ መልእክቶችን ማዘጋጀት እና በብዙሀን እና በማህበራዊ ሚዲያዎች ማሰራጨት፤
    - የአየር ብክለት ግንዛቤ መፍጠሪያ አጫጭር የመልዕክት ማስተላለፊያ ፅሁፎችን ማዘጋጀት፤
    - የቤት ውስጥ የአየር ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የተግባቦት ስልቶችን ማጠናከር እና ግንዛቤዎችን ማሳደግ፤
    - በአከባቢ አየር ጥራት ክትትል፣ የመከላከያ እርምጃዎችና የህብረተሰብ ግንዛቤ ላይ ስልጠናዎችን መስጠት፤
    - የአከባቢ አየር ብክለት ደረጃ በሌሎች የሚመለከታቸው ሴክተሮች እንዲለካ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
    - የአከባቢ አየር ብክለት ደረጃ መረጃ አንድ ቋት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤
    - የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅፆችን፣ የአከባቢ አየር ጥራት መከታተያ ሰነዶችን ማዘጋጀት፤

- **የኬሚካሎች አያያዝ እና አጠቃቀም ጤና ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘርፈብዙ የቅንጅት ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - የኬሚካልና አደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ የጤና መልክት ማዘጋጀትና ማስተላለፍ ፤
    - የኬሚካልና አደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ንቅናቂ ስራዎችን ማካሄድ፤
    - የኬሚካልና አደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ዳሰሳ ማካሄድና በተገኙት ግኝቶች መሰረት የማስተካክያ እርምጃ መውሰድ፤
    - የኬሚካልና አደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ማጠናቀቅና መተግበር፤
    - ለተለያዩ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- **የጤናው ዘርፍ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ሥርዓትን ማጠናከር፤**
    - በአየር ንብረት ለውጥ የጤና መልዕክት ማዘጋጀትና ማስተላለፍ፤
    - የተዘጋጀውን የጤናው ዘርፍ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ሰነድ በየደረጃው ማስተዋወቅ እና መተግበር፤
    - የጤናው ዘርፍ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ እቅድ ሰነድ ላይ ስልጠና መስጠት፤
    - የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም ተቋማትን ለመፍጠር የበጀትና ቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
- **የድንገተኛ የውኃ፣ሳኒቴሽንና ሃይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ዝግጁነትና ምላሽን ማጠናከር፤**
    - የድንገተኛ የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መመሪያን ማስተዋወቅ፤
    - በድንገተኛ የውኃ፣ሳኒቴሽንና ሃይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ የስልጠና ማኑዋል ላይ ስልጠና መስጠት፤
    - ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሁኔታዎች ለሚከሰቱ የማኅበረሰብ ጤና አደጋዎች የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤
- **የሃይጅን እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መረጃዎችን ክትትልን ማጠናከር፤**
    - የሃይጅን ከር ክትትል ጤና አጠባበቅ በመደበኛ የሚመጡ መረጃዎችን ጥራት መከታተል እና በወቅቱ ግብረመልስ መስጠት፤
    - የሃይጅን ከር ክትትል ጤና አጠባበቅ በመደበኛ የማይመጡ መረጃዎችን ቋሚና ወጥነት ያለው የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ እና ለውሳኔ መጠቀም ባህልን በየደረጃው ማሳደግ፤

## 1.6 የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እና የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አገልግሎትን ማጠናከር

**ዒላማ፡**

- ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ (PHCU) ሽፋን ወደ 40% ማድረስ፡፡
- በጤና ኬላዎች ልየታ መሰረት ኮምፕርሄንሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፓኬጆችን የሚተገብሩ ጤና ኬላዎችን ቁጥር ከ1 ወደ 4(7%) ማሳደግ፤
- የጤና ጣቢያ ሪፎርም መመሪያ ሪፖርት ምጣኔ ከ50% ወደ 95% ማድረስ፤
- መሰረታዊ የድንገተኛ ቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች ቁጥር ከ0 ወደ 3 ማሳደግ፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ጥምረት ለጥራት አተገባበር ሽፋን ከ80% ወደ 95% ማድረስ፤

- በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የህክምና መመሪያ መሰረት የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎችን ሽፋን ከ25% ወደ 75% ማድረስ፤
- በጤና ተቋማት የጤና አጠባበቅ ትምህርት ትግበራ ሽፋንን ከ81% ወደ 95% ማሳደግ፤
- በትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ጤና ማበልጸግ ፕሮግራምን ከ24 ወደ 107 ት/ቤቶች ማድረስ፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **የጤና ኬላዎች አደረጃጀትና አሰራር መልሶ ቅየሳን ትግበራ ማጠናከር፤**
    - የጤና ኬላዎች አደረጃጀትና አሰራር መልሶ ቅየሳን በሁሉም ጤና ኬላዎች በተሻለ ለመተግበርና ለህብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በየደረጃው ላሉ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተከታታይነት ያለው የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፤
    - በሁሉም ወረዳዎች ጤና ኬላዎች እንደገና ተደራጅተው (CHP,BHP&Merged HP/HEP Unit) ስራ እንዲጀምሩ አስፈላጊ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
    - የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማሻሻያ ፍኖተ ካርታን በየደረጃው ላሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ማስተዋወቅ፤
    - የጤና ኬላዎች አደረጃጀትና አሰራር መልሶ ቅየሳን ለማገዝ የተዘጋጁ ሰነዶች በሁሉም ወረዳዎች ጥቅም ላይ እንዲውል መደገፍና መከታተል፤
    - ኮምፕሬንሲቭ እና ቤዚክ ጤና ኬላዎች ግንባታ እንዲከናወን ከጤና ልማት ዕቅድ ጋር አብሮ መስራት፤
    - የጤና ኬላ ግብአቶችን ለCHP እና BHP ጤና ኬላዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማሟላት፤
    - ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በተለይም ከስትራተጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ(ልማት እቅድ) ጋር በመሆን በተሻሻለዉ ጤና ኬላዎች አደረጃጀትና አሰራር መሰረት የጤና ኬላዎች መረጃ አያያዝ እንዲሻሻል ማድረግ፤
- **የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሪፎርምን ትግበራን ማጠናከር፤**
    - በከተማ ጤና ጣቢያዎች ያለውን ትግበራ ለማጠናከር የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ፤
    - ሪፎርሙ ባልተስፋፋባቸው አዳዲስ ከተሞች ማስፋት፤
    - ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሪፎርሙን በአነስተኛ ከተሞች ለማስፋፋት የአተገባበር ማንዋሉን ለመከለስ እንዲቻል የውስጥ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
    - የዳሰሳ ጥናቱን መረጃ መሰረት በማድረግ ለአነስተኛ ከተሞች በማንዋሉ መነሻ ተግባራዊ ማድረግ፤
- **የሞዴል ቤተሰብ እና ሞዴል ጤና ተቋማትን የማፍራት ስራዎች ማጠናከር፤**
    - በተሻሻለው የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ መከታተያ መመሪያ ላይ ስልጠና መስጠት፤
    - የተሻሻለውን የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ መከታተያ መመሪያን ማሰራጨት እና ትግበራውን መከታተል፤
    - በተሻሻለው የወረዳ ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸም መከታተያ ዳሽቦርድ በመጠቀም በየሩብ ዓመቱ የወረዳዎችን አፈጻጸም መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፤
    - ሞዴል ወረዳዎች ማረጋገጥ እና እውቅና መስጠት፤
    - ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን ለመፍጠር የሚያግዙ ኢንሼቲቮች ትግበራን ክትትል ማድረግ፤

- አምስቱን የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን ቅንጅት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፤

- **የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን የማስፈፀም አቅም ማጎልበት፤**
  - በዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሞጁዩሎች ላይ ስልጠና መስጠት፤
  - የዋሽና የአካባቢ ጤና እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ሞጁዩሎችን እንደ አስፈላጊነቱ ክለሳ ላይ መሳተፍ፤
  - ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በጤና ሳይንስ ኮሌጆች ላይ የቅድመ ስራ ስልጠና አሰጣጥ ሂደትን በጋራ መፈተሽ እና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤
  - ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ጋር በተያያዘ አዳዲስ አሰራሮች ላይ ለጤና ሳይንስ ኮሌጆች ስልጠና መስጠት፤

- **የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ስርዓት ማዕቀፍን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
  - የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ስትራቴጂ ማዕቀፉን በየደረጃው ባሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ማስተዋወቅና ትግበራውን መከታተል፤
  - ስትራቴጂክ ማዕቀፉን መሠረት ያደረገ አደረጃጀትና አሰራር በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል ማድረግ፤

- **የጤና ጣቢያ መጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ መመሪያ ትግበራን ማጠናከር፤**
  - ከዚህ በፊት ስልጠና ያልወሰዱ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የተዋረድ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - የEPHCG ስታንዳርዶችን መሰረት ያደረገ ክትትልና ድጋፍ ማከናወን፤
  - ዲስክ ቶፕ መተግበሪያን በሁሉም ጤና ጣቢያዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የማስተዋወቅ፣ ስራዎች መስራት፤
  - በEPHCG ዳሽቦርድ የሚሰበሰበውን ሪፖርት በየሩብ አመቱ በጥልቀት በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፤
  - የክሊኒካል ኦዲት ስራዎችን ለማጠናከር ስልጠናዎችን መስጠት፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - የEPHCG ትግበራን ለህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ፤
  - የEPHCG ትግበራን በየጊዜው የሚያግዝና የህክምና መረጃዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤

- **የጤና ጣቢያ ሪፎርም ትግበራ ማጠናከር፤**
  - በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ስልጠና ላልወሰዱ ጤና ጣቢያዎች የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
  - የተከለሰውን የጤና ጣቢያ ሪፎርም መመሪያ ማሰራጨት፤
  - የጤና ጣቢያ ሪፎርም አፈፃፀም ሙሉዕነት፣ ጊዜውንና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን በየሩብ አመቱ መገምገምና ግብረ መልስ መስጠት፤
  - የጤና ጣቢያ ሪፎርም መመሪያ (EHCRIG) ትግበራን ለማጠናከር በየደረጃው ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - የመጀመርያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አመራሮችን አቅም በአመራርነትና አስተዳደር መስኮች ላይ ማሳደግ የሚችሉ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን፤
  - የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ በጤና ጣቢያዎች እንዲተገበር የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤

- በክልል ደረጃ የጥራት ማሻሻያና የህክምና ተግባቦት ክህሎት የተዋረድ ስልጠና መስጠት፤
- የጥራት ማሻሻያና የህክምና አሰጣጥ የተግባቦት ክህሎት(quality improvement and clinical communication skill) ማሻሻያ ማንዋሎችን ማሰራጨት፤

▪ **በጤና ጣቢያዎች የህክምና መሳሪያዎች እንዲሟሉ እንዲሁም የጤና ጣቢያዎችን የኦአር አገልግሎት ትግበራን ለማጠናከር በየደረጃው የድጋፍና የክትትል ስራዎች ማጠናከር፤**

- ለጤና ጣቢያዎች አገልግሎት ለማስጀመር የሚሆን በጀት ማስመደብ፤
- የህክምና መሳሪያዎች ለተመረጡት ጤና ጣቢያዎች እንዲሟላ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ክትትል ማድረግ፤
- ግንባታቸው ለተጠናቀቀና የኦአር የህክምና መሳሪያዎችን ያላገኙ ጤና ጣቢያዎች እንዲያገኙ ክትትል ማድረግ፤
- የኦአር አገልግሎት ለሚሠጡ ጤና ጣቢያዎች የተዋረድ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- የኦአር አገልግሎት ትግበራን ለማጠናከር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

▪ **የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጥምረት ለጥራት ማጠናከር፤**

- የተሻለ አፈፃፀም ላላቸው ወረዳዎችና ጤና ጣቢያዎች የማበረታቻ ስራዎችን ማካሄድ፤
- የEPAQ ሁለተኛ ሳይክል ኦዲት ቱል ዝግጅት ላይ መሳተፍ፤
- በEPAQ መለኪያዎች የተሻለ አፈጻጸም ባስመዘገቡ ወረዳዎችና ጤና ጣቢያዎች የልምድ ልዉዉጥ ማከናወን፤
- ሞዴል ጤና ጣቢያ የሚሆኑ ከወረዳዎች መምረጥ፣ መደገፍ፣ ማብቃትና ተሞክሮአቸውን ለሌሎች ማካፈል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ ጥምረት ለጥራት (EPAQ) ትግበራ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- የመጀመርያ ደረጃ ጤና ክብካቤ /PHC mentorship and coaching handbook/ ማስተግበር፤

▪ **የጤና ጣቢያዎች የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር ትግበራን ማጠናከር፤**

- የተከለሰውን የIPC መመሪያ ህትመትና ስርጭት ማካሄድ፤
- በተከለሰው የIPC መመሪያ ለጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- በየሩብ ኣመቱ የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር (IPC/CASH) Audit score ሪፖርት እንዲላክ ክትትል ማድረግና ግብረ-መልስ መስጠት፤
- የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች የሚውል ግብዓቶችን ማሟላት እና አጠቃቀማቸውን ክትትል ማድረግ፤
- የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት የሚውል መመሪያዎች እና ማስተማሪያ ማሰራጨት፤

▪ **በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የወረርሽኞችና ድንገተኛ አደጋ የመከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን ማጠናከር፤**

- ለጤና ጣቢያ ባለሙያዎች እና ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የተዋረድ የአቅም ግንባታ ስልጠና በCommunity based surveillance and case management ላይ መስጠት፣
- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና አዕምሮ ጤና ዙሪያ የተዘጋጁትን በራሪ ወረቀቶችን ማሰራጨት፤

- በግሎባል ፈንድ የኮቪድ 19 ግራንት ተገዝተው የተከፋፈሉትን የተለያዩ የህክምና መሣሪያዎች አጠቃቀም መከታተል፤
- የኮቪድ 19 ህክምና አሰጣጥ ላይ የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ከወረዳዎች ጋር ማድረግ፤
- የኮቪድ 19 ህክምና አሰጣጥና የህክምና መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ከወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ግምገማ ማካሄድ፤

## 2. የድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል

**ዒላማ፡-**

- ከስታንዳርዱ በላይ ሞት ሳያስከትል በቁጥጥር ስር የዋለ ወረርሽኝ ሽፋን 95% ማሳደግ፤
- የተሟላ ወቅቱን ጠብቆ የሚላከውን ሳምንታዊ የሰረቪላንስ ሪፖርት ሽፋን 100% ማስቀጠል፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቅኝት ስራዎች ማጠናከር (ኮቪድ-19)፤**
  - የተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቅኝት ማካሄድ፤
  - የተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ምርምር ማካሄድ፡
- **በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚሰሩ ስራዎች ማጠናከር፤**
  - በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ላይ ምርምር ማድረግ፤
  - በክትባት ዉጤታማነት ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤
  - በክልል ደረጃ የተሰሩትንና ለወደፊቱ ሊሰሩ የታቀዱትን የጥናት መረጃዎች መሰብሰብ፤
  - የሁለተኛ ደረጃ ዳታዎች/መረጃዎች ጥራት ሁኔታ ማሻሻል/ማሳደግ እና ለውሳኔ መጠቀም፤
  - የመረጃ አያያዝ ስርአትን መገምገምና ማጠናከር፣
  - የአካባቢ እና የጤና መረጃ የመሰብሰብ አቅምን ማሳደግ፤
  - የጤና መረጃ ትንተና እና የእይታ መንገዶችን ማዳበር፣
  - በክልሉ በጥናት የሚፈቱ ዋና ዋና የህብረተሰብ ጤና ችግሮችን መለየት፤
  - ምርምር ከሚያካሄዱ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት የመስራት ሥርዓት መዘርጋት፤
- **ትንበያ፣ የተቀናጀ እና የላቀ ስታቲስቲካዊ ዘዴዎችን በማዳበር የህብረተሰብ ጤናን ማዘመን፤**
  - የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ክስተት በወቅቱ የማረጋገጥ ሥርዓት መዘርጋት፤
  - ለተከሰቱ አደጋዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ቅድመ ዝግጅትን ማሻሻልና መተግበር፤
  - ለህብረተሰብ ጤና አደጋዎች/በሽታዎች የቁጥጥር አጋዥ ሰነዶች ማዘጋጀት፤
  - ለዋና ዋና የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች የተጋላጭነት ደረጃ እና መንስኤዎችን መለየት፤
  - ዋና ዋና የህበረሰብ አደጋዎች ሳይከሰቱ የቅድመ- ዳሰሳ ጥናቶችን ማካሄድ፤
- **ቀጣይነት ያለው ቅኝት ለማካሄድ በተመረጡ በሽታዎች እና ፈጠን ምላሽ የሚሹ የወረርሽኖች ቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - ለተመረጡ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች የቅኝት ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር (የሴንትኔል ቅኝት እና የላቦራቶሪ ቅኝት ማካሄድ)

- የህብረተሰብ ጤና አደጋ ጥቆማ/ጭምጭምታዎችን መሰብሰብ፣ ማረጋገጥና አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት መስጠት፤
- ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ የሆኑ በሽታዎች የቅኝት ስርዓትን ማጠናከር፤
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና የአደጋ ስጋት ተግባቦትን ማጠናከር፤
- የህብረተሰብ ጤና አደጋ ክስተት ከተረጋገጠ በኋላ የመከላከያና መቆጣጠሪያ እርምጃዎች መዉሰድ፤
- የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች የቅኝት ስራ ለማካሄድ ክልላዊ የጥሪ ማዕከል ማጠናከር፤
- በተመረጡ አካባቢዎች የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከልን (Emergency operating Center/ EOC) ማቋቋም፤መደገፍና ማጠናከር)፤
- ከአጎራባች ክልሎች ጋር የተቀናጀ የተላላፊ በሽታዎችን ቅኝትና ምላሽ ማጠናከር፤

- **የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች preparedness & readiness ማጠናከር፤**
    - ድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊዉን የሎግስትክስ እና በቂ በጀት ማስቀመጥ
    - ድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ሰጪ አካላትን በእዉቀት፣ በክህሎትና በቁሳቁስ ማብቃት
    - የህብረተሰብ ጤና ለመጠበቅ፣ አደጋዎችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ልዩ የሆኑትን አስፈላጊ ሥርዓቶችን መገንባት፣
    - ለወደፊት ልከሰቱ የሚችሉ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን ለመገመት እና ፈጣን እርምጃ ለመዉሰድ ከልምድ የተገኙ እዉቀቶችን መመዝገብ እና መጋራት (documenting and sharing lesson learned)
    - ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የምስራት ሥርዓት (coordination and collaboration) ማጠናከር
    - የድህረ የህብረተሰብ ድንገተኛ አደጋዎች መልሶ የማቋቋም ስራዎች መስራት፤
    - ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ጊዜና በኃላ ለተጎጅዎች የሥነ ልቦና ድጋፍ የማድረግ ሥርዓት ማጠናከር፣
    - የወረዳዎችን የአደጋ ዝግጁነት እና የአስተዳደር አቅም ማሳደግ፤
    - በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኋላ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ቀጣይነትን ማረጋገጥ፤
    - የጅምላ አደጋዎች ዝግጁነትና ምላሽን ማጠናከር፤

## 3. የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነትን ማሻሻል

**ዒላማ**

- የሞዴል ቤተሰብ መስፈርት አሟልተው በጤና ኤክስቴንሽን ሞዴል የሆኑ እማ /አባዎራዎች ሽፋን ከ 30% ወደ 50% ማድረስ፤
- የሞዴል ቀበሌዎች መስፈርት አሟልተው የተመረቁ ሞዴል ቀበሌዎች ሽፋን ከ22% ወደ 40% ማድረስ፤
- የሞዴል ወረዳ መስፈርት አሟልተው ሞዴል የሆኑ ወረዳዎች ሽፋን 11% ማድረስ፤

- የተሻሻለውን የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች የሚተገበሩ ወረዳዎችን ቁጥር ከ1 ወደ 7 ወረዳዎች ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን ማጠናከር፤**
    - በሰለጠኑ የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎችና የጎጥ ጤና መሪዎች አማካኝነት የህብረተሰቡን የንቃተ-ጤና እና ንቃተ-ጤና-ስርዓት የሚጨምሩ ተግባራትን ማከናወን፤
    - የቤተሰብ ጤና መመሪያ ለልማት ቡድን እና ለጎጥ ጤና መሪዎች ማሰራጨት፤
    - ለሴቶች ልማት ቡድን እና ለጎጥ ጤና መሪዎች የብቃት ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት፤
    - የብቃት ማጎልበቻ ስልጠና ያጠናቀቁትን ሴቶች ልማት ቡድን መሪዎች መመዘንና ሰርተፍኬት መስጠት፤
    - ስልጠና ያጠናቀቁ የጎጥ ጤና መሪዎች፣ የልማት ቡድን መሪዎች እና የተለያዩ አደረጃጀቶችን ወደ ስራ ማስገባት፤
    - ስልጠና አጠናቀው ወደ ስራ ለገቡ የሴቶች ልማት ቡድን እና የጎጥ ጤና መሪዎች አፈጻጸማቸውን መሰረት በማድረግ በተቀመጠው አሰራር መሰረት የማበረታቻ ስርዓትን መተግበር፤
- **ሞዴል ቤተሰብ እና ሞዴል ቀበሌ የማፍራት ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የዘርፈ ብዙ ትብብር ስራዎችን ማጠናከር፤
    - የሴቶች እና ሌሎች አደረጃጅቶችን በመጠቀም የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን ማጠናከርና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፤
    - አካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን የተቃኘ ማህበረሰብ ተኮር አዳዲስ ፈጠራዎችን መተግበር፤
    - ሞዴል ወረዳ ለመፍጠር ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋፋት፤
    - መሰረታዊ የጤና ፕሮግራሞችን ውጤታማ ማድረግ የጤና መዋቅሮችን እንዲጠናከሩ ድጋፍ መስጠት፤
    - የማህበረሰብ ተጠያቂነት ስርዓትን (የማህበረሰብ አስተያየት መመዘኛ) ጤና ኬላዎች ላይ የሙከራ ትግበራ መጀመር፤
- **የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - የተሻሻለውን የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ መከታተያ መመሪያን ማሰራጨት እና ትግበራውን መከታተል፤
    - በተሻሻለው የወረዳ ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸም መከታተያ ዳሽቦርድ በመጠቀም በየሩብ ዓመቱ የወረዳዎችን አፈጻጸም መከታተልና ግብረ መልስ መስጠት፤
    - ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃዶችን ለመፍጠር የሚያግዙ ኢንሼቲቮች ትግበራን ክትትል ማድረግ፤
    - አምስቱን የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን ቅንጅት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፤
    - ሞዴል ወረዳዎች ማረጋገጥ እና እውቅና መስጠት፤

## 4. የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማሻሻል

**ዒላማ:**

- ስታንዳርዱን ሙሉ በሙሉ እንዲተገበሩ ለማስቻል ቁጥጥር የተደረገባቸዉ ጤና ተቋማት ሽፋን ከ51% ወደ 80% ማድረስ፤
- ቁጥጥር የተደረገባቸው የምግብና መጠጥ ተቋማት ሽፋን ከ35% ወደ 65% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በምግብ፤ በመድሀኒትና በሌሎች ቁጥጥር በሚደረግባቸው ምርቶች ዙሪያ ለህብረተሰቡ የቁጥጥር ግንዘቤ የማሰጨበጥ ስራን በማሳደግ የህበረተሰቡን ባለቤትነት ማረጋገጥ፤**
  - ቁጥጥር በሚደረግባቸው ምርቶች ዙሪያ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ቀጥታ ውይይት ማካሄድ፤
  - የተለያዩ የህበረተሰብ አካላት ቁጥጥር በሚደረግባቸው ምርቶች ዙሪያ ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ እንዲያገኙ በህትመት እና ሚዲያ ማሰራጨት፤
  - በምግብ፣ መድኃኒትና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፤
- **ከህብረተሰቡ የሚመጡ ጥቆማዎችን ማሳባሰብና ምላሽ የመስጠት ስራን ማጠናከር፤**
  - ለቁጥጥር አሰራር ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ጥቆማዎችን፣ መረጃዎችንና አስተያየቶች መቀበል፤
  - ለቁጥጥር አሰራር ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ጥቆማዎችን መረጃዎችንና አስተያየቶች በመቀበል ተገቢውን ግብረ-መልስ መስጠት፤
  - የቁጥጥር ዘርፉን ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ጋር ተግባራዊ እንዲሆን የዞኖች እና ወረዳዎች የዝግጁነት ደረጃ ለመፈተሽ ዳሰሣ ማካሄድ፤
- **ለመድሀኒት እንዲሁም የምግብ ምርት ምዝገባ የፈጣን ምላሽ ስራዎቹን ማጠናከር፤**
  - ክልል ተሻጋሪ ላልሆኑ ተጨማሪ ምግብ በሰነድ ግምገማ አማካይነት ምዝገባ ማከናወን፤
  - ክልል ተሻጋሪ ላልሆኑ ለህፃናት ምግብ ሰነድ ግምገማ በማድረግ ምዝገባ ማከናወን፤
  - ሌሎች ክልል ተሻጋሪ ላልሆኑ ልዩ ልዩ ምግብ አይነቶች ሰነድ በመገምገም ምዝገባ ማከናወን፤
  - ለተለዩ የምግብ ምርቶች በማሳወቂያ /notification / ምዝገባ ማካሄድ፤
  - የባህል ህክምና አዋቂዎች እና ተቋማትን ምዝገባ ማካሄድ፤
  - የባህል ህክምና አዋቂዎች እና ተቋማትን ቁጥጥር ማካሄድ፤
  - ከሚመለከተዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሆን የባህል ህክምና ባለሙያዎችን እና ተቋማትን ምዝገባ እንዲያከዉኑ ለዞንና ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- **በምግብ ምርት ላይ ስጋት ተኮር የሆነ የምግብ ደህንነት ኢንስፔክሽን ስራን ማጠናከር፤**
  - ክልል ተሻጋሪ ላልሆኑ በምግብ አምራች ተቋማት ላይ የቅድመ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ማካሄድና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

- ክልል ተሻጋሪ ባልሆኑ ምግብ አምራች ተቋማት ላይ ስጋት ተኮር የሆነ ድህረ ፍቃድ የምግብ ደህንነት ኢንስፔክሽን ማካሄድ፤
- መስፈርቱን ላሟሉ ክልል ተሻጋሪ ላልሆኑ አዲስ የምግብ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፤
- በምግብ ችርቻሮ ድርጅቶች ላይ የቅድመ-ፍቃድ ኢንስፔክሽን ማካሄድና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

▪ **በምግብ ተቋማት ውስጥ፤ የምግብ ኮንሳይንመንት፤ የምግብ የድኅረ ገበያ ጥራት እና ምርመራ የማረጋገጥ ስርአት የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፤**

- በምግብ ተቋማት የውስጥ ጥራት ማረጋገጥ ስርአት እንዲዘረጉ ማድረግ፤
- ክልል ተሻጋሪ ያልሆኑ የምግብ አምራችና አከፋፋይ ተቋም የውስጥ ጥራት ስርአት እንዲይዙ ማድረግ፤
- የምግብ ኮንሳይንመንት ጥራት ምርመራ ማከናወን፤
- በተመረጡ የምግብ አይነቶች ላይ የድህረ ገበያ ጥራት ምርመራ ማካሄድ፤
- የተጠረጠሩ የምግብ ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ ማከናወን፤

▪ **በገበያ ውስጥ ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ የሕገ-ወጥ የምግብ ምርቶች ዝውውር ቁጥጥር ማጠናከር፤**

- ምግብ ከባዕድ ነገር መቀላቀል ላይ ሰርቬላንስ መስራትና ኦፕሬሽን ማከናወን፤
- ምግብን ከበአድ ነገር ጋር ከመቀላቀል ጋር በተያያዘ የሚመጡ የምግብ አይነት ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ ማከናወን፤
- በተለያዩ የምግብ ምርቶች ላይ በምግብ ገበያ ማዕከላት እና በምግብ ችርቻሮ ተቋማቶች ላይ ቅኝት ማድረግ፤
- ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ጋር በመቀናጀት በባአድ ነገር ሊከለሱ የሚችሉ የምግብ አይነቶችን በመለየት የበአድ ነገሩን ምንነት ለመመርመር የሚያስችል Advanced የምርመራ ዘዴ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤

▪ **የመድኃኒቶች ድህረ ገበያ ጥናት የማረጋገጥ እና አግባባዊ አጠቃቀም የሚሻሻልበት ስራዎችን ማጠናከር፤**

- ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ጋር በመቀናጀት ህገ ወጥ የመድሃኒት፣ ንግድ ዝውውር፤ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና ተመሳስለው የተሰሩ መድኃኒቶች ላይ የሰርቬላንስ ስራ መስራት እና አስፈላጊ ኦፕሬሽን ማካሄድ፤
- በተለያየ ምክንያት አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ የጤና ግብዐቶች በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጥ፤
- አግባባዊ መድሀኒት ስርጭትና ዕደላ መከናወኑን በመድሀኒት ተቋማት ቁጥጥር ማድረግ፤

▪ **የመድሀኒት የጥራት ቁጥጥር እና የፋርማኮቪጅላንስ ስራዎችን ማጠናከር፤**

- በክልሉ መውጫና መግብያ የቁጥጥር መስመሮች መደበኛ የቁጥጥር ፍተሻን ማከናወን፤
- ከተለያዩ አከባቢ የቀረቡ የ ADE ሪፖርቶችን በማጠናከር ለኢትየጵያ ምግብና መድኃኒት ዳታ ቤዝ መላክ፤
- በጤና ተቋማት ላይ የመድኃኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት/ADE አስመልክቶ የገፅ-ለገፅ ውይይት ማካሄድ፤
- የCovide-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት /AEFI/ ላይ ጥናት ለማድረግና የውሳኔ መረጃ ለመስጠት ሪፖርቶችን በየወሩ መሰብሰብ እና ለሚመለከተዉ አካል መላክ፤

- **የናርኮቲክ እና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን እና የህክምና ቁጥጥር ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሀኒቶች አጠቃቀምና ዝውውር ሪፖርቶች ለሚመለከተዉ አካል መላክ፤
    - ሰርቪላንስ በማካሄድ ህገወጥ የህክምና ሙከራ መለየትና እርምጃ መውሰድ፤
    - የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ማዘዣ ግዢ ፈቃድ መስጠት፤
- **የመዋቢያ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ማሳወቅ ስራዎች ማጠናከር፤**
    - ለመዋቢያ ምርት አምራቾች የቅድመ ፍቃድ ኢንስፔክሽን በማከናወን የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤
    - ለመዋቢያ ምርት አምራቾች የድህረ ፍቃድ ኢንስፔክሽን ማከናወን፤
- **የትንባሆ ምርት ቁጥጥር እና የጥራት ደረጃ አሰተዳደር ማጠናከር፤**
    - ከትምባሆ ጭስ ነጻ የሆኑ የሕዝብ መሠብሰቢያ ቦታዎች ማሳደግ፤
    - ሕገ ወጥ የትንባሆ ምርት ቁጥጥር ሥራዎች ማከናወን፤
    - ህገ ወጥ የትንባሆ ንግድና ዝውውር ላይ የሰርቬላንስ ስራ መስራት እና ኦፕሬሽን ማከናወን፤
    - ከ 21 ዓመት በታች ለሆኑ ታዳጊዎች ትንባሆ ሽያጭ እንዳይተገበር ክትትልና ቁጥጥር ማደረግ፤
- **የሕግ ማዕቀፎችን ዝግጅት እና ትግበራ ማሻሻል፤**
    - የህግ ማዕቀፎችን (አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን) ማዘጋጀት፤
    - ነባር መመሪያዎችን መከለስ፤
- **መረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥ ስርአትን ማሻሻል፤**
    - ሪፖርቶችን በአግባቡ ማጠናከርና በወቅቱ ለሚመለከተዉ አካል መላክ፤
    - የተቀናጀ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ማካሄድ፤

## የጤና ባለሙያዎች ቁጥጥር

### ዒላማ

- የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እና ቁጥጥር ስርዓቱን ከ83 ከመቶ ወደ 96 በመቶ ማድረስ፤

### ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት፤

- **የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ስርአትን ማሻሻል፤**
    - አዲስ የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ምስክር ወረቀት በመስጠት ፣
    - ጊዜ ያለፈባቸው የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ማሳደስ፣
    - ነባሪ የጤና ባለሙያዎች ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ (CPD) ሰርትፊኬት አቅርበው እንዲያሳድሱ ክትትል ማድረግ፤

- የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እና ቁጥጥር ስርዓቱን HRIS በመጠቀም ማዘመን (e-licensing ተግባራዊ ማድረግ)

## የጤና እና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻል፤

### ዒላማ

- ➢ ስታንዳርዱን ሙሉ በሙሉ እንዲተገብሩ ለማስቻል ቁጥጥር የተደረገባቸዉ የጤና ተቋማት ሽፋን ከ53% ወደ 80% ማድረስ፤
- ➢ ቁጥጥር የተደረገባቸው የምግብና መጠጥ ተቋማት ሽፋን ከ35% ወደ 65% ማድረስ፤

### እስትራቴጂክ እርምጃዎች

- የጤናና ጤና ነክ ተቋማትን ቁጥጥር ማጠናከር፤
- የምግብ እና መጠጥ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ሃይጅንና አካባቢ ጤና ቁጥጥር ስራን መስራት፤
- በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቁጥጥር ስርዓት ትግበራ ማጠናከር፤
- ሀገራዊ የጤና ተቋማት መረጃ አያያዝ (Master Facility Registry) ስርዓት ማጠናከር፤

### ዋና ዋና ተግባራት

- ፍትሐዊና ወጥ በሆነ መንገድ የጤና ተቋማትን የቅድመና ድህረ ፍቃድ ኢንስፔክሽን ስርዓት ማሻሻል፤
- የጤና ተቋማት ላይ የሚደረገውን የቁጥጥር ስርዓት መተግበር፤
- በጤና ነክ ተቋማት ላይ የሚደረገውን የሃይጅንና አካባቢ ጤና ቁጥጥር ስርዓት መተግበር፤
- በጤናና ጤና ነክ ተቋማት ላይ የሚሰሩ የቁጥጥር ስራዎችን ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣
- ከዞንና ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ህገወጥ የጤና አገልግሎት ላይ የጋራ ቁጥጥር ማድረግና የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ማጠናከር፤
- ከዞንና ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ አካላት ጋር የጤና ነክ ተቋማት ሃይጅንና አካባቢ ጤና ላይ የጋራ ቁጥጥር ማድረግና የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ማጠናከር፤
- በጤናና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ስርዓት ላይ የባለድርሻ አካላትንና የሙያ ማህበራትን ተሳትፎ ማጠናከር፤
- በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቁጥጥር ስርዓት ትግበራ ማጠናከር፤

## 5. የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ማሳደግና አግባባዊ አጠቃቀምን ማረጋገጥ

**ዒላማ፤**

- በጤና ተቋማት የመደበኛ አማካይ የህይወት አድን እና መሠረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት አሁን ካለበት 80% ወደ 82% ማሳደግ፤
- የመድኃኒት የብክነት መጠንን በክልል አሁን ካለበት 1.8 ወደ 1.5 መቀነስ፤
- ታካሚዎች የታዘዘላቸውን 100% መድኃኒት በታዩበት ጤና ተቋም ያገኙ ህሙማን ሽፋን ከ80% ወደ 85% ማሳደግ፤
- አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የህክምና መሳሪያዎች በመቶኛ ከ81% ወደ 90% ማሳደግ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ሽፋን ከ5% በታች ማድረስ፤
- በግለሰብ ደረጃ የታዘዙ ጸረ-ተህዋሲያን መድሃኒቶች በመቶኛ ከ56.2% ወደ 30% መቀነስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የጤና ተቋማትን የፋርማስቲካል አገልግሎት ስርዐትን ማጠናከር፤**
  - በክልል ባሉ ጤና ተቋማት ዉስጥ የመድኃኒት እጥረት እንዳያጋጥም የድጎማ ባጀት ማስመደብ፤
  - በሁሉም በክልል ሆስፒታሎች የመድኃኒትና ህክምና ኮሚቴን functional ማድረግ;
  - የAPTS አገልግሎትን ማስፋፋት፣ ማጠናከር እና ማዘመን፤
  - HCMIS (Dagu2) & LMD mobile appilication በጤና ተቋማት ማስፋፋት፤
  - የክልኒካል ፋርማሲ አገልግሎትን በሁሉም የክልሉ ሆስፒታሎች ማስጀመር፤
  - በሁሉም የክልሉ ሆስፒታሎች የመድኃኒት መረጃ አገልግሎትን ማጠናከር እና ተጨባጭ ስራ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፤
  - የመድኃኒት ቅመማ አገልግሎትን ማስፋፋት እና ማጠናከር፤
  - በጤና ተቋም የሚታየውን ያለአግባብ የመድሃኒት አጠቃቀም ለመከላከል ጥናቶች እንዲከናወኑ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
  - በሁሉም ሆስፒታሎች የመድሃኒት እና ህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ከትትልና ግምገማ ስረዓት ማጠናከር ለማጠናከር በተዘጋጀው ማዕቀፍ ዙሪያ የግንዛቤ መስጫ እና ስልጠና በመስጠት ሪፖረቶችን መሰብሰብ፣ ማቀናጀት እና መተንተን፤
  - ሞዴል የማህበረሠብ መድኃኒት ቤቶችን ማስፋፋት እንዲስፋፋ ከሚመለከተው አካል ጋር በመስራት እና ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ፤
  - ተከታታይ ህክምና ለሚሹ ታካሚዎች ልዩ የፋርማሲ አገልግሎትን ማስፋፋት፤
- **የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች መላመድን መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ማጠናከር፤**
  - በጤና ተቋማት አግባብነት ያለው የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማጎልበት አስፈላጊ የሆኑ ማንዋሎችን፣ መመሪያዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን ማሰራጨት፤
  - በጤና ተቋማት የAntimicrobial stewardship ፕሮግራምን ማስተግበር፤
  - አግባብነት ያለው የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማጎልበት የጤና ባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት፤

- በማህበረሰቡ አግባብነት ያለው የመድሃኒት አጠቃቀም እንዲኖር ለማስቻል የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት፤
- በህብረተሰቡና በጤና ተቋማት አግባብነት ያለው የመድኃኒት አጠቃቀም ያለበትን ደረጃ የሚያሳዩ የተለያዩ ጥናቶችን ማከናወን፤
- የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች መላመድን ለመከላከል የተዘጋጁ ስትራቴጂዎችን እና ትሪትመንት ጋይድላይኖችን ለጤና ተቋማት ማስተዋወቅ እና ትግበራን መከታተል፤

- **የመድኃኒት አቅርቦትን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
    - ወጥ የሆነ የመድኃኒት መረጃ ስረዓት መዘርጋት፤
    - የመድኃኒት ምጠና በጥራትና በወቅቱ እንዲሰራ መደገፍ፤
    - የተቀናጃ የመድኃኒት ሎጅስትክ ስርዓትን ማጠናከር፤
    - ተቋማት ለመድኃኒት ግዥ በቂ በጀት እንዲመድቡ አድቮኬት ማድረግ፤
    - የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘበ የመድኃኒት አቅርቦት በጤና ተቋማት እንዲኖር ማድረግ፤
- **አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ ግብአቶችን መጠን መቀነስና የአስተዳደር ስርዓት ማሻሻል፤**
    - የመንግስት እና የግል ድርጅቶች አጋርነትን/ትብብር በመፍጠር የማስወገጃ ቦታዎችን ማስፋፋት፤
    - በክልል አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ የመድሃኒት ብክነት መጠን፣ መንስኤዎች እና መፍትሔ ሀሳቦችን የሚሳይ ጥናት መስራት፤
    - የWarehouse inventory management /WIM/ ስርዓትን በተቋማት በማጠናከር ስታንዳርዱን የሚያሟላ የመድሃኒት መጋዘን መፍጠር፤
    - በጤና ተቋማት መካከል ሀብትን ለመጋራት የወጣ የአሠራር ሥርዓት መመሪያ በተቋማት ተግባራዊ ማድረግ፤
    - አገልግሎት ላይ የማይዉሉ የህክምና ግብአቶችን ለማስተዳደር እና ለማስወገድ የሚረዳ ዶክመንት /guideline/ መምሪያ በጤና ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ፤
- **የማይበገር የድንገተኛ በሽታዎችና እና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የህክምና ግብዓት አቅርቦት እና አስተዳደር ስርዓት መፍጠርና ማጠናከር፤**
    - ለድንገተኛ በሽታዎች የሚያገለግሉ ግብዓቶችን መለየት፣ መመጠን፣ ግዥ ማስጀመርና የግዥ ሀደቶችን መከታተል፤
    - የድንገተኛ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ግብዓቶችን የስርጭት ዕቅድ መስራት እና መከታተል፤
    - ዕርዳታዎችን ማስተባበርና ማስተዳደር እና የድንገተኛ ህክምና ግብዓት አመራርና አስተዳደር ስረዓት መዘርጋት፤
- **የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎትን ማጠናከር፤**
    - የህክምና መሳሪያዎች የጥገናና መለዋወጫ ልየታ ዘመቻን በዓመት ሁለት ግዜ ማካሄድ፤
    - የህክምና መሳሪያዎች ተከላን መደገፍና መከታተል፤
    - በሆስፒታሎች የኦክሲጅን አቅርቦትን እንዲሻሻል ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ማከናወን፤
    - የባዮሜዲካል ኢንጅነሮችን ክህሎት ለማሻሻል ስልጠናዎችን ማካሄድ፤
    - የህክምና መሳሪያ ጥገና ዎርክሾፖችን መደገፍና መከታተል፤

- የቀዝቃዛ ሰንሰለት፣ የassistive and rehabilitation አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎች ላይ ድጋፍና ክትትል ማደረግ፤
- የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት ስርዐቱን ለማገዝ የዳሰሳ ጥናት ወረቀት መስራት፤

- **የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት፣ አስተዳደርና ስርዓትን ማጠናከር፤**
  - የህክምና መሳሪያዎች የግዥ ፍላጎትን በመለየት የግዥ ትዕዛዝ መላክና ከዚህ በፊት የታዘዙ የህክምና መሳሪያዎችና መለዋወጫዎች ግዥ መከታተል፣
  - የህክምና መሳሪያዎችና መለዋወጫዎች የስርጭት መርሃግብር ማዘጋጀትና መከታተል፣
  - ክልላዊ የህክምና መሳሪያዎች መረጃ ስርዓት (MEMiS) አጠናክሮ መተግበር፤

## 6. በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትና ፈጠራ ማሻሻል

**ዒላማ፤**

- የመረጃ ዘገባን ወጥነት ማረጋገጫ (LQAS) የተመረጡ ጠቋሚዎች ውጤት ከ10% ያልበለጠ ልዩነት ያስመዘገቡ ጤና ተቋማት ከ90% ወደ 95% ማሳደግ፣
- የተወለዱ ልጆችን የማሳወቅ (Birth notification) ሽፋን ከ65% ወደ 90% ማድረስ፣
- የሞት የማሳወቅ (Death notification) ሽፋን ከ47% ወደ 80% ማድረስ፣
- የፐብሊክ ጤና ተቋማት ሪፖርት ወቅታዊነት ከ44% ወደ 90% ማድረስ፣
- የፐብሊክ ጤና ተቋማት ሪፖርት ሙሉነት ከ92% ወደ 99% ማድረስ፣
- የአርሶ አደር eCHIS የተገበሩ ጤና ኬላዎች ብዛት ከ248 ወደ 348 ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃና ዋና ዋና ተግባራት፤**

- **የዘርፉን የአንድ ዕቅድ፣ አንድ በጀትና አንድ ሪፖርት ትግበራን ማጠናከር፤**
  - በየወረዳውና በክልል ደረጃ የተሰራውን ዕቅድ በማሰባሰብ በማጣጣም የሃብት ክፍተት መለየትና በወረዳ ተኮር ዕቅድ ህትመት እንዲካተት ማድረግ፤
  - ለ2016 በጀት ዓመት ለዕቅድ ዝግጅቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማሰባሰብ፤
  - ለሆስፒታል ዕቅድ ዝግጅት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - ወረዳን መሰረት ያደረገ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - ለ2017 በጀት ዓመት ረቂቅ አንኳር ዕቅድ (Indicative plan) ማዘጋጀት፤
  - የጤና ቢሮ፣ ተጠሪ ተቋማት፣ ሆስፒታሎች በዕቅድ ዝግጅት መመሪያው መሰረት ዕቅዳቸውን እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ፤
  - የ2017 በጀት ዓመት የጤና ቢሮ ረቂቅ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፤
  - መረጃ መሰረት ያደረገ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ለባለሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- **ፕሮግራም መሰረት ያደረገ የበጀት ዕቅድ አሰራርን ማጠናከር፤**
  - በጤና ቢሮ ስር የሚተዳደሩ ተጠሪ ተቋማት እና ሆስፒታሎች የ2016 ፕሮግራምን መሰረት ያደረገ የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
  - በየሩብ ዓመቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ መላክ፤
  - Project Management ላይ ባለሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - ፕሮግራምን መሰረት ያደረገ መርሃ-ግብር (action plan) ማዘጋጀት፤

- **የማህበረሰብ የጤና መረጃ ስርዓት ማጠናከር፤**
    - የማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርዓት ስልጠና በ IRT ስርዓት ውስጥ ማካተት፤
    - የማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርዓትን ከጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ የማሻሻያ ፍኖተ ካርታ ጋር ማጣጣም፤
    - ለአርሶ አደር ማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርአት ግብአት ማሟላት፤
    - የከተማ ማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርዓት የሪፖርት ስርዓት መዘርጋት፤
    - በማህበረሰብ ጤና መረጃ ስርዓት ላይ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- **የኤሌክትሮኒክስ የማሕበረሰብ የጤና መረጃ ስርዓት (eCHIS) ትግበራ ማጠናከርና ማስፋፋት፤**
    - የeCHIS ትግበራ ባልጀመሩ ወረዳዎችና ጤና ኬላዎች ማስጀመር፤
    - eCHISን ተጠቅመው ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ኬላዎችን ማስፋፋት፤
    - የከተማ eCHIS ትግበራ በጤና ሚንስቴር በበለጸገዉ ሞጁል ላይ ስልጠና መስጠትና ማስጀመር፤
    - የማሕበረሰብ እና የተቋም መረጃዎች በአንድ የመረጃ ቋት እንዲገኙ የማድረግ ስራን (eCHIS ከDHIS2 Interoperable) መተግበር፤
    - በፌደራል የተዘጋጀዉን eCHIS Dash board atg$^2$bR$^3$ aešqMን በክልሉ ìS¨¨T፤
    - ለክትትል እና ድጋፍ የሚረዳ አሰራር ትግበራን መደገፍ፣ መረጃዎች እንዲመጡ መከታተል እና የሚመነጨውን መረጃ ተጠቃሚነት ማሳደግ፤
- **በጤና መረጃ ስርአት ላይ የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተሳትፎን ማሳደግ (CBMP)፤**
    - በCBMP የታቀፉ ወረዳዎችና ጤና ተቋማትን በIR ሞዴል ማድረግ፤
    - CBMP ዩኒቨርሲቲ በጤና መረጃ ስርአት ላይ ጥናት እና ምርምር እንዲያከናውኑ ድጋፍ ማድረግ፤
    - በተዘጋጀው የሜንተሪንግ የአጭር ጊዜ ስልጠና ካሪኩለም መሰረት ስልጠናዎችን እንድሰጡ ማድረግ፤
    - በCBMP ዩኒቨርሲቲ የHIS  ቅድመ ስራ ስልጠና በጋራ ማጠናከር፤
    - የCBMP ዩኒቨርሲቲ አፈጻጸም ከጤና ሚንስቴር ጋር መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፤
    - የግልና የመንግስት ሆስፒታሎችን በHIS ዙሪያ መደገፍ፤
- **የጤና መረጃ ስርአት አስተዳደርን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
    - በጤ/ሚንስቴር የወጣዉን የHIS ፖሊሲና የተጠያቂነት ማዕቀፍ በክልል ደረጃ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፤
    - የጤና አገልግሎት ደንብ እና አዋጅ ውስጥ የጤና መረጃ ስርአቱን ምዕራፎች ማስተግበር፤
    - የጤና መረጃ አስተዳደር መዋቅር ማጠናከር፤
    - በሁሉም የጤና መረጃ ስርአት ስታንዳርዶቹ መሰረት መተግበሩን  መከታተልና ማረጋገጥ፤
- **የጤና መረጃ ስርአትን ማዘመንና ማጠናከር፤**
    - ወረዳ መሰረት ያደረገ ዕቅድ ማቀጃ ሶፍትዌርን በተዋረድ እስከ ጤና ተቋማት ድረስ ለመተግበር ዝግጅት ማድረግ፤
    - በዲጅታል ጤና ቡድን የተዘጋጀዉን  ማኑዋል እና ኦዲዮ ቪዧል  መጠቀም፤
    - በተዘጋጀው ሶፍትዌር ላይ በተዋረድ እስከ ጤና ተቋማት ድረስ ለባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
    - የዘርፉን ወረዳን መሰረት ያደረገ ዕቅድ በተዘጋጀው ሶፍትዌር ማዘጋጀት፤

- የባለሙያዎችን የዲጂታል መረጃ ስርአት አጠቃቀም ክህሎት ማጎልበት፤
- ለዲጂታል ጤና መረጃ ስርአት ግብአት ማሟላት፣
- የዘርፈ ብዙ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃ ስርዓት (MRIS) መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፣

- **የክትትል፣ ምዘና ጥናትና ምርምር ስራዎች ማጠናከር፤**
    - የጥናትና ምርምር ስራዎች ከተለያዩ ፕሮግራም ባለቤቶች ጋር በማቀናጀት ማከናወን፤
    - የክትትል ስርዐት የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፤
    - የጤና መረጃ አጠቃቀም የአፈጻጸም መመሪያን መተግበር፤
    - የምዘና ጥናቶችን ለመተግበር የሚያስችል አቅም ግንባታ ስራ መስራት፤
    - የጥናትና ምርምር ስራዎች የትኩረት አቅጣጫዎችን መለየት፣
- **የጤና መረጃ አያያዝ፣ ጥራትና አጠቃቀምን በመንግስትና በግል ጤና ተቋማት ላይ ትግበራዉን ማጠናከር፤**
    - የጤና መረጃ አያያዝ፣ ጥራትና አጠቃቀም ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
    - የጤና መረጃ ጥራት እና አጠቀቃም መተግበር፤
    - ለጤና መረጃ አያያዝ የሚዉሉ ግብዓቶችን ማሟላት፤
    - የግል ጤና ተቋማት የመረጃ ስርዓት የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፤
    - የግል ጤና ተቋማት የመረጃ ስርዓት አፈጻጸም የክትትል ስራ መስራት፤
    - የግል ጤና ተቋማት በጤናው ዘርፍ አፈጻጸም የሚያሳይ ትንታኔ መስራት፤

## 7. የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደርን ማሻሻል

**ዒላማ**

- የጤና ባለሙያ ለ1,000 ሕዝብ ጥመርታ ከ 2.22 ወደ 2.3 ማድረስ፤
- ሀኪም እና ስፔሻሊስት ለ10,000 ህዝብ ጥመርታ ከ 0.83 ወደ 1.29 ማድረስ፤
- ጤና መኮነኖች ለ10,000 ህዝብ ጥመርታ ከ 1.70 ወደ 1.9 ማድረስ፤
- ነርሶች ለ10,000 ህዝብ ጥመርታ ከ ከ 7.6 ወደ 8.5 ማድረስ፤
- አዋላጅ ባለሙያዎች ለ10,000 ህዝብ ጥመርታ ከ 1.5 ወደ 1.8 ማድረስ፤
- የሚጠበቀውን የሰው ሀይል መስፈርት ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን ከ54% ወደ 64%

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በጤና ተቋማት የሚሰጥ የተግባር ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምን ማጠናከር፣**
    - የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትና የአካዳሚክ ትስስር ማሻሻል፤
    - ለጤና ባለሙያዎች የፕሪሴፕተርሺፕ ስልጠና መስጠት፤
    - በተመረጡ ጤና ተቋማት አጋዥ መፅሐፍት እና የክህሎት መለማመጃ ግብዓት ማሟላት፤
    - ለተመረጡ 4 (ሆኮ፣ ኛማ፣ ዳማባንቆ እና ጫፌ ኮትጃዌሳ)ጤና ጣቢያዎች የድንገተኛ ቀዶ ጥገና ባለሙያ ማሰልጠን/መመደብ፡
- **የጤና ሙያዎችን ሙያ ደረጃ (Qualification Framework) ማጠናከር፤**
    - ለጤና ሳይንስ ሙያዎች የብቃት ማእቀፍ ማዘጋጀት፤

- በፊልድ ኢፒዲሞሎጂ ፕሮግራም የተማሪዎችን ቅበላን ማስተባበር እና የፊልድ ኢፒዲሞሎጂ ስልጠና ፕሮግራምን ማሰተባበር፤
- በፊልድ ኢፒዲሞሎጂ የስልጠና ፕሮግራም የመጡ ለውጦችን ለማወቅ ከፌደራል ጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ጥናት ማድረግ፤

- **የህክምና ስፔሻሊቲና ሰብስፔሻሊቲ ስልጠና ፕሮግራም ማጠናከር፤**
    - የህክምና ስፔሻሊቲ ስልጠና በተመረጡ ፕሮግራሞች የጥራት ኦዲት ማስተባበር፤
    - የህክምና ሰብስፔሻሊቲ ስልጠና ፕሮግራም ማስተባበር፤
    - በጤና ሚኒስቴር ስፖንሰር የተደረጉ የስፔሻሊስት ሀኪሞችን የስራ ምደባ ድጋፍ ማድረግ ማካሄድ፤
    - የስራ አፈጻጸም እና አገልግሎት መሰረት ያደረገ የህክምና ስፔሻሊቲ ፕሮግራም ቅበላ ስርዓትን መተግበር፤
    - የህክምና ስፔሻሊቲ ስልጠና (ERMP) በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያመጣውን ለውጥ ለማወቅ ከፌደራል ጤና ሚኒስቴር ጋር በመሆን ጥናት ማድረግ፤
- **የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓት ማጠናከር፤**
    - የሙያ ፈቃድ እድሳትን ከተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ስርዓት ጋር ማስተሳሰር፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የድጋፍ፣ ቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት ማሻሻል፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ዳይሬክቲቭ እና ማስፈጸሚ መመሪያ መከለስ፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ዳታቤዝ (የመረጃ ቋት) ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ እና ተግባራዊ ማድረግ፤
    - የገጽ ለገጽ እና የበይነ መረብ ስልጠና ውጤታማነት ተአማኒነት ላይ ጥናት ማካሄድ፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ፕላትፎረም ማሻሻል፤
    - የበይነ መረብ ስልጠና ደረጃ ማስጠበቂያ ቼክሊስት ማዘጋጀት፤
    - አመታዊ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መድረክ ማዘጋጀት፤
- **የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅርቦትን ማጠናከር፤**
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎችን ማሳደግ፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የሙያ ዓይነት የብቃት ይዘቶች ስርዓት መዘርጋት፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ የኦንላይን ስልጠና ሞዳሊቲ ማስፋፋት፤
    - የአመራርነት ማፍሪያ ስልጠና ማስተባበር፤
- **ለተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት የሚውል ሃብት ማሰባሰብ**
    - በተለያዩ አጋር አካላት የሚሰጡ ስልጠናዎችን ወደ ስርዓቱ ማስገባት፤
    - የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎች የሚጠቀሙበት ወጥነት ያለው ፋይናንሻል ማንዋል ማዘጋጀት፤
    - የስራ ላይ ስልጠና የሚሰጡ አጋር ተቋማትን ከተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ አቅራቢዎች ጋር ማስተሳሰር፤
- **በጤና ተቋማት ያሉ የመማማሪያ መድረኮችን ወጥነት ባለው መልኩ ማጠናከር**
    - የምድብ ሁለት የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ተግባራት ትግበራን በጤና ተቋማት ማጠናከር
    - ከተቋማት ጋር ያለውን የሪፖርት ስርዓት የማጠናከር ስራ መስራት፤
- **ለጤናው ዘርፍ ሰራተኞች የማትጊያ ስርዓት መዘርጋትና ትግበራዉን ማጠናከር፤**
    - ለጤናው ዘርፍ ሰራተኞች ማትጊያ መመሪያ ማጠናቀቅና ትግበራውን ማስተባበር፤
    - በጤና ተቋማት የተረኛ ባለሙያዎችን ማደሪያ ክፍሎችን እድሳት ማጠናከርና መከታተል፤

- በጤና ተቋማት የሪፌረሽመንት ኮርነሮችን ጋር ተቀናጅቶ መሥራት፤
- የጤና ሰራተኞች የረጅም ጊዜ የትምህርት እድል ማመቻቸት፤

- **ከጤናው ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር፤**
  - የጤና ባለሙያዎች ሳምንት ማዘጋጀትና ማስተባበር፤
  - ከጤና ሙያ ማህበራት ጋር የጋራ የስራ አፈጻጸም ምክክር ማከናወን፤
  - ክልል ጤና ቢሮ ከኮሌጆችና ከትምህርት ተቋማት ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ ምክክር መድረኮችን ማካሄድ፡
- **በጤናው ዘርፍ የስራ ምዘናና እና ደረጃ አሰጣጥ ስራ ማስተባበርና ማጠናከር፤**
  - ያልተመዘኑ የጤና የስራ መደቦች ከተቋማት በተጠየቁ ጥያቄዎች እና በመስራያ ቤቱ ፍላጎት መሰረት መለየት፤
  - ለሲቪል ሰርቪስ በማቅረብ ያልተመዘኑ የስራ መደቦችን እንዲመዘኑ ወይም ቀድመው ከተመዘኑት ጋር እንዲዛመዱ ማድረግ፤
  - የጤና ባለሙያዎችን እና የጤና ስራ አመራር የቫሊዴሽን ስራ መስራት፤
  - የተመዘኑ የስራ መደቦች የስራ ዝርዝር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤
  - ለባለድርሻ አካላት ስለ ስራ ምዘና እና ደረጃ አሰጣጥ ስራ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መስራት፣
- **የሰራተኞችን ጥቅማ ጥቅም ወቅታዊነት በማሻሻል የስራ ተነሳሽነትን ማሳደግ፤**
  - ሰራተኞች ሊያገኟቸው የሚገቡ ማበረታቻ ፓኬጅ ማዘጋጀት፤
  - ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መሰረት በማድረግ የእውቅና ፕሮግራም ማድረግ፤
  - የጡረታ መለያ ቁጥር ለሌላቸው በበጀት ዓመቱ እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - በበጀት ዓመቱ የእድገት መሰላል ተጠቃሚ የሚሆኑ የጤና ባለሙያዎች ጊዜውን ጠብቆ ተግባራዊ ማድረግ፤
  - የተከለሰውን የጤና ሴክተር የማበረታቻ መመሪያ ትግበራዉን መከታተል፤
- **የሰው ሀብት መረጃ ሥርዓት በዘመናዊ መልኩ ዲጂታላይዝ በማድረግ ለውሳኔ ሰጪ አካላት ተደራሽ ማድረግ፤**
  - የጤናው ዘርፍ የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት (HRIS) በክልል እና በተጠሪ ተቋማት በተጨማሪም በወረዳዎች ማስተግበርና አፈፃፀሙን መከታተል፤
  - ክልላዊ የጤናው ዘርፍ የሰው ሃብት መረጃ ቋት (Regional Health Workforce Accounts (RHWA)) ትግበራ ማስተባበር፤
  - የጤና ዘርፍ የሰው ሃብት ስትራተጂ እቅድ ማዘጋጀትና ትግበራን ማስተባበርና መከታተል፣
  - የጤና ባለሙያዎች ያለበትን የፍልሰት ምጣኔ መረጃ ማጠናከር፤
  - የመ/ቤቱን የሰው ሀብት መረጃ በማዘመን ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ማደራጀት፤
  - የሰው ሀብት መረጃን ለውሳኔ ሰጪ በሚያመች መልክ ማዘጋጀት፤
  - ለአጠቃቀም የተዘጋጀ መረጃ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ሲቀርብ አረጋግጦ መስጠት፤
  - ለዞኖች፤ ለወረዳዎች፤ ተጠሪ ተቋማት እና የጤና ትምህርት ተቋማት በቅጥር፣ በዝውውር፣ በደረጃ እድገት፣ በምደባ እንዲሁም አጠቃላይ የሰው ሀብት አሰራሮች ላይና መረጃ አያያዝ ላይ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ እና በተገኘዉ ውጤት ላይ ምክክር ማድረግና ማስተካካያ እያደረጉ መሄድ፤

- የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች የዓመት እረፍት የሚወጡበትን ፕሮግራም መያዝ፣ መቀነስ፣ ለስራ ክፍሎች ማሳወቅ፤
- የመስሪያ ቤቱን የሰው ሀብት መረጃ ማዘመንና በመረጃ ላይ የተደገፈ ለውሳኔ ሰጪነት ዝግጁ ማድረግ፤
- በመረጃ አሠራርና አያያዝ ላይ መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ተግባራዊ ማድረግ፤

## 8. የጤና መሰረተ ልማት ማሻሻል

**ዒላማ፤**

- በግንባታ ላይ ያሉ ሁሉም ጤና ጣብያዎችን አሁን ካሉበት አማካኝ 63% ወደ 100% ማድረስ፤
- በግንባታ ላይ ያሉ ፋርማሲ ብሎኮችን አሁን ካሉበት አማካይ 60% ወደ 100% ማድረስ፤
- የተቋረጠውን የጣራቱ የጤና ባለሙያዎች ማደሪያ በአዲስ ውል ስራ ማስጀመርና 50% ማጠናቀቅ፤
- የቦና ሆስፒታል በመጀመሪያ ውል ላይ ተካቶ ያልተጀመሩ ብሎኮችን አዲስ ጨረታ አውጥቶ ስራ ማስጀመርና 25% ማጠናቀቅ፤
- የአላሙራ ሆስፒታል G+3 ብሎክ ግንባታን አሁን ካለበት 30% ወደ 70% ማድረስ፤
- የለኩ ሆስፒታል G+3 ብሎክ ግንባታን 30% ወደ 70% ማድረስ፤
- ይርጋለም ሪጅናል ላብራቶሪ አሁን ካለበት 85% ወደ 100% ማድረስ፤
- በጤና ተቋማት ውስጥ የሚገነቡ የተለያዩ ግንባታዎች አሁን ካሉበት አማካኝ 50% ወደ 100% ማድረስ፤
- የአዋየ-ቀራሮ እና ሩፎ ጫንጮ ጤና ጣብያዎች ግንባታ ስራ ማስጀመርና 50% ማድረስ፤
- ዕድሳትና ጥገና ለሚያስፈልጋቸዉ ጤና ጣብያዎች ለይቶ ጥገናዉን 100% ማጠናቀቅ፤
- የጤና ጣብያዎች ውሃ አቅርቦት አሁን ካለበት 75% ወደ 80% ማድረስ፤
- የጤና ጣብያዎችን የመብራት አቅርቦት አሁን ካለበት 80% ወደ 85% ማድረስ፤
- የጎርቼ ኮምፓክት የመጀመሪያ ሆስፒታል ግንባታ ጀምሮ 25% ማድረስ፤
- የመጸዳጃ አገልግሎት ያላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን ከ59% ወደ 70% ማድረስ፤
- የሆማቾ ጫዋ 2ኛ ጤና ኬላ ወደ ኮምፕርሄንሲቭ ጤና ኬላ ማሰደግ 50% ማድረስ፤
- ሁለት አዲስ ኮምፕርሄንሲቭ ጤና ኬላ ማስገንባት እና 30% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **ለጤና ተቋማት የኤሌክትሪክ ሃይል እና የውሃ አቅርቦትና አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን ማጠናከር፤**
  - የጨረታ ሂደት ማከናወን፤ የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ግምገማ ሂደት መስራት፤
  - አሸናፊ ስራ ተቋራጭን በመለየት የውል ስምምነት ሰነድ መፈራረም እና የግንባታ ቦታ ማስረከብ፤

- የቅድመ ክፍያ ሂደት ማከናወንና የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሂደት ማከናወን፣
- ለሚቀርቡ የግንባታ ግብአቶች አስፈላጊውን የጥራት ቁጥጥር ማከናወን፣
- በስራ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ክፍያዎችን መርምሮ ማረጋገጥ፤
- ርክክብ መፈጸም፤

▪ **ሁለተኛ ደረጃ/ኮምፕረንስቭ ጤና ኬላዎች ግንባታ ስራዎች ማኀልበት፤**

- የጨረታ ሂደት ማከናወን እና የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ግምገማ ሂደት መስራት፤
- አሸናፊ ስራ ተቋራጭን በመለየት የውል ስምምነት ሰነድ መፈራረም እና የግንባታ ቦታ ማስረከብ፤
- የቅድመ ክፍያ ሂደት ማከናወንና የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሂደት ማከናወን፣
- ለሚቀርቡ የግንባታ ግብአቶች አስፈላጊውን የጥራት ቁጥጥር ማከናወን፣
- በስራ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ክፍያዎችን መርምሮ ማረጋገጥ፣
- በግንባታ ሂደት ላይ ለሚከሰቱ ችግሮችና እንቅፋቶች መፍትሄ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- የመጀመሪያ ዙር ርክክብ መፈጸም እንዲሁም የመጨረሻ ዙር ርክክብ መፈጸም፤

▪ **አዲስ ጤና ጣቢያዎች ግንባታ ክትትልና የቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር፤**

- የጨረታ ሂደት ማከናወን እና የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ግምገማ ሂደት መስራት፤
- አሸናፊ ስራ ተቋራጭን በመለየት የውል ስምምነት ሰነድ መፈራረም እና የግንባታ ቦታ ማስረከብ፤
- የቅድመ ክፍያ ሂደት ማከናወንና የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሂደት ማከናወን፣
- ለሚቀርቡ የግንባታ ግብአቶች አስፈላጊውን የጥራት ቁጥጥር ማከናወን፣
- በስራ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ክፍያዎችን መርምሮ ማረጋገጥ፣
- በግንባታ ሂደት ላይ ለሚከሰቱ ችግሮችና እንቅፋቶች መፍትሄ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- የመጀመሪያ ዙር ርክክብ መፈጸም እንዲሁም የመጨረሻ ዙር ርክክብ መፈጸም፤

## 9. የጤና ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል

**ዒላማ፤**

- ከአጠቃላይ መንግስት በጀት የጤና ዘርፍ ድርሻ አሁን ካለበት 12% ወደ 16% ከፍ ማድረግ፤
- የማአጤመ አገልግሎት የጀመሩ ወረዳዎች ሽፋን አሁን ካለበት 93% ወደ 100% ማድረስ፤
- የአባውራ/እማውራ የማአጤመ የአባልነት ሽፋን ከ64% ወደ 85% ማሳደግ፤
- የማህበራዊ ጤና መድህን የአባልነት ሽፋን ከ64% ወደ 85% ማድረስ፤
- የእድሳት ምጣኔ ከ82% ወደ 100% ማሳደግ፤
- የተናጥል ድጎማ አሁን ካለበት 38% ወደ 70% ማሳደግ፤
- ኦዲት የሚደረጉ እስኪሞች አሁን ካለበት ከ52% ወደ 85% ማሳደግ፤
- አጠቃላይ ድጎማ አሁን ካለበት ከ10% ወደ 25% ማሳደግ፤
- ተመላላሽ ታካሚዎች የነፍስ ወከብ የጤና ተቋማት ግብኝት ከ1.2 ወደ 1.5 ማድረስ፤
- የክለም ኦዲት ምርመራ የተደረገላቸዉ የጤና አገልግሎት ክፍያ ጣያቂዎች ባሉበት 100% ማቆየት፤

- ዉል በገቡ የጤና ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት አሁን ካለበት ከ80% ወደ 85% ማሳደግ፤
- የአባላት ወይም ተጠቃሚዎች እርካታ መጠን ከ80% ወደ 90% ማድረስ፤
- መክፈል ለማይችሉ ማህበረሰብ ክፍሎች በወረዳ 30% በክልሉ 70% በድምሩ 100% በመመደብ ወደ ማዕጤመ ቋት ማስገባት፤
- የማዕጤመ ጠቅላላ ጉባኤ አሁን ባለበት 100% ላይ ማቆየት፤
- መክፈል የማይችሉ ወይ የድሃ ድሃ ምልመላ አሁን ካለበት ከ11% ወደ 18% ማሳደግ፤
- የክለም ኦዲት አሁን ካለበት ከ70% ወደ 85% ማድረስ፤

## ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት

- **ውጤትን መሰረት ያደረገ የፋይናንስ ስርዐት ትግበራ ማጠናከር፤**
  - ውጤትን መሰረት ያደረገ የፋይናንስ ስርአት መተግበርና ማስቻል፤
  - የጤና ባለሞያዎች ማበረታታትና ትጉህ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤
  - የጤና ተቋማትን አቅም ማጎልበትና የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ማስቻል፤
  - የተሻለ የጤና አገልግሎት ጥራት ዉጤት ለማስመዝገብ የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- **በክልል ደረጃ ሁሉን አቀፍ የጤና መድህን ሽፋንን ማጠናከር፤**
  - በወረዳዎች እና በከተማ አስተዳደሮች የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሰረት የማአጤመ ወረዳዎችን ሽፋን ለማሳደግ ሊያሰራ የሚችል ማንዋል ማዘጋጀት፤
  - የክልልና የማህበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቭዥን የቅስቀሳ ሥራ በመጠቀም እስከ ቀበሌ ድረስ ንቅናቂ ሥራን ማጠናከር፤
  - የተለያዩ የመድህን ፖስተሮች እና ብሮሽር ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤
  - ከተለያዩ ሚድያዎች ጋር በማቀናጀት የማሕበረሰብ ጤና መድህን የአባላት ምዝገባና ዕድሳት ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣
  - ስለ ማህበራዊ የጤና መድህን በተለያዩ ኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያዎች ማስተዋወቅ፤
  - ስለ ጤና መድህን ተጠቃሚዎች ዶክመንተሪ ፊልም ዘገባ ተሰርቶ ማሰራጨት፤
  - በክልሉ ደረጃ የዓመቱን የጤና መድህን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ዶክመንተሪ ማዘጋጀት፤
  - ወደ አገልግሎት ዉስጥ ያልገቡ ወረዳዎችን አገልግሎት የማስጀመር ሥራ መሥራት፤
  - የጤና መድህን ሽፋንን ከፍ ለማድረግ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን እንዲጎበኙ ማድረግ፤
- **በማዐጤመ የታቀፉ ቤተሰቦች እና የነባር አባላት እድሳት ስራዎች ማጠናከር፤**

- በክልሉ የአባላት ማፍራት ወቅት ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች በወቅቱ የንቅናቄ ስራ ማከናወን፤
- ክልላዊ ኮንፈረንስ ለማዘጋጀት ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና የሚመለከተዉን አካላት የበጀት ድጋፍ መጠየቅ፤
- የወረዳ አመራር ስምሪት ወስዶ የአባላት ምዝገባና እድሳት ሥራ በንቅናቄ እንዲሰራ ማድረግ፣
- በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አባልነት መታቀፍ የሚገባቸው ዜጎች በሙሉ አባል እንዲሆን ለማድረግ የወረዳ እና ከተማ አስተዳደሮች ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ሰነድ ማዘጋጀትና መከታተል እና አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፤
- የወረዳ እና የከተማ የአባላት ምጣኔ አፈጻጸም ግምገማ እንዲካሄድ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
- የጤና መድህን አባላት እድሳት የሚያቋርጡበት ምክንያት ለማወቅ ክልላዊ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- ከድህነት ወለል በታች ያሉ ቤተሰቦች አግልግሎት አንዲያገኙ ተቀናጅቶ መስራት፤
- በአገልግሎት ጊዜ ከኪስ የሚከፍሉ አባላት ምጣኔ እንዲቀንስ ጥረት ማድረግ፤

- **የጤና መድህን ፋይናንስ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉትን ጥረቶች ማጠናከር፤**
  - ከከፋይ አባላት የሚሰበሰብ የመዋጮ ገንዘብ በወቅቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሰበሰብ ክትትል ማድረግ፤
  - አማራጭ የሆነ የአባላት መዋጮ አሰባሰብ ስርዓት ለመዘርጋት የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፤
  - የተናጠል ድጎማ ገቢ ከፍ አንዲል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፤
  - የወረዳ ደሀ ደሀ ድጐማ በወቅቱና በበቂ መጠን ገቢ መሆኑን መከታተልና በመረጃ እንደረጋገጥ ማድረግ፤
  - ለወረዳዎች የ2016 የክልል ድጎማ(70%) በማስላት እንዲተላለፍ ማድረግ፤
  - ከአባላት የምስበሰብ መዋጮ ሙሉ በሙሉ ወደ ማዕጠም ሂሳብ ቁጥር ገቢ መሆኑን በየወሩ መከታተልና ማረጋገጥ፤
  - የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር የማአጤመ ስኪም የጤና ተቋማት አገልግሎት ክፍያን ወጪ በተገቢዉ መረጃ የመሰብሰብ እና እንዲሁም የቅርብ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤
  - የማዐጤመ የጋራ ቋት በክልሉ ባሉ ክላስተሮች እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ማድረግ፤
  - የማዐጤመ ወረዳዎች አመታዊ የፋይናንስ ኦዲት እንዲያደርጉና አፈጻጸማቸዉን ክትትል ማድረግ፤

- የክሌም ኦዲት የሚደረግላቸው የጤና አገልግሎት ተቋማት ልየታ ማድረግና ሥራዉን ማጠናከር፤

- **ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ፍትሃዊ አጠቃቀምን ማሻሻል፤**
  - ለከፋይ እና ከፍሎ መታከም ለማይችሉ የጤና መድህን አባላት በሙሉ መታወቂያ እንዲዳረስ ማድረግ፤
  - የተመላላሽ ታካሚዎች የነፍስ ወከፍ የጤና ተቋማት ጉብኝት እንዲደረግ ጥረት ማድረግ፤
  - ውል በገቡ የጤና ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት እንዲኖራቸዉ ክትትል ማድረግ፤
  - የተሻለ ደረጃ ላይ ያሉ ጤና ተቋማት ዝቅተኛ መስፈርት ያሟሉ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፤
  - የቅሬታ አፈታት የአሰራር ስርአት ተግባራዊ ያደረጉ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የመለየት ስራ መስራት፤
  - የአባላትን / ተጠቃሚዎችን እርካታ የዳሰሳ ጥናት መስራት፤
- **የጤና መድህን ስርዓት የመፈጸም አቅምን ማጠናከር፤**
  - ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች የማዕጠመ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂዱ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
  - በወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች የማዕጠመ ቦርድ ስብሰባ በየሩብ ዓመት እንዲካሄድ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
  - ለማዕጤመ ቦርድ አባላት የአጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠና የመስጠት ስራ መስራት፤ የቅርብ ክትትል ማድረግ፤
  - በአፈጻጸም ዙሪያ ሪፖርት ድጋፍ፤ ክትትልና ግምገማ መድረኮችን ማመቻቸት፤
  - ከባለድርሻ አካላት ጋር ዕቅዱን የጋራ በማድረግ የምክክር መድረክ ማካሄድ፤
  - የማዕጤመ ኦዲት ሥራ በወረዳዉ ፋይናንስ እንዲሠራ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤
  - ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚፈልጉ አካቶ ስራዎችን ማከናወን፤
  - የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች ማከናወን፤

## 10. አመራር እና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል

**ዒላማ፡-**

- የማህበረሰብ አስተያየት ምዘና ሥርዓት ተግባራዊ ያደረጉ ወረዳዎች ወደ 100% ማድረስ፤
- የማህበረሰብ አስተያየት ምዘና ሥርዓት ተግባራዊ ያደረጉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ (ጤና ጣብያዎች) ሽፋን ከ95% ወደ 100% ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በጤናው ዘርፍ የማህበራዊ ተጠያቂነት አሰራርን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
- **መልካም አስተዳደርን ማሻሻልና ማጠናከር፤**

- የዘርፋን የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ በማዘጋጀት ወደ ተቋማት እና የስራ ክፍሎች ማውረድ፤
- የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ ደሰሳ በተካሄደባቸው ሆስፒታሎች የመጡ ለውጦችን በሚመለከት የደሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- የውጭ ተገልጋዬች ቅሬታ አፈታት ስርአትን በዘመናዊ መንገድ ማከናወን፤
- የውጭ እና የውስጥ ተገልጋዬች እርካታ ዳሰሳ ማካሄድ፤

- **የለውጥ መሳሪያዎችን ትግበራ ማጠናከር፤**
  - በሁሉም የስራ ክፍሎች የዜጐች ቻርተር ተግባራዊ ማድረግ፤
  - በሆስፒታሎች የካይዘን ትግበራ ማጠናከርና ማስጀመር፤
  - የአገልግሎት ማሻሻያ ጥምረት ፎረሞች አፈጻጸም ትግበራወን ማካሄድ፤

## 11. የጤና ዲጂታል ቴክኖሎጂን ማሻሻል

**ዒላማ**

- በጤና ሚንስቴር 3 አዲስ/የተሻሻለ ዲጂታል መሳሪዎች ለምቶ የመጣውን ቴክኖሎጂ መተግበር፤
- ዲጂታል ጤና መረጃ ሲስተሞችን ተግባራዊ በማድረግ 1 ወረቀት አልባ ማሳያ ወረዳ ማስጀመር፤
- EMR ትግበራን በተጀመሩ 3 ሆስፒታሎች (አዳሬ፤ ቱላና ለኩ) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እና አዳዲስ በ3 ሆስፒታሎችና በ2 ጤ/አ/ጣቢያዎች ማስጀመር፤
- DHIS2 offline ትግበራን ከ75% ወደ 100% ማድረስ፤
- DHIS2 online ሽፋንን ከ16% ወደ 85% ማሳደግ፤
- eCHISን የተገበሩ ጤና ኬላዎች ሽፋን ከ45% ወደ 63% ማድረስ፤
- DAGU ትግበራን በተቋማት ከ23% ወደ 30% ማሳደግ፤
- የ eAPTS ትግበራን በ5 አጠቃላይ ሆስፒታሎች እና በ2 ጤ/አ/ጣቢያዎች ማስጀመር፤
- የ VPN ሽፋንን ከ16% ወደ 50% ማሳደግ፤
- የ i-HRIS ትግበራን በሁሉም ዞኖች፤ ወረዳዎች እና ሆስፒታሎች ማስጀመር፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የተተገበሩ የዲጅታል የጤና ሥርዓትን ዘላቂነት ማጠናከር፤**
  - በክልል ደረጃ የኤሌክትሮኒክስ የጤና መረጃ ስርዓት ትግበራ መከታተል፤
  - ማስተር ፋሲሊቲ ሪጂስትሪ ወቅታዊ ማድረግ፤ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
  - ኤሌክትሮኒክ ኦዲቴብል ፋርማሲዩቲካል ትራንሳክሽን ስርዓት ትግበራን ማስፋፋት፤

- **አዳዲስ እና ዘመናዊ የዲጂታል ሄልዝ ሲስትሞችን የፍላጎት ዳሰሳ እና የማላመድ ስራዎችን ማጠናከር፤**
    - ለአዳዲስ ዘመናዊ ዲጂታል ሲስተሞች የፍላጎት ዳሰሳ ማድረግ፤
    - ነባር ዲጅታል ሲስተሞችን ማሻሻል፤
    - ከጤ/ሚንስቴር ጋር የለሙ ሲስተሞችን በጋራ ፍተሻ ማድረግ እና መተግበር፤
- **በሆስፒታልና ጤና ጣቢያዎች የElectronic Medical Record(EMR) ሲስተም ትግበራን ማጠናከር፤**
    - አዳዲስ የሚተገበርባቸውን ጤና ተቋማት መለየት፤
    - በጤና ተቋማቱ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን በኔትዎርክ ማገናኘት፤
    - የ ICT መሣሪያዎች ግብዓቶችን ማሟላት፤
    - የኤሌክትሮኒክ የጤና መዝገብ ስርአት መተግበሪያን ለተጠቃሚዎች ማላመድ እና ስልጠና መስጠት፤
- **የኤሌክትሮኒክ ማሕበረሰብ የጤና መረጃ ሥርዓትን (eCHIS) ማዘመን፤ ማጠናከርና ትግበራ ማስፋፋት**
    - በተመረጡ ፕሮግራሞች ላይ በመመስረት ነባር እና አዳዲስ የ eCHIS ሞጁሎችን ከጤ/ሚንስቴር ጋር በመሆን ማሻሻልና ማልማት፤
    - በተመረጡ የጤና ኬላዎች ላይ የeCHIS ትግበራ ማስፋፋት፤
    - eCHIS ከሌሎች የዲጂታል ጤና ስርዓቶች ጋር ማናበብ፤
- **በኤሌክትሮኒክስ ኦዲት ሊደረግ የሚችል የመድኃኒት ግብይት ሥርዓት መዘርጋት (eAPTS)**
    - በተመረጡ የጤና ተቋማት የ eAPTS ትግበራን ማስጀመርና ማስፋፋት፤
    - ከEMR እና DHIS2 ሲስተሞች ጋር በማናበብ መጠቀም፤
- **በመረጃ ላይ የተመሰረተ የጤና አጠባበቅና ውሳኔ አሰጣጥን ለማቀድ፣ ለመከታተል እና ለመደገፍ የዲስትሪክት የጤና መረጃ ስርዓት (DHIS2) ማጠናከር**
    - የተሻሻለዉን DHIS2 ሲስተም መጠቀም እና በክልል ደረጃ ተጨማሪ የሲስተም ፍላጎቶችን መለየት፤
    - DHIS2 ከሌሎች የጤና መረጃ ስርዓቶች ጋር ማናበብና አቀናጅቶ መጠቀም፤
    - መልቲ ሴክቶራል የወረዳ ትራንስፎርሜሽን መረጃ ስርዓት ትግበራን ማስጀመር፤
- **የዲጅታል ህክምና ግብዓት አቅርቦት እና አስተዳደር ስርዓት መተግበርና ማስፋፋት፤**
    - በስራ ላይ ያለውን የeLMIS የጤና መረጃ ስርዓት መተግበርና ማጠናከር (Dagu2,..)፤
    - ክልላዊ የህክምና መሳሪያዎች መረጃ ስርዓት (MEMiS) ትግበራ ማጠናከር፤
    - ከሌሎች የዲጅታል ጤና መረጃ ስርዓቶች ጋር ማናበብ፤
    - የመረጃ ትንታኔ እና ምስላዊ ዳሽቦርድ ማልማትና መተግበር፤

- **የኤሌክትሮኒክስ የሰው ኃይል መረጃ ስርዓት (i-HRIS) መተግበርና ማስፋፋት፤**
    - የበለፀገዉን ኤሌክትሮኒክስ የሰው ኃይል መረጃ ስርዓት ማስጀመር፤
    - ኤሌክትሮኒክስ የሰው ኃይል መረጃ ስርዓት ትግበራዉን መከታተል፤
    - የሰው ኃይል መረጃ ስርዓትን ከሌሎች ሲስተሞች ጋር ማናበብ፤
- **በጤና ተቋማት መካከል የኤሌክትሮኒክ ሪፈራል መረጃ ስርዓትን (eRefIS) መተግበር፤**
    - የኤሌክትሮኒክ ሪፈራል መረጃ ስርዓት ሲስተምን ማስጀመር፤
    - ከሌሎች የዲጅታል ጤና መረጃ ስርዓቶች ጋር ማናበብ፤
- **የድንገተኛ ህክምና ምላሾችን ለማስተዳደር የኤሌክትሮኒክስ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት አስተዳደር ሥርዓት ማስጀመርና ማጠናከር፤**
    - የኤሌክትሮኒክስ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት አስተዳደር ሥርዓት መተግበር፤ (Ambulance Dispatching System(ADS)፤
    - ከሌሎች የዲጅታል ጤና መረጃ ስርዓቶች ጋር ማናበብ፤
- **ዲጂታል ጤና ስርዓቶች የጋራ አገልግሎቶችን ማበልጸግ (Shared Services)ና ማጠናከር፤**
    - የፋሲሊቲ መዝገብ ስርዓትን /MFR/ ማሻሻልና ማስፋፋት፤
    - ብሄራዊ የጤና መረጃ ስርዓት መዝገበ-ቃላት (NHDD) መተግበር፤
    - የጤና ተቋማትን ጂኦ ስፓሻል መረጃ ማካማቻ ስርዓት መተግበር፤
- **የኤሌክትሮኒካል ዘርፈ ብዙ ምላሽ ሰጪ የጤና መረጃ እና የዲጅታል ጤና መረጃ ስታንዳርድ ትግበራን (eMRIS) ማጠናከር፤**
    - የመረጃ ስርዓቱን መተግበር እና ከDHIS2 ጋር ማናበብ፤
    - የዲጂታል ጤና ሶሉሽኖች እና አገልግሎቶች ደረጃዎች መለኪያ መስፈርት እና የአተገባበር መመሪያዎችን መተግበር፤
- **የዲጅታል ጤና መረጃ ማዕከል እና የሄልዝኔት መሠረተ ልማት ማጠናከር**
    - የኮምፒተሮች፣ ታብሌቶች፣ ዩፒኤስ እና ሌሎች የአይሲቲ መለዋወጫዎችን ማቅረብ፤
    - በሁሉም የጤና ተቋማት የኔትዎርክ መሰረተልማት መተግበሩን ማረጋገጥ፤
    - እያደገ ያለውን ፍላጎት ለማስተናገድ የመረጃ ማዕከል ማቋቋም፤
- **የዲጂታል ጤና አስተዳደር፤ የዲጂታል ማዕቀፎችን እና መሳሪያዎችን ትግበራን ማሳደግ፤**
    - የዲጅታል ጤና መረጃ መዋቅር በክልል ደረጃ እንዲኖር ማድረግ፤
    - ወቅታዊ የዲጅታል ጤና አስተዳደር ማዕቀፍ በክልል ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ፤
    - የዲጂታል ጤና መረጃ ስርዓቶች፣ ስታንዳርዶች እና መሰረተልማቶች ለታመነላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትልና ግምገማ ማድረግ፤
    - ዲጂታል ሲስተሞች ጥራት የማረጋገጥ ስራ መስራት፤

- **የዲጂታል ጤና መረጃ አስተዳደር ሰነዶች፤ የማስፈጸሚያ ስልቶች መኖራቸውን የማረጋገጥ እና በዩኒቨርሲቲ ተሳትፎን የማሳደግ (CBMP) ስራዎችን ማጠናከር፤**
  - የዲጂታል ጤና መረጃ ስርዓቶችን የማጣጣም ስራ መስራት፤
  - የተዘጋጁ የዲጂታል ጤና ስትራቴጂ ዶክመንት፣ስታንዳርዶች፤ ፖሊሲዎች እና የአተገባበር መመሪያዎችን ስራ ላይ ማዋል፤
  - የዲጅታል ጤና መረጃ ስርዓቶችን ደህንነት ማስጠበቅ፤
  - የዲጂታል ጤና መረጃ ስርዓቶች ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ የአሰራር ስልት መዘርጋት፤
  - በዲጂታል ጤና መረጃ ስርዓቶች ላይ በዩኒቨርሲቲ የአፈፃፀም ጥናት እንዲሰራ ማስተባበር እና ግብዓት ማፈላለግ፤
  - የዲጂታል ጤና መረጃ ስርዓት ቴክኖሎጂዎች ላይ ትግበራ እና አቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፤

## 12. የባህላዊ ህክምናን ማሻሻል፤

**ዒላማ፤**

- አጠቃላይ የባህላዊ ህክምና አግልግሎት የሚሠጡ ባለሙያዎች ቁጥር ከ13 ወደ 21 ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የባህላዊና ዘመናዊ ህክምና የሚቀናጅበትን ስርዓት ማሻሻል፤**
  - ከፌደራሉ መነሻ ክልላዊ የባህላዊ ህክምና ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች፣ ማዘጋጀትና ማጠናቀቅ፤
  - ከሚመለታቸዉ ባለድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት በመሆን አመታዊ እቅዶች እንዲተገበሩ ማስተባበር እንዲሁም ግምገማ እና ክትትል ማድረግ፤
  - አግባባዊ የባህል ህክምና አጠቃቀም በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን፤
  - ለባህላዊ ህክምና አዋቂዎች ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ማከናወን፤
  - የባህላዊ ህክምና አገልግሎትን የሚያሻሽሉ ጥናቶችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት ማከናወን፤
  - ባህላዊ ህክምናን ለማሻሻል ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አመታዊ የጥናት ፎረም ማዘጋጀት፤
  - ከሚመለከተዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሆን የባህል ህክምና ባለሙያዎችን እና ተቋማትን በክልል ጤና ቢሮ በኩል ምዝገባ እንዲከናወን ማድረግ፤

## 13. ጤና በሁሉም ዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መካተቱን ማረጋገጥ

**ዒላማ፡-**

- በፌደራል የተጀመረውን ጤና በሁሉም ዘርፍ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች ማካተት የሚያስችል በክልል ደረጃ 1 ሰነድ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- ከጤና ዘርፍ ጋር ዕቅዳቸውን ያጣጣሙ ሌሎች የሚመለከታቸው ዘርፎች ቁጥር ወደ 18 ማሳደግ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የፖሊሲ እና ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት አሰራር ስርዓት ማጠናከር፤**
  - በክልል ደረጃ በስትራቴጂክ እቅድ እና ፍኖተ ካርታ ፕሮቶኮል ላይ ለሰራተኛ ስልጠና መስጠት፤
  - ለዘርፉ ፖሊሲ እና ስተራቴጂ ዝግጅትና ለውሳኔ አሰጣጥ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮችን መለየት፤
  - ለስትራቴጂ ትንተና አጋዥ የሚሆኑ መረጃ ማሰባሰብ፤
  - ዘርፉ ላይ ተጽእኖ ሊያመጡ የሚችሉ እና የቅድሚያ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ስተራቴጂክ ጉዳዮችን መለየት፤
  - ከስተራቴጂ ትንተና በሚገኘው ምክረ-ሃሳብ መሰረት ቅድሚያ የሚሰጣቸው አዳዲስ እና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን የዘርፉ ፖሊሲዎች እና ስተራቴጂዎችን በቅደም ተከተል መለየት፤
  - በክልል ደረጃ የሚረቀቁ ስትራቴጂዎች ከዘርፉ ፖሊሲዎች ጋር የተናበቡና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
  - የባለድርሻ አካላት በዘርፉ ፖሊሲ እና ስተራቴጂ ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ እና አስተያየታቸዉን መያዝ፤ ለግብአትነት እንዲውሉ ማድረግ፤
  - በዘርፉ የተረቀቁ ፖሊሲዎች እና ስተራቴጂዎች እንዲተገበሩ ክትትል ማድረግ፤

## 14. የግሉ ዘርፍ በጤና ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ

**ዒላማ**

- አጠቃላይ በጤና እና ጤና ነክ የሚሰሩ የግል ዘርፍ ለመጨመር 1 ጊዜ የምክክር አወደጥናት ማካሄድ፤

**ስትራቴጂክ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **በመንግስትና የግል አጋርነት ቦርድ በፀደቁ diagnostics ዘርፎች ፕሮጀክት ትግበራ ማጠናከር፤**
  - የፕሮጀክት ትግበራ ዝርዝር እቅድ ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማዘጋጀት፤
  - የግሉ ዘርፍ ገበያ ጥናት ማካሄድ (Early Market Engagement) ፤
  - የጨረታ (Request for Qualification, Request for Proposal) እና የዉል ሰነዶች ማዘጋጀት፤

## ተጨማሪ ከተለያዩ ዘርፎች ጋር የሚሰሩ ስራዎችን በሚመለከት

### የኦዲት ስራዎች ከማጠናከር አንፃር

**ዒላማ**

- አጠቃላይ በጤና ቢሮ የኦዲት ቁጥር 4 ማድረስ፤

**ስትራቴጂክ እርመጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት**

- **የማህበረሰብን ተሳትፎ ማሻሻልና ማጠናከር፤**
    - የጤና ቢሮ የስራ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የሥጋት ዳሰሳ ማከናወን፤
    - የጤና ቢሮን ሥጋት መሰረት በማድረግ የ2016 በጀት ዓመት እቅድና በጀት ማዘጋጀት፤
    - በውስጥ ኦዲት ጠቀሜታ ዙርያ ከማኔጅመንት አባላት ጋር ውይይት ማከናወን እና በጤና ቢሮ ትኩረት በሚሹ የክትትል ኦዲት ግኝቶች ዙርያ በየሩብ ዓመቱ ውይይት ማድረግ፤
    - የዳይሬክቶሬቱን አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ማዘጋጀት፣ ማቅረብና ማስገምገም፤
- **ለጤና ቢሮ የሚሰጡ የኦዲት ሪፖርቶች ነቀፌታ የሌላቸው እንዲሆኑ ማገዝ፤**
    - የጤና ቢሮን በበጀት ዓመቱ የአላቂ እቃ ቆጠራና ፈሰስ ሪፖርት አንድ ጊዜ ማከናወን፤
    - ለጤና ቢሮ የተመደበ የመደበኛና የካፒታል በጀት ሂሳብ ሪፖርትን ተገቢነትና ትክክለኝነት በፋይናንሺያል ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፤
    - በተመረጡ የዞንና የወረዳ ጽ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኝነትና ያልተወራረደበትን ምክንያት በኦዲት ማረጋገጥ፤
    - በተመረጡ የተጠሪ ተቋማት (ኤጀንሲዎችና ሆስፒታሎች) የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኝነትና ያልተወራረደበትን ምክንያት በኦዲት ማረጋገጥ፤
    - የየፕሮግራም ሂሳቦች ለታለመላቸው ዓላማ በአግባቡ መዋላቸውን በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች በሕጋዊነት ኦዲት ማረጋገጥና ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፤
    - በዉስጥ ኦዲትና በዋና ኦዲተር የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤
    - ከግኝት የጸዳ የኦዲት አስተያየት እንዲሰጥ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤
    - የተመረጠ የአንድ አሰራር አፈጻጸምን በክዋኔ ኦዲት ማረጋገጥ፤
- **የጤናውን ዘርፍ የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል የሰው ኃይል ፍላጎት መሙላትና የባለሙያዎችን አቅም (ክህሎት) ማሳደግ፤**
    - በኦዲት ደረጃ መሰረት የሥራ ክፍሉ ባለሙዎች በተመረጡ ርዕሶች ላይ የኦዲት ጥራት ግምገማን መሰረት ያደረገ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
    - የውስጥ ኦዲት ባለሙያዎች የCIA የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
    - በየሩብ ዓመቱ የእርስ በርስ መማማሪያ መድረክ ማከናወን እና ክዋኔ ኦዲት ቡድን ክትትልና

ድጋፍ ማድረግ፤

- ለእያንዳንዱ የፋይናንሸያልና ሕጋዊነት ኦዲት ቡድን 2 ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ለተመረጡ ብዛታቸው 2 ለሆኑ የተጠሪ ተቋማት እና ሆስፒታሎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- ለተመረጡ ወረዳዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- ከዞንና ከከተማ መስተዳድር ወረዳዎች የውስጥ ኦዲተሮች ጋር የምክክር መድረክ በማከናወን የልምድ ልውውጥ በማከናወን የኦዲት ጥራትና ሽፋን ማሳደግ፤

- **የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማሻሻልና ማጠናከር፤**
    - በተመረጡ የውስጥ አሰራሮች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱንና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በኦዲት ማረጋገጥ፤

## የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ

- **የፎረሞችን ትብብርና ትስስር ማጠናከር፤**
    - ህፃናት፤ ወጣቶች፤ አካል ጉዳተኞችና ሌሎችም ማህበራዊ ዘርፎች በተመለከተ ቅንጅታዊ ትስስር መፍጠር፤
    - በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶችና ሌሎች ማህበራዊ ዘርፎች ዙሪያ አለማቀፍና አገር አቀፍ በዓላትን ማክበር፤
    - የስርዓተ ፆታ፣ የሴቶች ፎረምና የወጣቶች ፎረም የምክክር መድረክ በአመቱ 2 ጊዜ ማዘጋጀት፤
    - በየሩብ አመቱ የጤናዉ ዘርፍ የሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች መዋቅሮች ጋር የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፤
    - በፆታዊ ጥቃት መከላከልና ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት፤
- **በጤናው ሴክተር የሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮችን አካቶ ተግበራ ማሻሻልና ማጠናከር፤**
    - ለጤና ሴክተር ባለሙያዎች በስርዓተ ፆታ እና ጤና ዙሪያ ስልጠና መስጠት፤
    - የሴቶች ውሳኔ አሰጣጥና ወደ አመራር እንዲመጡ ማብቃት፤
    - የወጣቶችን ጤና ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ማሳደግ፤
    - የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ማሳደግ፤
- ***ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከልና ምላሽ መስጠትን አገልግሎት ማጠናከር፤***
    - *ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከልና ምላሽ ማሳደግ፤*
    - *ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከልና ምላሽ የስልጠና ማዕቀፍ መከለስ፤*
    - *ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከልና ምላሽ ላይ ለባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፤*
    - *የፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽ የአገልግሎት የአንድ ማዕከል ላይ የሚሰጠው አገልግሎት በጥራት ማረጋገጫ መሳሪያ መሰረት ማረጋገጥ፤*
    - በወረዳዎች የፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማስፋፋት፤
    - *የፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት የልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት፤*

- ○ በፆታዊ ጥቃት መከላከልና ምላሽ ላይ የድንገተኛ ጊዜ ለሚመደቡ አዲስ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- **በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች የጤና አገልግሎቱ ለእናቶችና ለህፃናት ምቹ እንዲሆን ማድረግ፤**
  - ○ ከስደት ተመላሾችና የአይምሮ ጤና ዙሪያ ከሚመለከተው አካል ጋር መስራት፤
  - ○ በጦርነት ምክንያት ፆታዊ ጥቃት ለሚደርስባቸው ወገኖች በአካባቢው ካለ ጤና ተቋም ጋር በመተባበር አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፤
  - ○ ፆታዊ ጥቃትን መከላከልና ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ በሁሉም ወረዳዎች ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መስጫ መድረኮችን ማመቻቸት፤
- **የጤና መሰረተ ልማትን ለአካል ጉዳተኞችና ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ምቹ ማድረግ ስራ ለመስራት የሚያስችሉ ስራዎች ማጠናከር፤**
  - ○ መሰረተ ልማቱን የሚያስፋፉ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መስራት፤
  - ○ የፆታዊ ጥቃት ምላሽ መስጫ መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት፤
  - ○ ለመሰረተ ልማቱ ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች ምቹ መሆኑን መከታተል፤

# ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮችና ሊወሰዱ የታሰቡ የመፍትሄ እርምጃዎች

## ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች

- በጤና ተቋማት ቀጣይነት ያለው እና በቂ የሆነ የመድኃኒት አቅርቦተ አለመኖር፤
- በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ የሚከሰተውን የህብረተሰብ መፈናቀል እና ከዚህ ጋር የተያያዘ የወረርሽኝ በሽታ መከሰት፤
- በአዲሱ መዋቅር መሰረት የሚደረገውን ምደባ ሲዘገይ ሰራተኛው ተረጋጋቶ ያለመስራት፤
- በተሰራው አዲሱ መዋቅር የሚመደብ ሰራተኛ ስራው እስኪለምድ የክህሎትና የብቃት ችግር ሊያገጥም ይችላል፤
- በየደረጃው የሰራተኛ ፍስት እና አመራር መቀያየር፤
- በተፈለገው መልክ በየሳምንት፣ በየወር እና በየሩብ አመቱ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ማነስ፤
- በአፈፃፀም ላይ የአመራርና የሰራተኞች አቅም ክፍተት፤
- የኮቪድ 19 በሽታ ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የግብአት ችግሮችና የህብረተሰቡ ቸልተኝነት፤
- የጤና ዲጂታላይዝ ስርዓትን ለማጠናከር በሁሉም ፕሮግራም ዘርፍ እኩል ትኩረት አለመስጠት፤
- የጤና መሰረተ ልማት መጓደል፤
- የታቀዱ ተግባራትን ለማከናወን የበጀት እጥረት የመሳሰሉት ችግሮችና ተግዳሮቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡ ፡

## ሊወሰዱ የታሰቡ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ከሚመለከታቸው አካላትና አጋር ድረጅቶች በመቀናጀት በጤና ተቋማት ቀጣይነት ያለው እና የመድኃኒት አቅርቦተ እንድኖር ጥረት ማካሄድ፤

- አስፈላጊ የሆነና የተቀናጀ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ የሚከሰተውን የህብረተሰብ ችግሮች ለመቀልበስ የሚያስችለ አቅም መፍጠር፤
- የተጀመረውን አዲሱ መዋቅር አቅም በፈቀደ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሰራ ጥረት ማድረግ፤
- በየጊዜው አስፈላጊ ክትትል በማድረግ የክህሎትና የብቃት ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ የተመክሮ ልዉዉጥና ስልጠናዎችን ማመቻቸት፤
- በጤና ቢሮና በወረዳዎች የሚደረገውን የጋራ ስብሰባ የሰራተኛ ፍስት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎችን በጋራ ማቀድና መስራት፤
- በየጊዜው አላስፈላጊ የሆን የአመራር መቀያየር ጋር የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቀነስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት የሚስተካከልበትን ሁኔታ እንዲፈጥር ጥረት ማድረግ፤
- በተፈለገው መልክ በየሳምንት፣ በየወር እና በየሩብ አመቱ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ማጠናከር፤
- በየወሩ፤ በየሩብ አመቱና በየ6 ወሩ የሚደረገው የአፈፃፀም ግምገማ ማጠናከር፤

## የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ

### የልማት ዕቅድና ኢኮኖሚ አስተዳደር ዳይሬክቶረት

### ግንቦት 2015 ዓ.ም

### ሐዋሳ